# አዲስ ዘመን

እናድ

ሰኞ 81ኛ ዓመት ቁጥር 276 ሰኔ 6 ቀን 2014 ዓ.ም ዋጋ 10.00 ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!




ፎቶ፡ ሑዳሽ አብርሐ

# ኮርፖሬሽኑ ያስገነባቸው ቤቶች ለሀገሪቱ አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችን ያስተዋወቁ መሆናቸው ተገለጸ

**ፍቃዱ ዴሬሳ**

አዲስ አበባ፡- በ18 ወራት ውስጥ በሶስት ቢሊዮን ብር በፌዴራል ቤቶች ኮርፖሬሽን የተገነባው የገርጂ ዘመናዊ መኖሪያ መንደር ቴክኖሎጂ፣ ጊዜና ወጪ ቆጣቢ ፕሮጀክት እንደሆነ ተገለፀ ። የቤት አቅርቦት ችግር ለመፍታት የፌዴራል ቤቶች ኮርፖሬሽን ለሀገራዊ የቤት ልማት ፕሮጀክት የበኩሉን አስተዋጽኦ እየተወጣ እንደሚገኝም ተነግሯል ።

የፌዴራል ቤቶች ኮርፖሬሽን በቀበናና ገርጂ አካባቢዎች ያስገነባውን ዘመናዊ ቤቶች አስመርቋል።

የገርጂ ዘመናዊ መኖሪያ መንደር ፕሮጀክት በዓይነቱ በአገራችን ልዩ የመኖሪያ መንደር የሆነና እንደ አገር በመኖሪያ ቤት ግንባታ ዘመኑን የዋጀ አዲስ የግንባታ ቴክኖሎጂ ይዞ የመጣ እንዲሁም የአገራችንን ባለሙያዎች ቴክኖሎጂንና እውቀትን ቀስመው በፍጥነት ተግባራዊ የማድረግ ብቃት ያሳዩበት መሆኑ ተነግሯል ።

የፌዴራል ቤቶች ኮርፖሬሽን ዋና ሥራ አስፈፃሚ አቶ ረሻድ ከማል በምረቃ ሥነ-ሥርዓቱ ላይ ባስተላለፉት

ኮርፖሬሽኑ ያስገነባቸው... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

# የለገሐር አንድ ህንጻ ፕሮጀክት በሲሚንቶ እጥረትና በወሰን ማስከበር ምክንያት ግንባታው መጓተቱ ተገለጸ

**በኃይሉ አበራ**

አዲስ አበባ፡- በኢግል ሂልስ ግዙፍ ፕሮጀክት ምዕራፍ አንድ እየተገነባ የሚገኘው የለገሐር አንድ ህንጻ በሲሚንቶ እጥረትና በወሰን ማስከበር ችግር የተነሳ በሚፈለገው ፍጥነት እየሄደ አለመሆኑ ተገለጸ።

ላጋር ኢግል ሂልስ በአዲስ አበባ ለገሐር የድሮው ባቡር ጣቢያ አካባቢ በ360 ሺህ ካሬ ሜትር ስኩዌር ቦታ ላይ የሚያርፍ 4000 መኖሪያ ቤቶችን የሚይዝ ግዙፍ ግንባታዎች አንዱ ነው። ህንፃው ከለገሐር በስተሰሜን-ምሥራቅ አቅጣጫ የሚገኝ ዓለም አቀፍ ደረጃውን የጠበቀና የማህበረሰቡን የዕለት ተዕለት የጋራ አገልግሎቶችን በቀላሉ ለማግኘት በሚያስችል ቦታ ላይ እየተገነባ የሚገኝ ነው።

በራማ ኮንስትራክሽን ሥር የኢግል ሂልስ ፕሮጀክት የለገሐር አንድ ህንጻ ፕሮጀክት ማናጀር አቶ ዮሐንስ ጌታቸው ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት የሲሚንቶ አቅርቦትና የወሰን ማስከበር ችግሮች በአሰሪ ድርጅቱ በኩል የሚፈቱ ናቸው። እንደ ኮንትራክተር ሲሚንቶ ከውጭ በግዢ በማስመጣት ጭምር ለማቅረብ ጥረት እየተደረገ ነው ብለዋል።

ባለፉት ሶስት ወራት በገጠመው የሲሚንቶ አቅርቦት ችግር እና የቦታ ማጽዳት ሥራዎች መዘግየት ምክንያት ፕሮጀክቱ በሚፈለገው ፍጥነት እየተሰራ አለመሆኑንም ገልጸዋል።



ራማ ኮንስትራክሽን የላጋር አንድ ህንጻ ግንባታን ለማጠናቀቅ 12 ሚሊዮን ዶላር ኮንትራት የተፈራረመ

የለገሐር አንድ ህንጻ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል








# ህብረተሰቡ በክሪፕቶ ከረንሲ ከመገበያየት እንዲቆጠብ ባለሙያዎች አሳሰቡ

**ጌትነት ተስፋማርያም**

አዲስ አበባ፡- ክሪፕቶ ከረንሲ የተሰኘውን ዲጂታል መገበያያ ያላቸው ዜጎች ምናባዊው ገንዘብ ህጋዊ ፍቃድ እስኪያገኝ ድረስ የያዙትን ክሪፕቶ ከረንሲ ወደ ህጋዊ ገንዘብና ዕቃ ቢቀይሩት ይመከራል ሲሉ በአዲስ አበባ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ የሶፍትዌር ኢንጂነሪንግ መምህር ረዳት ፕሮፌሰር ሁሴን ሰይድ አስታወቁ።

ረዳት ፕሮፌሰር ሁሴን ከኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ጋር በነበራቸው ቆይታ፤ ህጋዊ ዕውቅና የሌለውን ክሪፕቶ ከረንሲ ወደዶላርና ወደብር እንዲሁም ወደዕቃ መቀየር ይኖርባቸዋል። ይህም በቅጽበት ምናባዊው ገንዘብ አሰራሩን ቢቀይር አሊያም አገራት ቢያስቆሙት ከሚደርሰው ኪሳራ እራስን ለመጠበቅ ይረዳል ብለዋል።

እንደ አዲስ ቴክኖሎጂ ወደፊት በስፋት ጥቅም ላይ መዋሉ አይቀርም በሚል ተስፋ ብዙዎች ወደዚህ ክሪፕቶ ከረንሲ ግብይት እንደሚገቡ የገለጹት ረዳት ፕሮፌሰር ሁሴን፤ ይሁንና ገንዘባችንን ስናወጣ በብዙ መልኩ ህጋዊ አካሄዱን ማሰብ ይገባናል ሲሉ አስተያየታቸውን ሰጥተዋል።

ክሪፕቶ ከረንሲ ኢትዮጵያ ውስጥ እስካሁን ፍቃድ ያገኘ መገበያያ አይደለም። ይህ ዲጂታል ገንዘብ ጥቅምም እንዳለው ሁሉ አሉታዊ ተጽእኖው ስላለው ህጋዊ ማዕቀፍ ተዘጋጅቶለት እስኪወጣ ድረስ እራስን ከአደጋ መጠበቅ ያስፈልጋል ብለዋል።

በተለይ አገራት የእራሳቸውን ስምምነት አድርገው እስካልተጠቀሙበት ድረስ በምናባዊው ገንዘብ ተማምኖ ለመቆየት አስቸጋሪ መሆኑን መምህሩ ገልጸዋል።

እንደ ረዳት ፕሮፌሰር ሁሴን ሃሳብ ከሆነ፤ አንድ አገር የወረቀት ገንዘብ አትሞ ሲያሰራጭ በወርቅ ክምችት ተግባብቶ ነው ገንዘቡን ወደሥራ የሚያስገባው። ክሪፕቶ ከረንሲውን የሚያሰራጭ ሰው ግን ካለምንም ዓለም አቀፍ ስምምነት መገበያያ ብሎ የሚያከፋፍለው እራሱ ያዘጋጃቸውን የኮምፒዩተር ኮዶችን ነው።

ባለቤቱ የኮምፒዩተር ኮዶቹን ለተለያዩ ሰዎች እያከፋፈለ በአንጻሩ ደግሞ ህጋዊ ገንዘቦችን የሚሰበስብበትና ሃብትን በእጁ የሚያስገባበት መንገድ እየሰፋ መሄዱ ደግሞ አይቀርም ብለዋል።

ህብረተሰቡ በክሪፕቶ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል







ክረምትን ለበጎነት ገጽ 7

እድልና ተስፋን ይዞ የመጣው የዲጂታል ትምህርት ማዕከል ገጽ 9



# በመተከል ዞን በተፈጠረው አንጻራዊ ሰላም አርሶ አደሩ ወደ ግብርና ሥራው እየተመለሰ ነው

**ሙሳ ሙሐመድ**

አዲስ አበባ፡- በመተከል ዞን በተፈጠረው አንጻራዊ ሰላም አርሶ አደሩ ወደ ግብርና ሥራው እየተመለሰ መሆኑን የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል ግብርናና ተፈጥሮ ሀብት ልማት ቢሮ ገለጸ ።

የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል ግብርናና ተፈጥሮ ሀብት ልማት ምክትል ቢሮ ኃላፊ አቶ በቀለ አንበሳ እንደገለጹት፣ በዞኑ ከመኖሪያ ቀዬአቸው ተፈናቅለው በአቅራቢያው በሚገኙት የአማራ ክልል ወረዳዎችና በቀርበት ባሉት የዞኑ ወረዳዎች ተጠልለው የነበሩ ነዋሪዎችና አርሶ አደሮች አሁን ላይ ወደ እርሻ ሥራቸው እየተመለሱ መሆኑንም ጠቁመዋል ።

እንደ አቶ በቀለ ገለጻ፣ የጸጥታ ችግር በነበረባቸው የመተከል ዞን አሁን ላይ በተገኘው ሠላምና መረጋጋት አርሶ አደሩ ወደ እርሻ ሥራው ከመመለስ ባሻገር ምርጥ ዘርና ማዳበሪያ እየቀረበ ነው ።

ሆኖም የምርጥ ዘርና የማዳበር አቅርቦት እጥረት ማጋጠሙንና ለዘር አገልግሎት የሚሆን የምርጥ ዘር አቅርቦት እጥረትን ለመቅረፍ ክልሉ ጉዳዩ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን እየሰራ መሆኑን ተናግረዋል ።

አቶ በቀለ እንዳሉት በምርት ዘመኑም በመተከል ዞን ከሚታረሰው 456 ሺህ 455 ሄክታር መሬት 14 ሚሊዮን 81 ሺህ 455 ኩንታል ምርት እንደሚሰበሰብ ይጠበቃል።

የአርሶ አደሩን ምርትና ምርታማነት ለማሳደግ በሚደረገው ጥረት አጋር ድርጅቶች ድጋፍ እያደረጉ መሆኑን አቶ በቀለ ጠቅሰው፣ ድርጅቶቹ እያደረጉት ያለውን ሁለንተናዊ ድጋፍ አጠናክረው እንዲቀጥሉም ጠይቀዋል ።

ድርጅቶቹ እያደረጉት ያለው ድጋፍም በቴክኖሎጂ፣ በትራክተር፣ በምርጥዘር አቅርቦት፣ እና በሌሎችም ዘርፎች መሆኑን አቶ በቀለ አመላክተዋል ።

የአርሶ አደሩን ምርታማነት ለማሳደግ ከዚህ ቀደም የግብዓት አቅርቦትና የማሰልጠኛ ተቋማትን የመገንባት ብሎም ሙያዊ ስልጠናዎች ሲሰጡ መቆየታቸውን የገለጹት አቶ በቀለ፣ ይህም ለቀጣይ የግብርና ሥራ አጋዥ እንደሚሆን ተናግረዋል ።

በመተከል ዞን በተገኘው አንጻራዊ ሰላምም በዞኑ በትምህርት፤ በውሀ ፤በጤና እና በግብርና የልማት ሥራዎች ላይ ትኩረቱን አድርጎ እየሰራ መሆኑን ጠቁመዋል ።

ባለፉት ዓመታት በክልሉ 903 ባለሃብቶች በእርሻ ዘርፍ የተሰማሩ ቢሆንም በተለይ በመተከል ዞን በተፈጠረው አመረጋጋት፣ በፀጥታና በተለያዩ ምክንያቶች ባለሃብቶቹ እንዲያለሙ በሚፈለገው ልክ ወደ እርሻ ሥራ ገብተው እንዳላለሙ አቶ በቀለ ጠቅሰዋል ።

አቶ በቀለ አያይዘውም፣ በመተከል ዞን በሠላም እጦት ተቋርጦ የነበረው የፖዌ ወረዳ ጥቁር ውሃ አነስተኛ መስኖ ግንባታ መቀጠሉን ተናግረዋል ።

# ለከተሞች ዘላቂ ሰላም መረጋገጥ የሃይማኖት አባቶችና የሀገር ሽማግሌዎች እገዛ ወሳኝ መሆኑ ተገለጸ

አዲስ አበባ፡- ለከተሞች ዘላቂ ሰላም መረጋገጥ የሃይማኖት አባቶችና የሀገር ሽማግሌዎች እገዛ ወሳኝ መሆኑን የአማራ ክልል ርዕሰ መስተዳድር ዶክተር ይልቃል ከፋለ ገለጹ፡፡

ርዕሰ መስተዳድሩ በጎንደር ከተማ ከሃይማኖት አባቶችና ከሀገር ሽማግሌዎች ተወካዮች ጋር በወቅታዊ ጉዳይ እየመከሩ ነው።

በጎንደር ከተማ ባለፈው ጊዜ የሃይማኖትን ሽፋን መሰረት አድርጎ የተፈጠረው ችግር ከዚህ የከፋ ጉዳት ሳይደርስ እንዲቀለበስ በተደረገው ጥረት የሀገር ሽማግሌዎችና የሃይማኖት አባቶች እገዛ ከፍ ያለ ነበር ብለዋል።

በተመሳሳይ ከአሁን ቀደም ተፈጥሮ በነበረው ግጭት ከአካባቢያቸው ተፈናቅለው የነበሩ ዜጎችን መልሶ ለማቋቋም በተደረገው ጥረት የሃይማኖት አባቶችና የሀገር ሽማግሌዎች የማይተካ ሚና ተጫውተዋል ብለዋል ርዕሰ መስተዳድሩ።

በክልሉ የሚገኙ ከተሞችን ሰላም አስተማማኝ በማድረግ ለተሻለ ዕድገት እንዲተጉ ለማድረግ የተለያዩ ተቋማት አደረጃጀቶች አበክረው እንዲሰሩ ጠይቀዋል።






ዶክተር ተሾመ አዱኛ

# በኦሮሚያ ክልል ሦስት ሺህ 588 የኢንቨስትመንት ጥያቄዎች ተቀባይነት አግኝተዋል

**አዲሱ ገረመው**

አዲስ አበባ፡- በተያዘው የበጀት ዓመት በኦሮሚያ ክልል ሦስት ሺህ 588 የኢንቨስትመንት ፕሮጀክት ጥያቄዎች መልስ ማግኘታቸውን የክልሉ ኢንቨስትመንት ቢሮ አስታወቀ ። በክልሉ የኢንቨስትመንት እንቅስቃሴ የለም ተብሎ የሚወራውም ሀሰት መሆኑንም ቢሮው አስተባብሏል ።

የኦሮሚያ ክልል ኢንቨስትመንት ቢሮ ኃላፊ ዶክተር ተሾመ አዱኛ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንዳስታወቁት፤ የኦሮሚያ ክልል ኢንቨስትመንት ቦርድ በተያዘው የበጀት ዓመት ለሦስት ሺህ 588 ኢንቨስተሮች መሬት ተሰጥቷቸው ወደ ሥራ እንዲገቡ ወስኗል ። ከአንድ ሺህ በላይ አዳዲስ ባለ ሀብቶችም የኢንቨስትመንት ፍላጎት አሳይተዋል ።

ዶክተር ተሾም እንዳሉት፤ ቢሮው ባለፉት አስር ወራት ውስጥ በተለያዩ የኢንቨስትመንት መስኮች በአገር ውስጥና በውጭ አገራት ባለሀብቶች የቀረቡ ሦስት ሺህ 588 የኢንቨስትመንት ጥያቄዎችን መልስ በመስጠት አጽድቋል ። ጥያቄ ከቀረበባቸው ፕሮጀክቶች መካከል አብዛኞቹ በአፈጻጸም ደረጃ የተሻሉ ሆነው የተገኙ ናቸው።

ኃላፊው ከላይ ከተጠቀሱት የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች በተጨማሪ ከ1000 በላይ አዳዲስ ባለሀብቶች የኢንቨስትመንት ፍላጎት ማቅረባቸውን ጠቅሰዋል ። ከመካከለኛው ምሥራቅ አገሮች፣ ከአውሮፓ፣ ከአሜሪካ እና ከሌሎችም የዓለም አካባቢዎች የተውጣጡ የሜጋ ዓለም አቀፍ የኢንቨስትመንት ኩባንያዎች ወደ ክልሉ ገብተው ኢንቨስት ለማድረግ እየገቡ እንደሆነም ጠቁመዋል ። በክልሉ የኢንቨስትመንት እንቅስቃሴ የለም ተብሎ የሚወራውም ሀሰት መሆኑን አስተባብለዋል ።

በክልሉ በርካታ ባለሀብቶችን በኢንቨስትመንቱ ለመሳብ የተለያዩ ምቹ ሁኔታዎችን በመፍጠር በርካታ ተግባራት እየተከናወኑ እንዳለ ኃላፊው አስረድተዋል። የክልሉ ባለሀብቶች በተለያዩ ንዑስ ዘርፎች ማለትም በግብርና፣ በአግሮ ፕሮሰሲንግ፣ በአትክልትና ፍራፍሬ፣ በጨርቃጨርቅና አልባሳት፣ በሆቴልና ቱሪዝም እንዲሁም በሌሎች መስኮች ኢንቨስት ማድረግ እንዲችሉ ምቹ ሁኔታ ተፈጥሯል ብለዋል ።

በተለያዩ አካባቢዎች በተከሰቱ ግጭቶች ምክንያት አለመረጋጋት እንደነበር፤ የውጭ ምንዛሪ እጥረትና አንዳንድ የኢንዱስትሪ ግብዓቶች እጥረትም አጋጥሞ እንደነበር ኃላፊው ገልጸዋል ። ይህም በክልሉ የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶችን በማደናቀፍ ትልቅ ተግዳሮት ፈጥሮ መቆየቱን ነው ያስታወቁት ። በአሁኑ ወቅት ግን የኢንቨስትመንት ፍሰቱ በጥሩ ሁኔታ ላይ እንዳለ አመላክተዋል ። ከተለያዩ አገራት በርካታ ኢንቨስተሮች ወደ ክልሉ እየመጡ ነው ብለዋል ።

በአሁኑ ወቅት ግብርና፣ ቱሪዝምና ኢንዱስትሪን ጨምሮ በሁሉም ሴክተር ለውጭ ኢንቨስተሮች ሊሆን የሚችል ምቹ አጋጣሚ እንዳለ የጠቀሱት ኃላፊው፤ አሠራርን በማዘመንና ተገልጋዮች ባሉበት ቦታ ሆነው መገልገል እንዲችሉ ለኢንቨስተሮች የኦን ላይን አገልግሎትም እየተሰጠ ይገኛል ነው ያሉት ።

ኃላፊው፤ ቢሮው የነባር ኢንዱስትሪዎችን የማምረት አቅም ለማሳደግ የተለየ ትኩረት በመስጠት ችግር ፈቺ ክትትልና ግምገማ በማድረግ እየሰራ መሆኑን ጠቁመዋል። በሌላ መልኩ ምርት ያልጀመሩ 80 ኩባንያዎች የመሬት ፍቃዳቸው ተሰርዞ መሬቶቹ ወደ መሬት ባንክ መተላለፋቸውን ተናግረዋል ።

# የመንግሥት ሰራተኞችን ባዶ የምሳ እቃ ያስያዘው የኑሮ ውድነት

**ዳግማዊት ግርማ**

አዲስ አበባ፡- እጅ ለአፍ ያጥራል ሲባል ተረት ይመስል ነበር፤ ብዙ እጆች ግን ከገዛ አፋቸው ተራርቀዋል ።ዘመኑ ሰውና ኑሮው የተራራቁበት ፤ብዙዎች በልተው ለማደር የሚፈተኑበት ጊዜ ላይ ደርሰናል ፡፡

በኑሮ መወደድ ምክንያትነት ብዙ ነጠላ ዘርግተው ገንዘብ የሚለምኑ አዳዲስ ነዳያን፣ እህቴን አጎቴን እናቴን አባቴን አሞብኛል ብለው ገንዘብ የሚሰጧቸውን ብሩካንን የሚጠባበቁ እጆች፣ የትራንስፖርት ቸግሮኛል ሙላልኝ የሚሉ ብዙ ሰዎች ማየት የተለመደ ነገር እየሆነ መጥቷል፡፡

ኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት የአዲስ አበባ ከተማ ነዋሪዎችን የኑሮ ነገር እንዴት አደረጋችሁ ሲል ጠይቋል፤ ድርጅታችን በዚህ ጥያቄው ምክንያት ብዙ የተከፉ ፊቶች እልፍ የዳመኑ ገፆችን አስተናግዷል፡፡

ሸማቾች ለኑሮ ውድነቱ መባባስ ጣታቸውን በነጋዴው ላይ ሲጠቁሙ ነጋዴዎችም በሌሎች ነጋዴዎች ላይ እጃቸውን ሲቀስሩ ታዝበናል ።የመንግሥት አካላትም የኑሮው መወደድ በኢትዮጵያ ላይ ብቻ ሳይሆን በመላው ዓለም በሚገኙ ሀገራት ላይ የተደቀነ ፈተና መሆኑን ገልጸው፤ መንግሥት ጉዳዩን በትኩረት እየሰራበት እንደሚገኝና የቤት ሥራውን እየተወጣ እንደሚገኝም ነግረውናል፡፡

ወይዘሮ ሃና ጌታቸው ትባላለች፤ መተዳደሪያዋን በመንግሥት ሰራተኝነት አድርጋ ነው የምትኖረው፤ ወይዘሮ ሃና እንደነገረችን ኑሮ በአዲስ አበባ እየከበደ መጥቷል፤ ሸቀጣሸቀጥ፣ የሴቶች ንፅህና መጠበቂያዎች፣ መብል መጠጥ ሁሉ ለመግዛት አዳጋች ሆኗል ፡፡

መንግሥት ከወር እስከ ወር ተዳደሪበት ብሎ የሚከፍላት ክፍያና ለመኖር የሚያስፈልጋት ገንዘብ መጠን የሰማይና የምድር ያህል ተራርቀዋል፤ የመንግሥት ክፍያ ለቤት ኪራይ ክፍያም አይበቃ ትላለች፡፡

የወይዘሮዋ ምስኪን ልብ ሕይወት ለመንግሥት ሰራተኞች በዚህ ልክ ካስቸገረ በዝቅተኛ ገቢ ለሚተዳደሩ ሰዎች ደግሞ የበለጠ አስቸጋሪ እንደሚሆን በማሰብም ይጨነቃል፡፡

ሌላው የከተማዋ ነዋሪና በኑሮ ውድነት መማረሩን የገለጸው ደረጄ አብዲሳ በበኩሉ፤ አብዛኛው ሰው የሚበላው ምግብ እስከማጣት ድረስ መቸገሩን ቁርስ፣ ምሳና ራት መብላት የከበደበት ጊዜ ላይ መደረሱን ገልጾ፤ የኑሮው ውድነት የመንግሥት ሰራተኞችን ባዶ ምሳ እቃ እየያዙ ቢሯቸው እስከመሄድ እንዳደረሳቸውም ነግሮናል።

አቶ አብዲሳ በከተማዋ በየቀኑ የሚጨምር የህዝብ ብዛት፣ የህገወጥ ነጋዴዎች መፈልፈልና ሌሎችም እልፍ ጉዳዮች መኖር በየቀኑ እየናረ ለሚመጣው የኑሮ ውድነት በምክንያትነት ያነሳሉ ።

ሌላኛው አስተያየት ሰጪያችን ደረጄ አለምሸትም የኑሮው ውድነት እንደ ማንኛውም ኢትዮጵያዊ አሳስቧቸዋል ።በስግብግብ ነጋዴዎች ምክንያት የፍጆታ እቃዎች በተጋነነ ዋጋ መጨመር፣ መሰረታዊ ፍላጎት የቅንጦት ያህል መታየታቸው ሕይወትን እያከበደው እንደሚገኝም ተናግረዋል፡፡

ከሸማቾቹም ባሻገር ነጋዴዎቹም የኑሮ ውድነቱ ፈትኖናል እያሉ ነው ።የሴቶች ውበት መጠበቂያ ቁሳቁሶችን በመሸጥ የምትተዳደረው ወጣት የአብስራ ንጉሱ ከአከፋፋዮች ስናመጣ በውድ እየገዛን በትንሽ ትርፍ ነው እየሸጥን ያለነው ትላለች፡፡

ህብረተሰቡም ከሚመገበው ነገር ተርፎት ለውበት መጠበቂያ ቁሳቁሶች መግዣያ የሚሆን አቅም እንዳጣም ትናገራለች ።

የተለያዩ አልባሳትን በመሸጥ የሚተዳደረው አቶ እዮብ በበኩሉ የኑሮ ውድነቱ እኛን ነጋዴዎችንም ይነካናል ይላል ። አቶ እዮብ ለኑሮ ውድነቱ ከእነሱ በላይ ያሉ ነጋዴዎችን ተጠያቂ አድርጓል ።

አቶ እዮብ መንግሥት አንዳንድ ሸቀጦች ላይ ጣልቃ በመግባት ነጋዴውም ከዚህ በላይ እንዳትሸጥ ህብረተሰቡም ከዚህ በላይ እንዳትገዛ ተብሎ መታገድ አለበት ብሎ ማወጅ እንደሚጠበቅበትም ነግረውናል፡፡

የአዲስ አበባ ንግድ ቢሮ ምክትል ኃላፊ አቶ መስፍን አሰፋም የኑሮ ውድነት መስፋፋቱን አመላክተው የዋጋ ንረቱ ዋንኛ ምክንያቶች ዓለም አቀፋዊ ናቸው ብለዋል ።መንግሥት ኑሮውን ለማሻሻል ብዙ የቤት ሥራዎችን በመወጣት ላይ ነው፤ የከተማ ግብርናን ማስፋፋት፣ የእሁድ ገበያዎችና የመሰረታዊ ፍጆታ እቃዎች ላይ ያስቀረውን ታክስም ለአብነት ገልጸዋል፡፡

# በዘንድሮው የበጎ ፈቃድ አገልግሎት 11 ቢሊዮን ብር የሚደርስ ወጪ ለማዳን መታቀዱን ፌዴሬሽኑ አስታወቀ

## • በበጎ ፈቃድ አገልግሎቱ ከ19 ሚሊዮን በላይ ወጣቶች እንደሚሳተፉ ይጠበቃል

**ፋንታነሽ ክንዴ**

አዲስ አበባ፡- በ2014 ዓ.ም የክረምት በጎ ፈቃድ አገልግሎት መንግሥትና ሕብረተሰቡ ሊያወጡ የሚችሉትን 11 ቢሊዮን ብር የሚደርስ ወጪ ለማዳን መታቀዱን የኢትዮጵያ ወጣቶች ፌዴሬሽን አስታወቀ።በሚሰጠው የበጎ ፈቃድ አገልግሎት በመላው አገሪቱ የሚገኙ ከ19 ሚሊዮን በላይ ወጣቶች እንደሚሳተፉም ተጠቆመ፡፡

የኢትዮጵያ ወጣቶች ፌዴሬሽን ጽህፈት ቤት ኃላፊ አቶ ሙሐዲን ናስር አህመድ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በ2014 ዓ.ም የክረምት በጎ ፈቃድ አገልግሎት በ11 የተለያዩ ዘርፎች በሁሉም ክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች ይሰጣል ።በሚከናወነው የበጎ ፈቃድ አገልግሎት መንግሥትና ሕብረተሰቡ ሊያወጡ የሚችሉትን 11 ቢሊዮን ብር የሚደርስ ወጪ ለማዳን መታቀዱን ጠቁመዋል፡፡

ባለፈው ዓመት በተከናወነው የበጎ ፈቃድ አገልግሎት 19 ሚሊዮን ወጣቶችን ለማሳተፍ ታቅዶ 23 ሚሊዮን ገደማ ወጣቶች የበጎ ፈቃድ አገልግሎት ላይ መሳተፋቸውን ያስታወሱት ጽህፈት ቤት ኃላፊው፤ በዚህም መንግሥትና ሕዝብ ሊያወጡ ይችሉ የነበረውን 12 ቢሊዮን ብር ማዳን ተችሏል ።በዘንድሮው የክረምት በጎ ፈቃድ አገልግሎት በሚሳተፉ ከ19 ሚሊዮን በላይ ወጣቶችም እስከ 11 ቢሊዮን ብር የሚደርስ ወጪ ለማዳን የሚያስችል አገልግሎት ለመስጠት ዝግጅት መደረጉን አስታውቀዋል፡፡

አገልግሎቱን በተቀናጀ መልኩ ለመስጠት እቅድ የማዘጋጀትና ሌሎችም አስፈላጊ የቅድመ ዝግጅት ሥራዎች ተከናውነዋል ያሉት አቶ ሙሐዲን፤ የተዘጋጀው እቅድም ለሁሉም ክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች ለሚገኙ የፌዴሬሽን አደረጃጀትና ባለድርሻ አካላት እንዲወርድ የማድረግ ተግባር ተከናውኗል ብለዋል ።

ከጊዜ ወደ ጊዜ ወጣቶች በጎ ፈቃድ ላይ ያላቸው ግንዛቤ ከፍ እያለ በመምጣቱ ከዓመት ዓመት በጎ አድራጎት ሥራዎች ላይ የሚሳተፉ ወጣቶች ቁጥር እየጨመረ መጥቷል ያሉት አቶ ሙሐዲን፤ የዘንድሮው የክረምት በጎ ፈቃድ አገልግሎት ከሰኔ 15 ቀን 2014 ዓ.ም ጀምሮ እስከ መስከረም 30 ቀን 2015 ዓ.ም የሚቀጥል ይሆናል ።አገሪቱ ካለባት ዘርፈ ብዙ ችግሮች አንጻር ሁሉም ወጣቶች በዘንድሮው በጎ ፈቃድ አገልግሎት በመሳተፍ የበኩላቸውን አገራዊ ኃላፊነት



እንዲወጡ ጥሪ አቅርበዋል፡፡

በዘንድሮው የክረምት በጎ ፈቃድ አገልግሎት አረንጓዴ አሻራ፣ የአካባቢ ጥበቃ፣ ሰላም፣ መንገድ ደህንነት፣ ኮቪድ 19 መከላከልና ሌሎችም ጤና አጠባበቅ ሥራዎች፣ ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶችን ለማስቀረት ግንዛቤ መፍጠር ላይ ትኩረት አድርጎ እንደሚሠራ የተገለጸ ሲሆን፤ በተጨማሪም የማጠናከሪያ ትምህርት መስጠት፣ የአረጋውያንና አቅመ ደካሞች ቤት እድሳት፣ ህገወጥ የሰዎች ዝውውር ላይ መከላከልና ግንዛቤ ፈጠራ መሥራትን ጨምሮ በሌሎችም አሥራ አንድ ዘርፎች ላይ ያተኮረ አገራዊ የበጎ ፈቃድ አገልግሎት እንደሚሰጥ ከኢትዮጵያ ወጣቶች ፌዴሬሽን ያገኘነው መረጃ ያመለክታል፡፡

# ዓለም አቀፉ ማኅበረሰብ ለአፋር ሕዝብ ትኩረቱን እንዲሰጥ ጥሪ ቀረበ

## • 1ነጥብ 3 ሚሊዮን ህዝብ የዕለት እርዳታ ይፈልጋል

**አብዱረዛቅ መሐመድ**

ሰመራ፡- ዓለም አቀፉ ማኅበረሰብ በሕወሓት የሽብር ቡድን ጉዳት ለደረሰበት የአፋር ክልልና ሕዝብ ትኩረቱን እንዲሰጥና እያደረገው ያለውን ድጋፍ አጠናክሮ እንዲቀጥል የአፋር ክልል አደጋ መከላከልና የምግብ ዋስትና ፕሮግራም ማስተባበሪያ ጽሕፈት ቤት ጥሪ አቀረበ።

በተያያዘ ዜና፣ የኢትዮጵያ ሕዝብ በሕወሓት የሽብር ቡድን ወረራ ምክንያት በችግር ውስጥ ላለው ለአፋር ክልልና ሕዝብ ላሳየው አጋርነት ጽሕፈት ቤቱ ምስጋናውን አቅርቧል።

የጽሕፈት ቤት ዋና ኃላፊ አቶ መሐመድ ሁሴን ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደተናገሩት፤ ሁለት ሚሊዮን ከሚሆነው የአፋር ሕዝብ አንድ ነጥብ ሦስት ሚሊዮን ያህሉ በተለያዩ ምክንያቶች የእለት ደራሽ እርዳታ ጠባቂ ሆኗል። የእነዚህ ተረጂዎች ፍላጎት በመንግሥት አቅም ብቻ የሚሸፈን ባለመሆኑ ዓለም አቀፉ ማኅበረሰብ ለጉዳዩ ትኩረት ሰጥቶ እያደረገው ያለውን ድጋፍ አጠናክሮ እንዲያስቀጥል አቶ መሐመድ ጥሪያቸውን አቅርበዋል።

እንደዋና ኃላፊው ገለጻ፤ በሕወሓት የሽብር ቡድን ወረራ፣ በድርቅ፣ በጎርፍ አደጋ፣ በአንበጣ መንጋና በሌሎችም ምክንያቶች በክልሉ የምግብ ዋስትናቸው ጥያቄ ውስጥ የገባ ዜጎች ቁጥር አንድ ነጥብ ሦስት ሚሊዮን ደርሷል።

በሽብር ቡድኑ ወረራ ምክንያት ከተፈናቀሉ ስድስት



ፎቶ - እዮብ ተፈራ

መቶ 45 ሺህ ዜጎች ሦስት መቶ ስምንት ሺህ ተፈናቃዮች ወደ ቀዬአቸው ተመልሰዋል፤ በአሁኑ ሰዓት ሦስት መቶ 36 ሺህ ተፈናቃዮች በክልሉ ባሉ 17 ጊዜያዊ መጠለያ ጣቢያዎች ውስጥ ይገኛሉ ብለዋል።

የክልሉ መንግሥት ከፍተኛ በጀት በመመደብ በምግብ፣ በውሃ፣ በሕክምና፣ በመጠለያና ሌሎችም ቁሳቁሶች አቅርቦት አቅሙ የፈቀደውን ሁሉ አድርጓል ያሉት ዋና ኃላፊው፤ "ችግሩ ከአቅማችን በላይ ሲሆንብን ለብሔራዊ የአደጋ ስጋት ሥራ አመራር ኮሚሽን ጥሪ አቅርበን የፌዴራል መንግሥትም የሚችለውን ሁሉ አድርጓል፤ እያደረገም ይገኛል" ሲሉ ገልጸዋል።

ክልሉ ያለበትን ዘርፈ-ብዙ ችግሮች በተመለከተ ከሀገር በቀልና ዓለም አቀፍ ግብረ-ሰናይ ድርጅቶች ጋር ባለው የጋራ ፎረም አማካኝነት በተቀናጀ ጥናት ላይ ተመስርቶ ለተቋማቱ ጥያቄ ማቅረቡን የተናገሩት አቶ መሐመድ፤ ከፌዴራል መንግሥት ጋር በመናበብ ዓለም አቀፍ የእርዳታ ድርጅቶች ለአፋር ሕዝብ አጋርነታቸው እንዲያሳዩ ለማድረግ በትኩረት እየተሠራ መሆኑን አስረድተዋል፤ በዚህም መሰረት ዓለም አቀፍ ተቋማት ጥሩ ምላሽ እንደሰጡም አቶ መሐመድ አክለው ገልጸዋል።

የእለት ደራሽ እርዳታ ከሚፈልገው አንድ ነጥብ ሦስት ሚሊዮን ወይም ሁለት ሦስተኛው የክልሉ ሕዝብ ውስጥ ተደራሽ የተደረገው ዘጠኝ መቶ 60 ሺህ የሚሆነውን ብቻ መሆኑን ጠቅሰው፤ ከዚህ ውስጥ የዓለም የምግብ ፕሮግራም ስድስት መቶ 68 ሺህ የሚሆነውን ሕዝብ እየረዳ እንደሚገኝም አብራርተዋል።

እንደአቶ መሐመድ ገለጻ፤ በክልሉ የእለት ደራሽ እርዳታ ጠባቂ ከሆነው ሕዝብ ውስጥ ሦስት መቶ 40 ሺህ ያህሉ እስካሁን ተደራሽ አልተደረገም፤ ዓለም አቀፍ የረድዔት ድርጅቶች ለትግራይ ሕዝብ እየሰጡት ያለውን ትኩረት ለአፋር ሕዝብም በመስጠት ድጋፋቸውን አጠናክረው ሊቀጥሉ ይገባል።

የኢትዮጵያ ሕዝብና የፌዴራል መንግሥት ተቋማት እንዲሁም ሀገር በቀል የእርዳታ ድርጅቶች ለአፋር ክልልና ሕዝብ ላሳዩት አጋርነት ክልሉ ከፍተኛ ምስጋና ያቀርባል ሲሉ ዋና ኃላፊው ገልጸዋል።

የበራህሌ ወረዳ ተፈናቃዮች እርዳታ አስተባባሪ አቶ መሐመድ ሙሳ በበኩላቸው፤ ከመንግሥት በተጨማሪ በዓለም የምግብ ፕሮግራም፣ ቀይ መስቀል ኮሚቴ እና በሌሎችም ሀገር በቀልና ዓለም አቀፍ የእርዳታ ድርጅቶች አማካኝነት ለተፈናቃዮች ስንዴ፣ ሩዝ፣ ፉርኖ ዱቄት፣ ዘይት፣ አተር፣ የምግብ ማብሰያና ሌሎችም እርዳታዎች እየቀረቡ መሆኑን ገልጸው፤ ባለፉት ሁለት ወራት የእርዳታ አቅርቦቱ እየተቀዛቀዘ መሆኑን አስረድተዋል።

የተፈናቃዮች የምግብ ፍላጎት ለማሟላትና በዘላቂነት ለማቋቋም ሁሉም ባለድርሻ አካላት ሊረባረቡ ይገባል ሲሉ ጥሪ አቅርበዋል።

መንግሥት ለተፈናቃዮች የቻለውን ሁሉ እያደረገ ይገኛል ያሉት አቶ አሕመድ ኢብራሂም ናቸው። አቶ አሕመድ የኮነባ ወረዳ ነዋሪ ሲሆኑ በሽብር ቡድኑ ወረራ ምክንያት አካባቢያቸውን ለቀው ዱብቲ መጠለያ ካምፕ ከገቡ ሁለት ወራት ተቆጥረዋል።

የክልሉ ሕዝብና መንግሥት፣ መንግሥታዊና መንግሥታዊ ያልሆኑ ተቋማት ድጋፍ ለሚሹ ዜጎች ድጋፍ እያደረጉ ይገኛል ያሉት አቶ አሕመድ፤ "ይህ ማለት ግን ፍላጎታችን ተሟልቷል፤ ጥያቄያችን ሁሉ ተመልሷል ማለት አይደለም" ብለዋል።

በዱብቲ መጠለያ ጣቢያ ላሉ ተፈናቃዮች የዱቄት፣ ስንዴ፣ ዘይት፣ ስኳር፣ የምግብ ማብሰያና ሌሎችም ድጋፎች እየተደረገላቸው መሆኑን ጠቅሰው፤ በቂ ባይሆንም የሕክምና አገልግሎት እያገኙ እንደሆነም አብራርተዋል።

"የዱብቲ ሕዝብ የችግራችን ተካፋይ ሆኗል፤ ግብረ-ሰናይ ድርጅቶችም እየረዱን ይገኛሉ" ያሉት አቶ አሕመድ፤ የረድዔት ድርጅቶች ከመንግሥት ጋር በመተባበር ድጋፋቸውን አጠናክረው ሊቀጥሉ ይገባል ሲሉ ጥሪ አቅርበዋል።

# ኢትዮጵያ የራሷን ሳተላይት በማበልጸግ ከዘርፉ ተጠቃሚ መሆን እንዳለባት ተገለጸ

**ሞገስ ጸጋዬ**

አዲስ አበባ፡- ከለውጡ ማግስት ጀምሮ መንግሥት ለስፔስ ሳይንስ ትኩረት የሰጠ በመሆኑ ኢትዮጵያ የራሷን ሳተላይት በማበልጸግና በዘርፉ የጠለቀ እውቀትን በማዳበር ከዘርፉ ተጠቃሚ መሆን እንዳለባት የኢትዮጵያ ስፔስ ሳይንስ ሶሳይቲ አስታወቀ ።በትናንትናው ዕለት የኢትዮጵያ ስፔስ ሳይንስ ሶሳይቲ 17ተኛ ጠቅላይ ጉባኤውን አካሂዷል ።

በጉባዔው ላይ የተገኙት የኢትዮጵያ ስፔስ ሳይንስ ሶሳይቲ ቦርድ ሊቀመንበር ወይዘሮ መሰንበት ሸንቁጤ እንደገለጹት፤ ኢትዮጵያ ለእርሻ፣ ለተለያዩ ልማቶችና ለአየር ንብረት ቁጥጥር ስፔስ ሳይንስ ጥቅም በኪራይ ነው የምታገኘው ። ለዚህም ከፍተኛ የሆነ መዋዕለነዋይ ታወጣለች ። ወደፊት የራሷን ሳተላይት በማበልጸግ፣ በማሳደግና በዘርፉ የጠለቀ እውቀትን በማዳበር ከዘር ተጠቃሚ መሆን አለባት ብለዋል ።

ከለውጡ በኋላ ዘርፉን ለማሳደግ ከፍተኛ እንቅስቃሴ ተደርጓል ያሉት ሊቀመንበሯ፤ ነገር ግን በኮቪድ 19 ወረርሽኝና በጦርነቱ ሳቢያ የተወሰነ ተስተጓጉሏል ።በመንግሥት ትልቅ ትኩረት የሰጠው በመሆኑ ወደፊት ከዘርፉ ብዙ ተጠቃሚ መሆን እንደሚቻል አስረድተዋል።



የስፔስ ሳይንሱ ዋና አላማው ግንዛቤ ማስጨበጥ ነው ያሉት ሊቀመንበሯ፤ ከፍተኛ የሆነ የግንዛቤ ማስጨበጥ ሥራ በመስራት መንግሥት ለዘርፉ ትኩረት እንዲሰጠው ማድረግ ተችሏል ። የኢትዮጵያ ስፔስ ሳይንስ ሶሳይቲ ኢትዮጵያ ወደ ስፔስ ሳይንስ ልማት እንድታተኩር ተተኪዎችን በማፍራት፣ ኢትዮጵያን በዓለም አቀፍ ደረጃ በማስተዋወቅ፣ የዘርፉ ምሁራን በማሳተፍና ስለ አስፈላጊነቱ በማስረዳት ስለ እስፔስ ሳይንስ ያለውን የተሳሳተ ግንዛቤ በማረም ወደ ልማት ለመቀየር እንዲቻል በርካታ ሥራዎች መሰራታቸውን ገልጸዋል። እንዲሁም ሶሳይቲው የኢትዮጵያ ስፔስ ሳይንስ አዋጅ እንዲወጣ፣ ኢንስቲትዩት እንዲቋቋምና ተተኪዎች እንዲኖሩ ከፍተኛ ሚና መጫወቷን አስረድተዋል ።

የስፔስ ሳይንስ ሶሳይቲ የቦርድ አባል ዶክተር ቱሉ በሻ በበኩላቸው እንደገለጹት፤ የኢትዮጵያ ስፔስ ሳይንስ ከተቋቋመበት ጊዜ አንስቶ የተለያዩ መድረኮችን በመፍጠር ኢትዮጵያ ለዘርፉ ተገቢውን ትኩረት እንድትሰጥ የግንዛቤ ፈጠራ ሥራ ሲሰራ ቆይቷል ። በተለያዩ ዩኒቨርሲቲዎች ከሰላሳ በላይ ቅርንጫፎችን በማቋቋም የስፔስ ሳይንሱ ጠንካራ ተቋም እንዲሆን እየሰራ ይገኛል ብለዋል ። የስፔስ ሳይንስና ፕሮግራም ጠንክሮ እንዲሄድ ለማድረግ መንግሥትም ለዘርፉ ከፍተኛ ትኩረት እንዲያደርግ የሳይንቲፊክ ሥራውን በኃላፊነት ወስዶ እየሰራ መሆኑን ገልጸዋል ።

የውሳኔ ሰጭ አካላትና ተተኪ ታዳጊዎች ስለ ስፔስ ሳይንስ በአግባቡ እንዲረዱ ለማድረግ ሰፊ የሆነ የአቅም ግንባታ ሥራ ተሰርቷል ያሉት ዶክተሩ፤ ኢትዮጵያ በሳይንሱ ዘርፍ ጠንካራ የሆነ ማሕበረሰብ እንዲኖራት በተለያዩ ተቋማት የስፔስ ሳይንስ ፕሮግራሞች እንዲጀመሩ ጥረቶች ተደርገዋል ። የተወሰኑ ዩኒቨርሲቲዎች በመጀመሪያና በሁለተኛ ዲግሪ ትምህርቶችን መስጠት ጀምረዋል ። የእንጦጦ ኦብዘርቫቶሪ ማዕከል እንዲከፈት በማድረግ ጠንካራ ሥራን ተሰርቷል፤ ለመጀመሪያ ጊዜም የኢትዮጵያ የሳተላይት ፕሮግራም አስጀምሯል ብለዋል ።

# የጉምሩክ ኮሚሽኑ በዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ላይ ለሚገኙ ነዋሪዎች ከ14 ሚሊዮን ብር በላይ ድጋፍ አደረገ

አዲስ አበባ ፡- የጉምሩክ ኮሚሽን የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር እያካሄደ ላለው የዝቅተኛ ማህበረሰብ የቤት እድሳት ፕሮግራም ሊሆን የሚችል 26ሺህ 890 የቤት ክዳን ቆርቆሮና ከ3ሺ500 በላይ ኩንታል ሲሚንቶ በድምሩ ከ14 ነጥብ 5 ሚሊዮን ብር በላይ የሚገመት ድጋፍ አደረገ ።ድጋፉን በትላንትናው እለት የጉምሩክ ኮሚሽን ኮሚሽነር አቶ ደበሌ ቃበቶ ለከንቲባ ወይዘሮ አዳነች አቤቤ አስረክበዋል ።

በርክክብ ሥነሥርዓቱ ላይ ንግግር ያደረጉት ከንቲባ ወይዘሮ አዳነች ፕሮጀክቶቻችን ባቀድነው መሰረት እንዳይሄድ ህገወጦች ግብዓቶችን መያዛቸው ለሥራ እንቅፋት መሆኑን ተናግረዋል ።

ጉምሩክ ኮሚሽን ከህገወጦች ጋር አንገት ላንገት ተናንቆ፤ የተገኙትን ግብዓቶች ዛሬ ለህዝብ ጥቅም እንዲውል በማድረጉ ሊመሰገን እንደሚገባ አንስተዋል ። እንደዚህ የሚሰሩ የሚያስተባብሩ ብዙ ተቋማት ብዙ መሪዎችና ብዙ ሰራተኞች ያስፈልጉናል ያሉት ከንቲባዋ ሌሎች የፌዴራል ተቋማትም ከጉምሩክ ኮሚሽን ትምህርት መውሰድ አለባቸው ሲሉም አሳስበዋል ።

የጉምሩክ ኮሚሽን ኮሚሽነር አቶ ደበሌ ቃበታ በበኩላቸው ኮሚሽኑ እነዚህን ንብረቶች ከተለያዩ የሃገሪቱ አካባቢዎች ራቅ ካሉ የጉምሩክ ጣቢያዎችና የኮንትሮባንድ ቁጥጥር ቦታዎች በማሰባሰብ ማምጣት መቻላቸውን ገልፀው አስተዳደሩ በተለይም ከንቲባ አዳነች አቤቤ ቀን ከሌሊት በመስራት የህዝቡን ሕይወት ለመቀየር የሚያደርጉትን ጥረት በእጅጉ እንደሚያደንቁና የአስተዳደሩ ጥረትን ለመደገፍ ኮሚሽኑ ምንጊዜም ከአስተዳደሩና ከህዝቡ ጎን እንደሚቆሙና ድጋፋቸውን አጠናክረው እንደሚቀጥሉ ገልፀዋል ።

አቶ ዘሙኑ ደሳለኝ የቂርቆስ ክ/ከተማ ዋና ሥራ አስፈፃሚ እንዲሁ በሰጡት አስተያየት የፌዴራል ጉምሩክ ኮሚሽን መቀመጫው በክ/ከተማው ውስጥ በመሆኑ በቤት እድሳት እየተሳተፈ መሆኑን ገልፀው ህግን በማስከበር ከሚያገኙትም ውጤት የዜጎችን ኑሮ ለማሻሻል የሚያደርጉትን ጥረት የሚያስመሰግን መሆኑን ገልፀዋል ።

የጉምሩክ ኮሚሽን ባለፈው ሳምንት በተመሳሳይ 15 ሚሊዮን ብር የሚገመት ድጋፍ ማድረጉ የሚታወስ ነው ።

# ህብረተሰቡ በክሪፕቶ...

**ከ1ኛው ገጽ የዞረ**

አንድ የኮምፒዩተር ባለሙያ ወይም ድርጅት አንድ የክሪፕቶ ከረንሲ መገበያያ ቢፈጥርና ያ ገንዘብ ገበያው ቢገባ ኮዶችን ብቻ እያከፋፈለ በቅጽበት የዓለም ሃብታም የሚሆንበትና በአንድ ጀንበር የዓለምን ኢኮኖሚ የሚቆጣጠርበት ዕድሉ ሰፊ መሆኑን ረዳት ፕሮፌሰሩ ጠቁመዋል።

በተጨማሪ አጨቃጫቂ የሚሆነው ጉዳይ ክሪፕቶ ከረንሲን ማን እንደሚያሰራጨውና ባለቤቱ ማን እንደሆነ እንኳን አይለይም። በመሆኑም ካለው ስጋት አኳያ አንድ ቀን አገራት በሙሉ ምናባዊውን ገንዘብ ሊያቋርጡበት የሚችሉበት ዕድል እንዳለ ማሰብ ያስፈልጋል ሲሉ ምክረ ሃሳባቸውን አስቀምጠዋል።

አንድ ድርጅት ቢት ኮይን የተባለ ወይም ሌላ ስም ሰጥቶ ይህንን ምናባዊ ገንዘብ አስተዋውቄያለሁ ስላለ ብቻ ሰዎች ገንዘባቸውንም ንብረታቸውንም ሰጥተው ያንን ምናባዊ ገንዘብ ለማግኘት የሚሯሯጡ ከሆነ እጃቸው ላይ የሚቀራቸው ሃብት እንደማይኖር ሊያስቡ ይገባል ሲሉ አሳስበዋል።

ስለዚህ ይህን ምናባዊ የኮምፒዩተር ኮዶች የገዙ ሰዎች በተቻለ መጠን እራሳቸውን ከአደጋ ለመጠበቅ የያዙትን ምናባዊ ገንዘብ ወደህጋዊ ንብረት አሊያም በባንክ መገበያያነት እያገለገሉ ወደሚገኙ ገንዘቦች ቢቀይሩ ሃብታቸውን በቅጽበት ከማጣት ስጋት መላቀቅ ይችላሉ ብለዋል።

እንደአገርም ይህንን ምናባዊ ገንዘብ ተግባራዊ ለማድረግ ሰፊ ዝግጅት ይጠይቃል ያሉት መምህሩ፤ ብዙ ሕጎችም መውጣት አለባቸው። በተጨማሪም በአገራት መካከል ጭምር ድርድሮችና ማካሄድና ምናባዊው ገንዘብ ላይ ስምምነቶች ማካሄድ ይኖርባቸዋል። ያን ጊዜ በሙሉ ልብ ይህንን ክሪፕቶ ከረንሲ መጠቀም እንደሚቻል ዕምነታቸው መሆኑን ገልጸዋል።

ዲጂታል መገበያያ ገንዘብ አለያም ምናባዊ ንብረትን ለግብይት መጠቀም በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ዕውቅና ያልተሰጠው ድርጊት በመሆኑ ህብረተሰቡ ከእንደዚህ አይነት ሕገ-ወጥ ተግባር እራሱን እንዲጠብቅ ባንኩ ማሳሰቡ የሚታወስ ነው።

የእንግሊዙ ኪንግስተን ዩኒቨርሲቲ ባካሄደው ጥናት መሰረት፤ በዓለም አቀፍ ደረጃ በኮቪድ ወረርሽኝ ምክንያት የኢኮኖሚ ቀውስ ሲፈጠር የክሪፕቶ ከረንሲ የመገበያያ አቅም ቀንሶ ታይቷል። ይህም ለክሪፕቶ ከረንሲ የሚወጣ ሃብት በተለይ በሪል እስቴት፣ በወርቅና ነዳጅ ዘይት ላይ ከሚደረጉ ኢንቨስትመንቶች አንጻር በዓለምአቀፍ ደረጃ ከፍተኛ ስጋት ያለው ግብይት መሆኑን አመላክቷል።

# የለገሐር አንድ ህንጻ...

**ከ1ኛው ገጽ የዞረ**

መሆኑን የገለጹት ኮንትራቱ ከፊኒሺንግ ጋር የተያያዙ ጊዜያትን ሳይጨምር 670 ቀናትን የያዘ መሆኑን ጠቁመዋል።

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ግን በሀገር አቀፍ ደረጃ የገጠመው የሲሚንቶ እጥረት ከምንጊዜውም በላይ ችግር ሆኗል ያሉት የስትራክቸር እና ብሎኬት ሥራ በዋነኛነት ሲሚንቶ የሚያስፈልገው በመሆኑ የሲሚንቶ ድጋፍ ያስፈልገናል ብለዋል።

ለገሐር ስካይ ጋርደን አንድ የመጀመሪያው በለገሐር የሚገነባው ህንጻ ሲሆን ባለ1 ፣ ባለ2፣ ባለ 3 እና ባለ 4 መኝታ የመኖሪያ አፓርትመንቶችን ያካተተ ነው ። 4000 ሜትር ስኩየር ላይ እየተሰራ ያለው ለገሐር አንድ የሕንጻ ፕሮጀክት በጠቅላላው 92 አፓርትመንቶችን፣ ከ260 በላይ ፓርኪንጎችን የሚያካትት መሆኑን ገልጸዋል።

የግንባታ ሂደት 10ኛ ፎቅ የደረሰ ሲሆን፣ የብሎኬት እና የልስን ሥራ እስከ 8ኛ ፎቅ፣ የውስጥ ልስን 5ኛ ፎቅ መድረሱን ለማየት ተችሏል።

የላጋር አንድ ህንጻ ሥራ የማማከር እና ቁጥጥር ሥራ የሚሰራው የዚያስ ዲዛይን ኢንተርናሽናል ምክትል ማናጀር አቶ ምስክር ዘበነ በበኩላቸው መሰረታዊ ችግር ያሉት የሲሚንቶ እጥረት ከተስተካከለ የግንባታ ሂደቱን በሚፈለገው ፍጥነት ለማስኬድ ያስችላል ብለዋል።

በየጊዜው የተለያየ ቢሆንም አሁን ላይ በህንጻ ግንባታው ምክንያት ከ700 በላይ ለሚሆኑ ሰራተኞች የሥራ እድል ተፈጥሯል ብለዋል።

የትላልቅ ፕሮጀክቶች ግንባታ ፅሕፈት ቤት የኮሙኒኬሽን ዳይሬክተር አቶ አዲስ አረጋይ በበኩላቸው እንደገለጹት፣ የላጋር ኤግል ሂልስ በአጋርነት እና በሽርክና ከሚሰሩት ሶስት ሜጋ ፕሮጀክቶች መካከል አንዱ ነው።

የላጋር ኢግል ሂልስ፣ አዲስ ቱሞሮ፣ አዲስ አፍሪካ ዓለም አቀፍ ኮንቬንሽን እና ኤግዚቢሽን ማዕከል ፕሮጀክቶች የከተማ አስተዳደሩ በሜጋ ፕሮጀክቶች አማካይነት በአጋርነትና በሽርክና የሚሰራቸው ናቸው።

ከእነዚህም መካከል ኢግል ሂልስ ፕሮጀክት ቀድሞ ወደ ሥራ የገባ ሲሆን ግንባታውም በ36 ሄክታር ላይ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር እና በኢግል ሂልስ በሽርክና የሚለማ ሪል ስቴት ነው።

የከተማዋን ገጽታ በአዎንታዊ መልኩ መቀየር የሚችል፣ ዜጎችን የቤት ባለቤት በማድረግ የኢኮኖሚ ተጠቃሚነት የሚያረጋግጥ፤ የከተማዋን ቱሪዝም በማስፋት ከፍተኛ ገቢ የሚያስገኝ ፕሮጀክት እንደሆነም ጠቁመዋል።

የከተማ አስተዳደሩ ከሰሞኑ ባደረጋቸው የከተማዋ ሜጋ ፕሮጀክቶች ጉብኝት አጠቃላይ በትላልቅ ግንባታ ፕሮጀክቶች ላይ ከውጭ ምንዛሪ ጋር በተያያዘ እና ሌሎች ችግሮችን የሚያጋጥሙ ተግዳሮቶችን ለመቅረፍ ባለ አቅም ለመደገፍ ዝግጁነቱን የገለጸ መሆኑንም ጠቁመዋል።

የከተማ አስተዳደሩ መሬት ከማቅረብ ባለፈ በሽርክና ከሚሰራባቸው አንዱ ሥራም ለፕሮጀክቶቹ ግንባታ እንቅፋት የሚሆኑ ችግሮችን መቅረፍ በመሆኑ የግንባታ ቦታዎችን ነጻ አድርጎ ዝግጁ ማድረግ፣ እንዲሁም በሚፈለገው ጥራት እየተካሄዱ መሆኑን መከታተል እና ድጋፍ ማድረግ ተጠናክረው እንደሚቀጥሉም ጠቁመዋል።ለፕሮጀክቱ መጓተት እንቅፋት በሆኑት የሲሚንቶ እጥረትና የወሰን ማስከበር ችግሮች እንደሚቀረፉ ተናግረዋል ።

# ኮርፖሬሽኑ ያስገነባቸው...

**ከ1ኛው ገጽ የዞረ**

መልዕክት የሚታየውን የቤት እጥረት ችግር ለመቅረፍ ተቋሙ ሁሉን አቀፍ ሪፎርም በማዘጋጀት ሲተገብር የቆየና ላለፉት 28 ዓመታት የቆመውን የቤትልማት ፕሮጀክት ዳግም በማስጀመር ባለፉት አራት ዓመታት ውስጥ አስር የሚደርሱ ፕሮጀክቶችን አስጀምሮ በማስገንባት በታቀደላቸው ጊዜ በጥራትና ምቹ በሆነ መልኩ እየገነባ እንደሚገኝ አስታውቀዋል ።

በ18 ወራት ውስጥ በሶስት ቢሊዮን ብር የተገነባው የገርጂ ዘመናዊ የመኖሪያ መንደር የአገራችን በለሙያዎች ቴክኖሎጂንና እውቀትን ቀስመው በፍጥነት ተግባራዊ የማድረግ ብቃት ያሳዩበት የግንባታ ፕሮጀክት ነው ብለዋል።

በዓይነቱ ልዩ የሆነው የገርጂ ዘመናዊ መኖሪያ መንደር ፕሮጀክት አሥራ ስድስት ብሎኮች ባለ አስር ወለል ያላቸው ዱፕሌክስ እስካይ ቪላና አፓርትመንት የሆኑ በአልሙኒየም ፎርምዎርክ ቴክኖሎጂ የተገነቡ እንደሆነ የገለፁት ዋና ሥራ አስፈፃሚው፣ ይህ ቴክኖሎጂ ጊዜንና ወጪን በመቆጠብ ወደር ያልተገኘለት መሆኑን ተናግረዋል ።

የጠቅላይ ሚኒስትር ፅ/ቤት ኃላፊና የኮርፖሬሽኑ ሥራ አመራር ቦርድ ሊቀመንበር አቶ ተፈሪ ፍቅሬ በበኩላቸው የቤት አቅርቦት ችግር ለመፍታት የፌዴራል ቤቶች ኮርፖሬሽን የተያዘውን ሀገራዊ የቤት ልማት ፕሮጀክት አላማ ለማሳካት በሚደረገው ጥረት የራሱን አሻራ እያስቀመጠ የመጣ ተቋም መሆኑን ገልፀዋል።

በግንባታ ኢንዱስትሪው ባልተለመደ መልኩ በአሥራ ስምንት ወራት ውስጥ ግዙፍ ዘመናዊ የመኖሪያ መንደር ገንብቶ ማጠናቀቅ መቻሉ፣ ተቋሙ ፕሮጀክቶችን የመጀመር ብቻ ሳይሆን ተገቢውን አመራርና ክትትል በማድረግ በወቅቱና በጥራት እንዲጠናቀቅ ማድረግ መቻሉን ያሳያል ብለዋል ።

የገርጂ ዘመናዊ መኖሪያ መንደር በሦስት ሄክታር ይዞታ ላይ የተገነባ፣ 510 ቤቶችን የያዙ 16 ህንፃዎች እያንዳንዳቸው ከ150 ካሬ ሜትር እስከ 500 ካሬ ሜትር ስፋት ያላቸው ቤቶች ናቸው ።

የቀበና ዘመናዊ የቤት ግንባታ ፕሮጀክት ደግሞ ባለ 2B+G+10 ህንፃ ሲሆን ስፋታቸው እያንዳንዳቸው ከ 70 ካ/ሜትር እስከ 185 ካሬሜትር የሚደርሱ ከባለ 1 እስከ ባለ 4 መኝታ ክፍል ያላቸው ዘመናዊ መኖሪያ ቤቶችን ያካትታል።

በተጨማሪም ለኑሮ አስፈላጊ የሆነ የደህንነት መጠበቂያ የተገጠመለት፣ ከ800 በላይ መኪና ማቆሚያ ያለው፣ የጋራ መጠቀሚያ አዳራሽ፣ ስፖርት ማዘውተሪያ ጂምናዚየም፣ ካፌና ሬስቶራንት፣ የአረንጓዴ ቦታና መናፈሻ፣ አምፊ ቴአትር፣ ዘመናዊ የቆሻሻ ማስወገጃ ፣ የቅርጫትና መረብ ኳስ ሜዳዎች፣ የልጆች መጫወቻ ቦታና የመዋኛ ገንዳ እንዲሁም ሌሎች አስፈላጊ ነገሮች አሟልቶ የያዘ ማራኪ ገጽታ የተላበሰ የመኖሪያ መንደር መሆኑን ከተቋሙ የተገኘው መረጃ ያመለክታል ።

# ርዕሰ አንቀፅ

## የብልጽግና ጉዞውን ለማስቀጠል ከለውጥ ኃይሉ ጎን መቆም ወሳኝ ነው!

ሀገራችን በታሪክ ካጋጠሟት ከፍ ያሉ ፈተናዎች መካከል አሁን ያለንበት ወቅት አንዱ እንደሚሆን ይታመናል። ሀገሪቱ እንደ ሀገር ለመፍረስ ፤ ሕዝቦቿንም ለመበተን በሀገር ውስጥም ሆነ በዓለም አቀፍ ደረጃ የተቀናጁ ሴራዎች በግልጽም በስውርም እየተከናወኑ ነው። ታሪካዊ ጠላቶቻችንም ይህንን አጋጣሚ እንደ መልካም ዕድል በመቁጠር የተቻላቸውን ሁሉ እየተጉ ነው።

ሀገሪቱ ውስጥ ከፍ ባለ ድምጽ እየተሰማ ያለው የብልጽግና /ከዘመናት እንቅልፍ የመንቃት ዜማ ለአንዳንዶች ጆሮ የሚጥም አልሆነም። ከሁሉም በላይ ይህ የመንቃት ዜማ ያስደነገጣቸው ታሪካዊ ጠላቶቻችን ከዜማው በስተጀርባ ያለው ሕዝባዊ ቁርጠኝነት ከሁሉም በላይ አስጨንቋቸዋል።

እነዚህ ታሪካዊ ጠላቶቻችን በሀገር ውስጥ ዓላማቸውን ሊሸከሙ የሚችሉ ባንዳዎችን ከመፈልፈል አንስቶ፣ ሀገሪቱን በዘርና በሃይማኖት በመከፋፈል በሀገሪቱ መቆሚያ የሌለው የእርስ በርስ ግጭቶችንና ሀገራዊ አለመረጋጋቶች በመፍጠር የጀመርነውን የብልጽግና ጎዞ ለማሰናከል ሌት ተቀን እየተጉ ነው።

የተጀመረው ሀገራዊ ልማት እንዳይቀጥል በባንዳዎቻቸው አማካኝነት ለለውጥ ኃይሉ የተለያዩ የቤት ስራዎችንና አጀንዳዎችን በመስጠት፤ ትኩረቱን ከልማቱ ላይ እንዲያነሳ ባላቸው አቅም ሁሉ እየሰሩ ነው። ከፍ ባለ የፕሮፓጋንዳ ዘመቻዎችም የለውጡን ኃይል ስምና ምግባር ለማጠልሸት በስፋት እየተንቀሳቀሱም ነው።

ከዚህ ጎን ለጎንም የብልጽግና ዜማው በተስፋ መቁረጥ ከዚህ በሚመነጭ ቁዘማ መንፈሳቸው በወደቀ ልባቸው ለተሰበረ አፍሪካውያን ተስፋ ፈንጣቂ ከመሆን ባለፈ በሕዝቦቹ ላይ ሊፈጥረው የሚችለው መነቃቃትና መነቃቃቱ የሚወልደው ወደ ራስ የማየት እና ራስን የመሆን ቁጭት ያሳሰባቸው በአህጉሪቱ ሕዝቦች ብልጽግና የሚቆምሩ ኃይሎች የቁማር ካርዳቸውን የተነጠቁ ያህል እንዲሰማቸው አድርጓል።

በቀደመው ዘመን ለአፍሪካውያን ወንድሞቻችን የነጻነት ፋና ወጊ የሆነችው ሀገራችን የጀመረችው የብልጽግና ጉዞ በአህጉሪቱ ሕዝቦች ትከሻ ላይ ተፈናጠው በአህጉሪቱ ሕዝቦች ድህነት ለሚቆምሩ ኃይሎች ይዞት የመጣው የይቻላል መልዕክት አስደንጋጭ ሆኗል። ከማስደንገጥም አልፎ መንፈሱን ለማዳፈን እንደ ሀገር ዘመቻ እንዲከፈትብን አድርጓል ።

ከሁሉም በላይ አሸባሪው ሕወሓት በሥልጣን ዘመኑ ብሔራዊ ተቋማትን ፤ ከብሔራዊ ተቋምነት ይልቅ የፓርቲው የመጨረሻ ምሽግ እንዲሆኑ አድርጎ የመገንባቱ እውነታ፤ ቡድኑ በሕዝባዊ አመጽ ከሥልጣን ከተወገደ ማግስት ጀምሮ ሀገሪቱ በተፈጠረው የተቋማት አደረጃጀት ክፍተት ዋጋ እንድትከፍል አድርጓታል። እውነታውም ለለውጥ ኃይሉ ከፍተኛ ተግዳሮት ሆኖበት ቆይቷል።

በዚህ ሁሉ ፈተናዎችና ተግዳሮቶች እየተፈተነ ያለው የለውጥ ኃይሉ ችግሮቹ ለሚጠይቁት ሕዝባዊ ቁርጠኝነትና ትዕግስት ራሱን በመግራት በአንድ በኩል ታሪካዊ ጠላቶቻችን ፤ የውስጥ ባንዳዎቹና በአህጉሪቱ ሕዝቦች ድህነት የሚቆምሩ ሀይሎች የጥፋትና ሀገር ማፍረስ ተልዕኮ በማምከን በሌላ በኩል ደግሞ የሕዝቡን የለውጥ ፍላጎትና የብልጽግና መሻት እውን ለማድረግ በልበ ሙሉነት እየሰራ ይገኛል።

ከለውጡ ማግስት የነበረውን ቁመና በተለያየ መልኩ በማሳደግ ዛሬ ላይ ከትናንት በተሻለ ለውጡ የሚመራበትን አቅም እየገነባ ነው። ከሁሉም በላይ የጸጥታ፣ የደህንነትና የመከላከያ ኃይሎቹ አስተማማኝ ብሄራዊ ቁመና እንዲላበሱ ከማድረግ አልፎ በጠንካራ መሰረት ላይ እንዲዋቀሩ በዚህም ለሕዝባችን አስተማማኝ ደህንነት አቅም እንዲሆኑ እያደረገ ያለው ተጨባጭ ጥረት እውቅና ሊሰጠው የሚገባ ነው ።

የተቋማቱ ግዳጅ የመፈጸም አቅም ዕለት ተዕለት ሀገራዊ ሰላምና መረጋጋትን በተሻለ መልኩ መፍጠር እያስቻለ ነው፤ በተቋማቱ የቀደመ የአደረጃጀት ክፍተት ለመጠቀም ሲሞክሩ ለነበሩ ኃይሎችም ጠንካራ መልእክት ማስተላለፍ ያስቻለ ነው። ታሪካዊ ጠላቶቻችንም በኛና በኛ በሆነ ጉዳይ ላይ ደጋግመው እንዲያስቡ እያስገደዳቸው ይገኛል።

ከዚህ ተጨባጭ እውነታ በመነሳት መላው ሕዝባችን ከፌዝ ቡክ አልባልታና ከመንደርተኞች በሬ ወለደ ወሬ ወጥቶ ይህን በብዙ እሳት እየተፈተነና በጽናት እየተጓዘ ያለውን የለውጥ ኃይል በመደገፍ እንደ ህዝብ የጀመረው የልማትና የብልጽግና ጉዞ ስኬታማ እንዲሆን በቁርጠኝነት መንቀሳቀስ ይጠበቅበታል።

እንደሀገር እያጋጠሙን ያሉ ችግሮች ወደ ተስፋችን የሚያሻግሩን አቅሞቻችንና ለህልማችን እውን መሆን እያጋጠሙን ያሉ ተፈጥሯዊ ተግዳሮቶች መሆናቸውን መገንዘብ ያስፈልጋል። ችግሮቹን አሸንፈን ለመውጣት የምንከፍለው የትኛውም ዋጋ የሀገርን እና የትውልዶችን እጣ ፈንታ የሚለውጥ ፤ በታሪክና በትውልዶች መካከል ከፍ ያለ ዋጋ የሚያሰጥ እንደሆነም በአግባቡ ማጤን ተገቢ ነው!


# አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስኪያጅ**

ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22

**ዋና አዘጋጅ**

አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**

ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**

ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4240
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**

- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- አልማዝ አያሌው
- እስማኤል አረቦ

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**

ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**

ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**

ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ**

ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


**ነፃ ሃሳብ**

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡ በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

## መገናኛ ብዙሃን ከአሉባልታና ከፈጠራ ወሬ ወጥተው በሃላፊነት መንፈስ ሊንቀሳቀሱ ይገባል!

**ዶክተር ጀኔኑስ**

መገናኛ ብዙሃን ለአንድ አገር ህልውና መሰረት ከሚባሉት የመጀመሪያውን ቦታ ይይዛሉ፡፡ በአሁኑ ወቅት በሀገራችን የገጠሙን ችግሮችን በማራገብም ሆነ መፍትሄ በማፈላለግ የመገናኛ ብዙሃን አውታሮች እና ባለሙያዎች የማይተካ ሚና አላቸው የሚል የፀና ዕምነት አለኝ፡፡

መገናኛ ብዙሃን ሀገርን በመገንባት የሚኖራቸው ሚና በቀላሉ አይታይም፡፡ በዚያው ልክ ሀገርን በማፍረስም ያላቸው አሉታዊ ሚና እጅግ የጎላ ነው፡፡ ምዕራባውያን አንድን ሀገር ማፍረስ ሲፈልጉ የመጀመሪያ ሥራቸው በመገናኛ ብዙሃን ነፃ ሃሳብን ማራመድ በሚል ብሂል ሥም የማጥፋት ዘመቻ ውስጥ መግባት ነው፡፡ ይህን በማድረጋቸውም በርካታ ሀገራትን አፈራርሰዋል፡፡

ለአብነት ኢራቅ፣ ሊቢያ፣ ሶሪያ እና ሌሎች ሀገራትን ለማፈራረስ የመጀመሪያ ሥራቸው የነበረው በሀገራትና በመንግሥታት ላይ የስም ማጥፋት ዘመቻ ውስጥ መግባት ነበር፡፡ ለዚህ ደግሞ ቢቢሲ፣ አልጀዚራ፣ ሲ.ኤን.ኤን እና ሌሎች መሰል ሚዲያዎች የሚሰሩት ሥራዎችና ሲሰሩ የቆዩትን ተግባራት ማስታወስና መመልከት በቂ ነው፡፡

የመን የምትባለው ሀገር መንግሥት አልባ የሆነችው በጦርነት ብቻ ሳይሆን የምዕራባውያን መገናኛ ብዙሃን ሌት ተቀን በከፈቱት የፕሮፓጋንዳ እና የሚዲያ ዘመቻ ነው፡፡

ሶማሊያ ጠዋትና ማታ የደም አብዓላ የሚያጥለቀልቃት ራሳቸው በፈጠሩት ችግር ሳይሆን፤ የምዕራባውያን ሚዲያ ሳይታክቱ በዘሩት የጎሳ ልዩነትና የጥላቻ ዘመቻ ነው፡፡ በዚህም ሞቃዲሾ በየቀኑ በአሸባሪዎች እየተናጠች ነው፡፡ ይህም ብቻ አይደለም ምዕራባውያን ባቀጣጠሉት የውሸት ፕሮፓጋንዳ በሩዋንዳ የዘር ፍጅት እንዲከሰት ሆኗል፡፡ ይህ ሁሉ ሲሆን የምዕራባውያን ሚዲያ የጥፋት ቡራኬውን ይጀምሩና፤ መንግሥታቶቻቸው ደግሞ በሠላም ማስከበርና ሌሎች ሰበቦች ወደሚፈልጉት ሀገር ዘው ብለው ይገባሉ፡፡

እነዚህ ፈተናዎች ባለፉት ሶስት ዓመታት ኢትዮጵያ ላይም በተመሳሳይ መልኩ ፤ከዛም በከፋ ሁኔታ ተጠናክሮ መቀጠሉ ይታወሳል፡፡ አንዳንድ መገናኛ ብዙሃን አውታሮች በፈጠሩት እና እየፈጠሩት ባለው ችግር ሀገር ስትታመስ እየተመለከትንም ነው፡፡ በተለይም ደግሞ በዘውጌ አስተሳሰብ የተፈጠሩና እሳቤያቸው ከኢትዮጵያ ሉዓላዊነት ጋር የተጋጨ የመገናኛ ብዙሃን እየተበራከቱ መምጣታቸው ችግሩን አግዝፎታል፡፡ በዚህም ሀገሪቱ ያልተገባ ዋጋ እንድትከፍል እያደረጋት ይገኛል።

የመገናኛ ብዙሃን በአግባቡ እና በሃላፊነት ካልተያዙ ከፍ ያለ ችግር ምንጭ ስለመሆናቸው የተለያዩ ጥናቶች ያመለክታሉ፡፡ በተለይ ደግሞ የዲጂታል ሚዲያው ማደግ ችግሩን በእጅጉ አሳሳቢ አድርጎታል፡፡ ከምንም በላይ በምጣኔ ሀብት ያላደጉ ሀገራት ፈተናው ይፀናባቸዋል፡፡ ቲውተር፣ ማህበራዊ ሚዲያ (ፌስ ቡክ)፣ ኤሜይል እና ሌሎች የመረጃ መለዋወጫ መንገዶች በአንድ ጎኑ መልካም ቢሆኑም ታዳጊ ሀገራትን ግን ክፉኛ እየተፈታተኗቸው ይገኛሉ፡፡

ችግሩ ለታዳጊ ሀገራት መዘጋትና መክፈት በማይችሉት አሊያም ቁልፉ በሌላ እጅ ያለ ቤት ሆኖባቸዋል፡፡ በዚህም የተነሳ በርካቶች ሃሳብን በነፃነት የሚገልጹባቸው ሳይሆን አመፅ ፤ የተበረዙና የተመረዙ መረጃዎችን ተሸካሚ አደገኛ የዘመኑ የጦር መሳሪያ ሆነዋል፡፡ መንግሥታትን በአየር ላይ እስከ መሸምና መሻር የዘለቀ ድፍረትም እየተላበሱ መጥተዋል።

ይህ ዓለም አቀፍ እውነታ የሀገራችንንም የጋዜጠኛነት ሙያ ሆነ የመገናኛ ብዙሃን ነጻነት መፈታተን ከጀመረ ዋል አደር ብሏል። ሀገሪቱ እያጋጠማት ባለው ፖለቲካዊ ፣ ኢኮኖሚያዊና ማሕበራዊ ችግር በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ እየሆነም ይገኛል። በሽርፍራፊ ሳንቲሞች በመደለል የሀገርን ጥቅም አሳልፎ ከመስጠት ጀምሮ ግለሰቦች መፍጠር ለሚፈልጉት ተራ ጀብድ መሳሪያ በመሆን ላይም ነው።

እስካሁን ባለው ዓለም አቀፍ ተሞክሮ ሀገር አልባ ሕዝብና መንግሥት እየተፈጠረ ያለው ከጦርነት በፊት ሆነ በጦርነት ወቅት በሚሰራጩ መርዘኛ መረጃዎች ነው፡፡ መረጃዎቹ የሚፈጥሩት የተዛባ አስተሳሰብና ከዚህ የሚቀዳው ለጥፋት ዝግጁ የመሆን መነቃቃት ነው ወደ ዋናው ግጭት (ጦርነት) የሚወስደው፡፡

ከዚህ አንጻር በሀገራችን እንደ አሸን እየፈሉ የመጡ የማህበራዊ ሚዲያ ጀግኖች (ፌስ ቡከሮች) እና ዩቱዩበሮች ላይ ትኩረት ሰጥቶ መስራት ያስፈልጋል። ሃሳብን በነጻነት የመግለጽ መብት በሚል እየሄዱበት ካለው መረን የወጣ መንገድ የሚመለሱበትን አሰራር መፍጠር ያስፈልጋል። ይህን ማድረግ ሳይቻል ለሚፈጠረው ጥፋት ከሁሉም በላይ የመንግሥት ተጠያቂነት ከፍ ያለ ይሆናል።

በየትኛውም መልኩ የመንግሥት ሆደ ሰፊነት ሀገረ መንግሥቱንና ሕዝብን አደጋ ውስጥ ሊከት የሚችል መሆን የለበትም። የመንግሥትንም መንግሥትነት ጥያቄ ውስጥ የሚያስገባ መሆን የለበትም ፤ የተሳሳተን እንዳይሳሳት ማስተማር ሲሳሳት መገሰጽና ማረም እምቢ ሲል በተገቢው የሕግ አግባብ መቅጣትና ችግሮች ሳያድጉና ባህል ሳይሆኑ ማስቆም የአንድ ጤነኛ መንግሥት ባህሪ ነው።

የሀገሪቱ የመገናኛ ብዙሃን አዋጅ 790/ 2008 በመግቢያው እንዲህ ይላል «በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት እንዲሁም ኢትዮጵያ በተቀበለቻቸው ዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብት ሥምምነቶች የተረጋገጠውን ሃሳብን በነፃነት የመግለፅ መብትና የመገናኛ ብዙሃን ነፃነትን በተሟላ መልኩ ተግባራዊ ለማድረግ ሕግ ማውጣት አስፈላጊ ሆኗል....”፡፡

“...ሃሳብን በነፃነት የመግለፅና የመገናኛ ብዙሃን መብቶች በሕገ መንግሥቱ የተረጋገጡ ሰብዓዊ መብቶችንና ነፃነቶችን ለማረጋገጥ ያላቸውን ፋይዳ በመገንዘብ እና በሀገራችን ዴሞክራሲያዊ ሥርዓትን በመገንባት የሚደረገው ጥረት ስኬታማ እንዲሆን መገናኛ ብዙሃን የሚጫወቱትን የማይተካ ሚና በመረዳት...» እያለ አዋጁን ማውጣት አስፈላጊ እንደሆነ ያብራራል፡፡

ከዚህ መረዳት የሚቻለው በኢትዮጵያ ውስጥ መገናኛ ብዙሃን ሚናቸው ሀገርን በመገንባት፣ ዴሞክራሲን በማስረጽና በማበልጸግ ብሎም ከዘመኑ ጋር የተስማማ ማሕበረሰብ ለመፍጠር በሚደረገው ጥረት ላይ ሚናቸው እጁን የጎላ መሆኑን ነው፡፡ ይህ ማለት የዴሞክራሲ ሥርዓት ግንባታን ለማሳደግ መገናኛ ብዙሃን የተሰጣቸውን ትልቅ ኃላፊነት እንደሆነ የሚያሳስብም ጭምር ነው፡፡

ይሁንና ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የመገናኛ ብዙሃን አውታሮች በተለይም ደግሞ ዩቱዩበሮች የኢትዮጵያን ህልውና ጭምር የሚፈታተኑ መረጃዎች በማሰራጨት መጠመዳቸውን የፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽን አስታውቋል፤ የተወሰኑትን ደግሞ በሕግ አግባብ እንዲጠየቁ ለማድረግ በሕግ ሂደት ላይ መሆናቸው አብራርቷል፡፡ ይህ መሆን ያለበትና የሚጠበቅም ነው፡፡

ሀገሪቱ የመገናኛ ብዙሃንን ነፃነት ለመጠበቅ ብሎም ሕግን አክብረው እንዲሰሩ ለማድረግ ሲባል በአዋጅ ጭምር የተደገፈ መብትና ግዴታን በግልጽ ማስፈሯን አቅሎ ማየት አይገባም፡፡ የትኛውም የመገናኛ ብዙሃን በሀገር ሉዓላዊነት እና ጥቅም ላይ የመደራደር የሞራል ብቃት ሆነ ሙያዊ ተጠየቅ የለበትም፡፡

በተለይም አሁን ባለንበት ሀገራዊ የፈተና ወቅት መገናኛ ብዙሃን ሀገርና ሕዝብ የማረጋጋት ከፍተኛ ሃላፊነት አለባቸው። ሽርፍራፊ ሳንቲም ለመቃረም ከአሉባልታና ከፈጠራ ወሬ ወጥተው ተጨባች በሆኑ ጉዳዮች ላይ ሚዛናቸውን የጠበቁ ፣ ለሙያው ሥነምግባር የተገዙ ዘገባዎችን ማሰራጨት፤ ለዚህም እራሳቸውንም ማዘጋጀት ይጠበቅባቸዋል።

ስፖርት እና መዝናኛ

# ፋሽን

## የብርዳማው ወቅት ፋሽን

**ተገኝ ብሩ**

"ኡፉ! ሙቀቱ እንዴት ይጨንቃል..." ብለን ከላይ የለበስነው ያስወለቀን ሙቀት፤ በጊዜ ዑደት ቦታውን ለቆ ቆዳን የሚያኮማትር ቅዝቃዜ ይሰማን ጀምሯል። ይሄኔ ቀድመን አውልቀነው የነበረ ልብስ ብንደርብ እንኳን አይበቃንም። ተጨማሪ ከቁምሳጥናችን ፈልገን አልያም ከሌለን ገዝተን እንደርባለን። እንዲህ ሰማይ ሲያስገመግም መሬቱ ርሶ አየሩ ሲቀዘቅዝ ሰውነታችን ሙቀት ይፈልጋል።

በዚህ ወቅት ደረብረብ አድርጎ መውጣት በምቾት መንፈላሰስ ያምረናል። ፋሽን ተከታዮችና ዘመነኞች ሙቀትን ሲፈልጉ ከምቾት ባሻገር የሚያስቡት ጉዳይ አለ። ለእነዚህ የልብሱ ያማረ ዲዛይን፣ ቀለምና ወቅታዊነት ዋንኛ መለኪያዎች ናቸው። ስለዚህም ክረምት ላይ የሚለበስ ፋሽን ለአየር ጠባዩ የሚስማማ ከመሆኑ ባሻገር ተለብሶም የሚያዘንጥ ወይም ሲጫሙት የሚያሳምር መሆን ይጠበቅበታል።

የክረምት ወራት መጀመሪያው የሆነው ሰኔ ይዞት የመጣውን ቅዝቃዜ ለወራት የሚዘልቅ ነውና ቅዝቃዜው እንዴት እንለፈው ማለታችን አይቀርም። በዛሬው የፋሽን ገፃችን ለክረምት የቀረቡ አልባሳት ላይ ትኩረት አድርገን፤ በክረምቱ ወቅት ሙቅትም የሚያላብሱን አልባሳት ምን አይነቶች እንደሆኑና የገበያ ሁኔታ ለመመልከት ወደድን።

ወፈርፈር ያለ ልብስና ከቁርጭምጪሚት ከፍ ያለው የእግር ክፍል የሚሸፍን ጫማ በክረምት ወቅት ፋሽን ከፍ ብሎም ከብርድ መከላከያ ጋሻ ነው። ይህ ደግሞ የመስኩ ባለሙያዎች በደንብ ያውቁታል። ለዚያ ነው፤ በከተማችን ላይ የሚገኙ የተዘጋጁ አልባሳት መሸጫ ሱቆች ወቅቱን ያማከሉ አልባሳት በየመደርደሪያና አልባሳት ማሳያዎቻቸው ላይ የሚያበረክቱት። እኛም ሰውነታችን በብርድ እንዳይጎዳ፤ አካላችን በቅዝቃዜ እንዳይረታ የሰውነታችን ሙቀት የሚጠብቁ አልባሳት መፈለጋችን አይቀርምና ወደ ሱቆቹ ጎራ እንላለን።

ሰኔ መግባቱን ተከትሎ የሰዎች አለባበስ ተቀይሯል። በፊት የነበረው ቀለል ያለ አለባባስ ሙቀት ወደሚሰጡ ሹራቦችና ካፖርቶች ተለውጧል። በከተማዋ የተለያዩ ዋና ዋና ጎዳናዎች ላይ የበዙት የተዘጋጀ ልብስ መሸጫ ሱቆች በክረምት አልባሳት ይሞላሉ።

በጋውን በተለያዩ አልባሳት ከፊት አሰልፈው ለተጠቃሚ ሲያቀርቡ የቆዩት የተዘጋጁ ልብሶች መሸጫ ሱቆች በአሁኑ ወቅት የሚፈለጉት የክረም አልባሳት መሆናቸው አሳምረው ያውቁታልና የልብስ መስቀያቸውን በክረምት አልባሳት ሞልተውታል። በሱቆቹ ወቅቱን ያገናዘበ የክረምት ፋሽን አልባሳት በየበራቸው በልብስ ማሳያ አሻንጎሊቶች ተወድረው ለተመልካች አጓጊ ተደርገው ይቀርባሉ።

ዛሬ ላይ የቴክኖሎጂ መመንጠቅ በፋሽኑ ዓለም የፈጠረው ትልቅ ዕድል አለ። በተለያየ ጥናትና ምርምሮች በመታገዝ አልባሳት ለሰዎች የተለየ ውበት እዲያላብሱና ጤንነትን የሚጠብቁበት ማድረግ ተችሏል። ሰዎች በሚፈልጉት መልኩ ላሻቸው ግልጋሎት ይጠቀሙበት ዘንድ አልባሳት በተለያየ ግብዓት ተሰርተው ለገበያ ቀርበዋል።

በእኛ አገር አይለመዱ እንጂ ባደጉትና እጅጉን በዘመኑት አገራት ክረምት ላይ ሙቀትን የሚሰጡና በሚፈለገው መልኩ የሙቀት መጠንን ለመቆጣጠር የሚያስችሉ ልብሶች አሉ። እነዚህ አልባሳት በፈለጉት መልክ ሙቀትን ከፍና ዝቅ ባለ መልኩ እንዲሰጡ ተደርገው የተሰሩ የኤሌክትሪክ ሥርዓት የተገጠመላቸው ዘመናዊ አልባሳት ናቸው።

እኛም አገር ወቅትን መሰረት አድርገው የሚለበሱ አልባሳት ተጠቃሚዎች ይመርጡዋቸው ዘንድ ለዲዛይናቸውም ልዩ ትኩረት ተሰጥቶ ይዘጋጃሉ። ለክረምት ወቅት የሚዘጋጁ አልባሳት ሙቀት ሊሰጡ ከሚችሉ ግብዓችም ይዘጋጃሉ። የክረምት አልባሳት የሰውነት ሙቀትን ከመጠበቅ ባለፈ እንደ ፋሽን ተወስደው ውበትን የሚያጎናፅፉ አምረንና ሽክ ብለን እድንታይ የሚያደርጉም ናቸው።

በመዲናችን በፋሽን አልባሳት በስፋት ከሚታወቁት ሰፈሮች አንዱ በሆነው ሜክሲኮ መሀል ተገኝተናል። የክረምት አልባሳት አይነቶች፣ ገበያና ተፈላጊነት ምን ይመስላል? የሚለውን ምላሽ ለማግኘት ቅኝት ስናደርግ ሜክሲኮ ላይ ጎልቶ የሚታየው ደብረ ወርቅ ህንፃ ስር በተርታ ተሰልፈው ያገኘናቸው የተዘጋጁ አልባሳት መደብሮች ጎራ አልን።

ብርቱኳን አየለ በአካባቢው ታዋቂ ከሆነው የፋሽን አልባሳት መሸጫዎች ሱቅ ውስጥ በአንዱ ደንበኞችዋን ስታስተናግድ አገኘኋት። በሱቅዋ ውስጥ የተደረደሩት አልባሳት በአብዛኛው የክረምት እንደሆኑ ገልፃ፤ የፋሽን ኢንዱስትሪው ባህሪ መሆኑንና የደንበኞች ፍላጎትም ያማከለ መሆኑን ትናገራለች።

በክረምት ወቅት እጅግ ተፈላጊ የሆኑ አልባሳት በሴቶችም በወንዶችም ወፈር ያሉና የሰውነት ሙቀት የሚጠብቁ እንዲሁም ዝናብን የሚቋቋሙ ልብሶች መሆናቸውን ትገልፃለች። በዋጋቸውም ቢሆን በበጋ ወቅት ከነበረው ከፍ እንደሚል ገልፃ ተፈላጊነታቸው ሲጨምር ዋጋቸውም ከፍ እንደሚል ትናገራለች።

እጅግ የሚማምሩ የሴቶች ፋሽን አልባሳት መሸጫ ሱቅዋ ውስጥ የተሰቀሉ ልብሶች ወቅቱን ያገናዘቡና በተጠቃዎች በተለይም በዘመንኛ ወጣቶች የሚፈለጉ መሆናቸውን የምትገልጸው ብርቱኳን አልባሳቱ ተፈላጊነታቸው ስለሚጨምር በብዛትና በአይነት በስፋት ለደንበኞችዋ እንደምታቀርብ ትናገራለች።



አሁን ላይ ሰዎች በተለይም ሴቶች ልብስ ሲገዙ ሙቀት ብቻ የሚሰጥን ብለው ሳይሆን ፋሽን መሆኑንና በዲዛይን አዲስ መሆኑም ላይ ትኩረት አድርገው እንደሚገዙም ታስረዳለች። አካባቢው ላይ ባሉ ሱቆች በብዛትን ለገበያ የሚቀርቡት አልባሳት የሰውነት ሙቀት ከመስጠታቸውም ባለፈ ፋሽን የሆኑና በደንበኞች የሚመረጡ በተለያየ ዲዛይን የተዘጋጁ መሆናቸውን ታብራራለች።

ዋጋ በተመለከተ በፊት ከነበረው ሁሉም በሚባል መልኩ የዋጋ ጭማሪ እንዳለው ገልፃ አልባሳቱ እንደተሰሩበት ጥሬ እቃና ተፈላጊነት ዋጋቸው ይለያያል። በሱቅዋ ውስጥ የሚገኙ ቀሚሶች በአማካይ ከ1500 እስከ 4900፣ ጃኬቶች ከ1800 እስከ 3500 ድረስ ዋጋ ተተምኖላቸው ለሽያጭ እንደተዘጋጁ ትገልፃለች።

ተገልጋዮች ወይም ደንበኞች እዚህ ላይ ምን ይላሉ ብለን የሚሉት ለመስማት ወደ ሱቁ አጋጣሚ ለመግዛት የገባቸውን አንዲት ወጣት ተጠግቼ አወራኋት፡ ፡ቤዛዊት አየለ ትባላለች፤ ለክረምት የሚሆን ሹራብ ለመግዛት እንደገባች ነግራኝ፤ ሁሌም ወቅቱን ያገናዘበ አልባበስ እንደሚመቻትና እራስዋንም ከወቅቱ ጋር በአለባበስ ለማስታረቅ እንደሆነ አስረዳችኝ። ገበያውን በተመለከተ "አይቀመስም" በማለት አስተያየትዋን የምትገልጸው ቤዛዊት የአልባሳቱ ዋጋ እጅግ የተጋነነ መሆኑን ትናገራለች።

ከቄራ ታክሲ መጫኛ ፊት ለፊት ባሉት የበዙ የተዘጋጁ ልብሶች መሻጫ ሱቆች ውስጥ የሚገኙ አልባሳት በዋጋ ከሱቅ ሱቅ የሚለያዩ መሆኑን በምልከታዬ ታዝቤያለሁ።

አካባቢው በአማካይ ከ500 እስከ 4500 ድረስ የወንዶችና የሴቶች አልባሳት ሹራቦች፣ ጃኬችና ካፖርች በብዛት ይሸጣሉ። ለዚህ ልዩነት መነሻ የአካባቢው የገበያ ሁኔታና በአካባቢው የሚኖረው ሕብረተሰብ የመግዛት አቅም እንዲሁም የሱቆቹ የኪራይ ዋጋ መብዛትና ማነስ ምክንያት አድርገው የመሸጫ ሱቆቹ ልብሶቹን በተለያየ ዋጋ ያቀርባሉ።

በሱቆቹ ባደረግነው ቅኝት ከሴቶች አልባሳት ይልቅ የወንዶች በዋጋ ከፍ የሚል ወይም የሚወደድ ሲሆን በተጨማሪም የወንዶች አልባሳት ከሴቶች ይልቅ በአብዛኛው የልብስ መሻጫ ሱቆች ውስጥ በርክተው ይገኛሉ። ለወንዶች የሚሆኑ የክረምት ቡትስ ጫማዎች በአማካይ ከ1200 እስከ 3500 ብር የሚጡ ሲሆን ለሴቶች የሚሆኑ ቡትስ ጫማዎች ደግሞ በአማካይ ከ850 እስከ 3500 ድረስ ይሸጣሉ። በእግጥ የአልባሳቱ ዋጋ ከሱቅ ሱቅ የዋጋ ለውጥ እንዳለውም ለመታዘብ ችለናል።

# ማረፊያ/ትዝብት

## ብዛቱ ሳይሆን አጠቃቀሙ ነው ዋናው

**(አቤል ገ/ኪዳን)**

የፌዴራሉ መንግሥት ለቀጣይ ዓመት የያዘውን በጀት መጠን ይፋ አድርጓል። የጠቅላይ ሚኒስትር ጽ/ቤት እንዳስታወቀው ለ2015 በጀት ዓመት ለመደበኛ ወጪ ብር 347.12 ቢሊዮን፣ ለካፒታል ወጪ ብር 218.11 ቢሊዮን እንዲሁም ለክልል መንግሥታት ድጋፍ ብር 209.38 ቢሊዮን እና ለዘላቂ የልማት ግቦች ማስፈጸሚያ ብር 12.0 ቢሊዮን የተያዘ ሲሆን አጠቃላይ የፌዴራል መንግሥት የ2015 በጀት ብር 786.61 ቢሊዮን ይሆናል። ይህ በጀት ከ2014 በጀት ዓመት በጀት ጋር ሲነጻጸር የብር 111.94 ቢሊዮን ወይም የ16.59 በመቶ እድገት አሳይቷል። ቁጥሮቹ ካለፈው ዓመት አንጻር ሲታዩ ጨምረዋል። ነገር ግን አሁን ካለው የዋጋ ግሽበት አንጻር ሲታይ በጀቱ አነስተኛ ነው ማለት ይቻላል። ሀገሪቱ ከሚያስፈልጋት በጀት አንጻር ሲታይ ደግሞ በጣም ጥቂት ነው። በጦርነት የወደመ ብዙ መሰረተ ልማት ፤ ድርቅ ፤ የእቃዎች የዋጋ ንረት ፤ ወረርሽኝ ፤ ዓለም አቀፍ ጫና እና ሌሎች በርካታ ችግሮች በየቦታው መደቀናቸውን ላየ ሰው በጀቱ ብዙም የሚያወላዳ እንዳልሆነ መገንዘብ ይችላል። ለዚህም ይመስላል የፋይናንስ ሚኒስትሮቹ ሰሞኑን በተደጋጋሚ በጥቂት በጀት እቅድን ስለማከናወን በተደጋጋሚ ሲያወሩ የሚደመጠው።

የሆነ ሆኖ ብሩ ጥቂት እንደሆነ መተማመን ይቻላል። ስለዚህ ዋነኛው ጥያቄ ያለውን እንዴት አድርገን እንጠቀም የሚለው ነው። በዚህ ላይ ብዙ ነገር ማለት ይቻላል። ጥቂቶቹን በቅደም ተከተል ማንሳት እንችላለን። የመጀመሪያው ጉዳይ አዋጭ ፕሮጀክቶችን መምረጥ እና የማያዋጡትን ወደ ጎን ማድረግ ነው። በቅርቡ የፕላንና ልማት ሚኒስቴር ሚኒስትር ሃላፊዎች በአንድ ዘገባ ላይ ሲናገሩ እንደሰማነው ቁጥራቸው ቀላል የማይባሉ ፕሮጀክቶች የአዋጭነት ጥናት ተካሂዶባቸው አዋጭ ባለመሆናቸው ተሰርዘዋል ብለዋል። እንዲህ አይነት አሰራር መጠናከር አለበት። በዘፈቀደ የሚሰሩ ፋይዳ ቢስ ፕሮጀክቶች ሀገርን እዳ ውስጥ የሚከትቱ ናቸው።

ከዚህ ቀደም እንደ ሀገር ገብተንባቸው ከነበሩ ችግሮች መሀከል አንዱ እና ዋነኛው ጀምረናቸው የነበሩት ግዙፍ ፕሮጀክቶችን መጨረስ አለመቻላችን ነበር። ከለውጡ በኋላ መንግሥት ከወሰዳቸው እርምጃዎች መሀከል ቀዳሚውም እነዚህን ፕሮጀክቶች ማጠናቀቅ ነበር። በዚህ መልኩ ተበላሽተው የነበሩ ብዙ ፕሮጀክቶች ወደ ስራ ተመልሰዋል። አሁን አዳዲስ ፕሮጀክቶች እየተጀመሩ ነው። እነዚህ ፕሮጀክቶች ሲጀመሩ አንደኛ ጉዳይ ያስፈልጉናል ወይ ብለን መጠየቅ ያለብን ሲሆን ሁለተኛ ደግሞ ልንፈጽማቸው እንችላለን ወይ ብለን ራሳችንን መገምገም አለብን። ምክንያቱም እነዚህ ፕሮጀክቶች የሚከናወኑት በዚሁ ትንሽ ነው ባልነው ዓመታዊ በጀት ላይ ነው። ያለንን ጥቂት አቅም በትክክለኛው ቦታ ላይ አውለን በአግባቡ መጠቀም ካልቻልን ያለችውን ጥቂት ሀብትም አባክነን ለከርሞውም እዳ ተሸክመን ልንቀመጥ እንችላለን።

በሁለተኛ ደረጃ ልንጠነቀቅበት የሚገባ ሙስና ነው። የሙስና ነገር አሁንም መላ ሊገኝለት ያልቻለ መሰረታዊ ሀገራዊ ችግራችን ነው። አሁንም ከፍተኛ የመንግሥት በጀት በሙስና ይወድማል። በሙስና ምክንያት ቀላል የማይባል ገንዘብ አላስፈላጊ ፕሮጀክቶች ላይ ይወጣል ወይም ፕሮጀክቶቹ ከሚያስፈልጋቸው ገንዘብ በላይ እንዲወጣባቸው ይደረጋል። በጥናት ፤ በሥልጠና ፤ በምርምር ፤ በሲምፖዚየም ፤ በምክክር መድረክ ወዘተ ስም ይባክናል። ይህን ማስቆም ካልተቻለ ይቺው ጥቂት በጀት የሙሰኞች ሲሳይ ልትሆን ትችላለች። አሁን ላይ ካለው የኑሮ ውድነት አንጻር ግለሰቦች በሕገወጥ መልኩ ገንዘብ ወደ ማግኘት ሊያመዝኑበት የሚችልበት እድል ሰፊ ነው። ስለዚህም ጠንካራ ቁጥጥር ካልተደረገ ሙስናው አይን ያወጣ የአደባባይ ተግባር ሊሆን ይችላል።

በሶስተኛ ደረጃ ተቋማት የተመደበላቸውን የስራ ማስኬጃ በጀት የሚጠቀሙበትን መንገድ ማስተካከል በጣም አስፈላጊ ነው። የብዙዎቹ ተቋማት ለስራ ማስኬጅ የሚሰጣቸው በጀት ከዓመት ዓመት እየጨመረ ነው። ይህ የሚበረታታ እና የሚያስፈልግ ነው። ነገር ግን ብዙዎቹ ተቋማት በየጊዜው በጀታቸው የመጨመሩን ያህል አገልግሎት አሰጣጣቸው ሲጨምር አይታይም። ይህ ምክንያቱ ብዙ ቢሆንም የብዙዎቹ ተቋማት በጀት ግን የሚያልቀው አገልገሎትን በማሻሻል ላይ እንዳልሆነ እርግጥ ነው። ዓላማ የሌላቸው ስብሰባዎች ፤ የማይተገበሩ ጥናቶች ፤ ስፍር ቁጥር የሌለው አበል ፤ ተደጋጋሚ ድግሶች ወዘተ.. መንግሥትን ለስራ የመደበውን የመስሪያ ቤቱን በጀት ሙጥጥ አድርገው ሲበሉት በተደጋጋሚ ታይቷል። ስራው አንዲት እርምጃ ሳይራመድ የስራ ማስኬጃው በጀት ካለቀ ይህ የብዙ ችግር ምልክት ነውና ይህን ማየት እና ማስተካከል አስፈላጊ ነው።

በመቀጠል ሊታይ የሚገባው ጉዳይ የበጀት አጠቃቀሙን ግምገማ በየጊዜው በቋሚነት ማካሄድ አስፈላጊ ነው። ብዙውን ጊዜ እንደታየው የመንግሥት በጀት አንዴ ከተለቀቀ በኋላ ተመልካች የሌለው ዝርው በጀት ነው። የብዙ ተቋማት የበጀት አጠቃቀም ግምገማ ገለልተኛ በሆነ አካል የማይታይ ሲሆን መንግሥት የመደባቸው ኦዲተሮችም የበጀት ግምገማቸው ውጤት ምን ላይ እንደደረሰ ለማወቅ በጣም አስቸጋሪ ነው። እንደ አሰራር የመንግሥት ተቋማት በጀት በየጊዜው ጥቅም ላይ የሚውሉበት መንገድ መከታተያ ሥርዓቶች ቢኖሩም እነዚህ ሥርዓቶች በሚገባ ጥቅም ላይ ባለመዋላቸው በጀቱ በከፍተኛ ደረጃ መባከኑን ቀጥሏል። ስለዚህም በቀጣዩ ዓመት ያለችንን አነስተኛ በጀት በቅጡ መጠቀም ከፈለግን የተሻለ ጠንካራ የበጀት ክትትል ሥርዓት መፍጠር አስፈላጊ ነው።

በመጨረሻም የበጀት አጠቃቀማችን ሁነኛ ውጤት እንዲያመጣ ከተፈለገ የፖለቲካ አመራሩ ቁርጠኛ መሆን አለበት። ከላይ የተባሉት ሃሳቦችም ሆነ ሌሎች የተሻሉ የበጀት አጠቃቀሞችን ለመፍጠር የፖለቲካ አመራሩ በሕዝባዊነት እና ሀገር ወዳድነት መንፈስ እየተመራ ውሳኔዎችን መወሰን አለበት። የፖለቲካ አመራሩ ሕዝባዊነትን ሲላበስ ለሀገር እና ለሕዝብ የሚጠቅሙ ፕሮጀክቶችን ብቻ ይተገብራል። የፖለቲካ አመራሩ ቁርጠኛ ከሆነ ሙስና አይፈጽምም ፤ ለሙስና እና ለሙሰኞች የሚሆን ትእግስትም የለውም። የፖለቲካ አመራሩ ቁርጠኛ ከሆነ በየተቋሙ የሚመደበው በጀት ምን ላይ እንደዋለ ይከታተላል ፤ ይወስናል። ከሁሉም በላይ የፖለቲካ አመራሩ ቁርጠኛ ከሆነ የበጀት አጠቃቀሙን ሂደት በቋሚነት ይከታተላል። ብክነት ሲኖርም ያርማል ፤ አጥፊዎችንም ይቀጣል። ስለዚህም የፖለቲካ አመራሩ ቁርጠኝነት ወሳኝ ነው። አልያም አሁን እንደሚደረገው በውስጣዊ ግምገማ እና ቦታ በመቀያየር ብቻ የሚያልፍ ከሆነ ይህ አዲሱም በጀት ከዚህ ቀደም እንደነበሩት በጀቶች የሚባክን ይሆናል።

**ፖለቲካ እና ወቅታዊ**

# ነፃ ሃሳብ

# ክረምትን ለበጎነት

**በትረ ሙሴ (መልከ ኢትዮጵ)**

አሲዮ ብለን፣ የመስቀል ወፍና የአደይ አበባ፣ ቀጠሮ እንዳላቸው መስከረም ሲጠባ ስንል ገጥመን፣ በጥሌ ዜማ፣ በዘሪቱ ጌታሁን እንቁጣጣሽ እንኳን መጣሽ፣ በአበቦች መሀል እንምነሽነሽ ብለን ተምነሽንሽንና የአዲስ ዓመት ብስራታችንን መስከረምን ሸኝተን፣ ከገናና ከፋሲካ፣ ከአረፋና ከረመዳን በረከት ተቋድሰን፣ በኑሮ ውድነትና በኮሮና ስጋት ተይዘን፣ በጦርነትና በሞት ስጋት ተከበን አያልፍ የለ 2014 እየተንገዳገደ አስር ወራትን ቆጥረን እንሆ ሰኔ ላይ ከተምን። ጊዜ ሕይወት ነው.. ጊዜ ስኬት ነው። ጊዜ ለራሳችንም ሆነ ለሀገራችን በጎውን እንድናደርግ እድል የሚሰጠን አጋጣሚ ነው።

እኔም በዚህ የጊዜ ምህዋር ላይ ተረማምጄ የክረምት ሁሉ አባት በሆነው ሰኔ ላይ ቆሜ ክረምትን ለበጎነት ስል መጣሁ። ጊዜ ድር ነው.. ጊዜ እኔና እናት የተሸመንበት ማግ ነው። ጊዜ ሕዝብ ለሀገር፣ ሀገር ለትውልድ የምትሰጠው የቅብብሎሽ በትር ነው። በጊዜአችን ውስጥ በጎ ነገር ስናጣ፣ ጊዜአችንን ተጠቅመን ለራሳችንም ሆነ ለሌላው መልካም ነገር ማድረግ ሲያቅተን ያኔ ዘመን የሸመነው ሰውነታችን እያረጀና እየጃጀ እንደ ልብስ እናልቃለን ከዛም ከእድሜ አመሻሽ ላይ ቆመን ‹ወይኔ እንዲህ አድርጌ ቢሆን ኖሮ› ብለን እንቆጫለን።

ሰኔ የክረምት መግቢያ በር ነው። ሰኔ ዝርክርክ ብሎ የሚያዝረከርከን የጿጋና የመከራ ጌጣችን ነው። ወፍራም በመልበስና  የላመ በመብላት አንሸሽውም ምክንያቱም ወፍራም መልበስ የማይችሉና የላመ ለመብላት አቅም የሌላቸው ወገኖች አሉንና ነው። ሰውነት ስለ ሌላው መታመም ነው። ሰውነት በሌሎች ስቃይ መሰቃየት ነው። ክረምት ደግሞ ስለሌላው እንድንታመምና እንድንሰቃይ የሚያደርግ ጥሩ አጋጣሚያችን ነው። ምክንያቱም በክረምት ቤት የሌላቸው፣ በክረምት መሸሸጊያ ያጡ ነፍሶች ብዙ ናቸውና ነው።

ክረምት እንባና ሳቅ ነው። የሞቀ ቤት ያለን እኔና እናተ እንደምንስቅ ሁሉ ክረምት በመጣ ቁጥር የሚያለቅሱ፣ መግቢያ የሚያጡ ነፍሶች ጥቂቶች አይደሉም። ክረምት ለሀገራችን በጎውን እንድንሰራ እድል ከሚሰጡን አጋጣሚዎች ውስጥ አንዱ ነው። እንጿድቅበት ዘንድ ጥሩ አጋጣሚም ይመስለኛል። በእርግጥ ለመጽደቅም ሆነ ለሀገር መልካም  ለመስራት ሁሉም ጊዜአቶች እኩል ቢሆኑም የክረምትን ያክል ሀገር ወገን የሚረዳበት ጊዜ አለ ብዬ አላስብም።

ምክንያቱ ደግሞ ክረምት ሲመጣ ይዟቸው የሚመጣው ብዙ ችግሮች ስላሉ ነው። ከነዚህ ውስጥ ዋና ዋናዎቹ ጎርፍ፣ የአካባቢ መጥለቅለቅ፣ የመንገድ መበላሸት፣ በዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ላይ የሚገኙ የማሕበረሰብ ክፍሎች በቂና አስተማማኝ መኖሪያ ስለሌላቸው በክረምቱ መቸገር የመሳሰሉት ይጠቀሳሉ። እንግዲህ ክረምትን ለበጎነት የሚለው መነሻ ሃሳቤ ትርጉም የሚያገኘው እዚህ ጋ ነው።

እንደሚታወቀው ሀገራችን ብዙ ድሆች የሚኖሩባት ሀገር ናት። የእኛን እርዳታ፣ የእኛን ድጋፍ የሚፈልጉ አያሌ የማሕበረሰብ ክፍሎች አሉ። ክረምት ሲሆን ደግሞ ይሄ ማሕበራዊ ምስቅልቅል እጅጉን ይጨምራል። በዚህም መሰረት ለወገናችን የምንደርስለት ትክክለኛ ጊዜ ላይ ነን እላለሁ። በጎ መሆን ከኪሳችን የምናወጣው ሳይሆን ከልባችን የምናወጣ ነገር ነው። በዙሪያችን የእኛን በጎ መሆን የሚሹ ብዙ ማሕበራዊ ችግሮች አሉ። ሀገር የምትቆመው የአንዱን ችግር አንዱ የኔ ነው ብሎ ሲነሳ ነው። ዜግነት ትርጉም የሚያገኘው የወገኖቻችንን ስቃይ መሰቃየት ስንችል ነው።

ለራስ ብቻ በማሰብ ውስጥ፣ ለራስ ብቻ በመኖር ውስጥ ዜግነት የለም። ሀገር ማለት ምንድነው ብሎ ለጠየቀ የመልካም ልቦች ሕብረት ነው የሚል መልስ ያገኛል። በእውቀታችን፣ በጉልበታችን፣ በገንዘባችን ለሀገርና ወገን አለኝታ መሆን ካልቻልን እኛ ምንም ነን ማለት ነው። ስለሆነም ክረምት ይዞብን የሚመጣው ማሕበራዊ ቀውስ የታወቀ ነውና ከወዲሁ መረዳዳታችንን ማጠንከር ይኖርብናል። በጎነታችንም በዙሪያችን ካሉ የሚጀምር ነው። በጎነታችን ከሰፈርና ከጎረቤት የሚጀምር ነው።

ክረምቱ ስቃይ እንዳይሆንባቸው በዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ላይ ያሉ ወገኖቻችንን ችግሮቻቸውን ጠይቆ በመረዳት መፍትሄ መስጠት ሰኔን የምንበቀልበት አንዱ መንገድ ነው እላለሁ። ቤት ለሌላቸው ቤት በመስራት፣ ቤታቸው ያረጀባቸውን ቤታቸውን በማደስ፣ ጎዳና ላይ የሚኖሩ ወገኖቻችንን ክረምቱን የሚያልፉበትን መንገድ

**ሰኔ የክረምት መግቢያ በር ነው። ሰኔ ዝርክርክ ብሎ የሚያዝረከርከን የጿጋና የመከራ ጌጣችን ነው። ወፍራም በመልበስና  የላመ በመብላት አንሸሽውም ምክንያቱም ወፍራም መልበስ የማይችሉና የላመ ለመብላት አቅም የሌላቸው ወገኖች አሉንና ነው። ሰውነት ስለ ሌላው መታመም ነው። ሰውነት በሌሎች ስቃይ መሰቃየት ነው። ክረምት ደግሞ ስለሌላው እንድንታመምና እንድንሰቃይ የሚያደርግ ጥሩ አጋጣሚያችን ነው። ምክንያቱም በክረምት ቤት የሌላቸው፣ በክረምት መሸሸጊያ ያጡ ነፍሶች ብዙ ናቸውና ነው**

በመፍጠር በተለያየ መልኩ ክረምቱን በበጎ ስራ ማሳለፍ እንችላለን።

በዛው ልክ ከተጠቀምንበት ክረምት ጿጋችን ነው። የሚያዘንብልንን ዝናብ ለበጎ ነገር የመጠቀም አቅሙና ሕብረቱ ካለን ከነበርንበት የድህነት ዝቅታ ከፍ ማለት ይቻለናል። በዓለም ላይ ቀዳሚ ያደረገንን የአረንጓዴ አሻራ ፕሮግራም ያሳካነው እኮ በክረምት ጿጋ ነው። ከራሳችን አልፈን አፍሪካን ያማከለ የአካባቢ ጥበቃ እንቅስቃሴ ያደረግነው እኮ በሰኔ ጉርምርምታ ታጅበን ነው። የታላቁ ህዳሴን ሶስተኛ የውሃ ሙሌት ለማስተናገድ የተዘጋጀነው እኮ በክረምት ሃይል ነው። እጆቻችንን ለልማት፣ ልቦቻችንን ለመልካም ስራ ያተጋነው እኮ ክረምት ስለመጣ ነው። ዘንድሮም ብዙ ችግኞችን ለመትከል እቅድ ይዘን እየተንቀሳቀስን ያለነው እኮ በክረምት ጿጋ ነው። እንደዚሁም ደግሞ የአቅመ ደካሞችን ቤት አድሰን ለመመረቅና ለመመስገን የተነሳነው እኮ በዚህ ጊዜ ነው።

ከሁሉ በላይ ደግሞ የመኖር ዋስትናችን የሆነው የአርሶ አደሩ መሬት የተሻለ ምርት ይይዝ ዘንድ ክረምት እጅግ አስፈላጊያችን ነው። አብቅለን ለመብላትና እያሰቃየን ካለው የኑሮ ውድነት ተላቀን ጥሩ ኑሮ ለመኖር ክረምት ዋስትናችን ነው። እንዲሁም ደግሞ አዲሱን ዓመት በደስታና በፍቅር እንድንኖር ክረምት ያሻናል እንዴት ላለኝ እንዲህ እለዋለው..ሁሉም አዲስ ዓመት የሀምሌና የነሀሴን ክረምት ጠጥተው ያማሩና የቆነጁ ናቸው። የምንናፍቀው መስከረም እንኳን አምሮና ተውቦ የምናገኘው ከፊቱ ባሉት የክረምት ወራት ተደግፎ ነው።

ዓለም ላይ መለያችን የሆነው፣ ጳጉሜን ተንተርሶ ነፍስ የሚዘራው አደይ አበባ እኮ የሀምሌና የነሀሴ ጽንስ ነው። በዓመት አንድ ጊዜ ብቅ ብላ የምትሰወረው የመስቀል ወፍ እኮ ጎጆዋን የምትቀልሰው በመስከረም ተስፋ ነው.. ተስፋዋን የሰጣት ደግሞ ክረምት ነው። እናም ክረምት ከተጠቀምንበት ጿጋችን ነው ካልተጠቀምንበት ደግሞ መከራችን ይሆናል።

ከእኛ የሚጠበቀው በክረምት ጿጋ እየተጠቀምን ችግሩን በጋራ ማሸነፍ ነው። ክረምት የፍቅር ወቅት ነው። ከመቸውም ጊዜ በላይ በዚህ ወቅት መዋደድና መፋቀር ይኖርብናል። በክረምት ጠብና ቁርሾ የማይታሰብ ነው። በክረምት ሁሉም ጦረኞች ጦር የሚጥሉበት፣ ይቅር ለእግዜር ተባብለው ወደ ስራ የሚገቡበት ጊዜ ነው። በክረምት እልኸኞች እልሃቸውን ትተው ወደ ልማት የሚሰማሩበት ነው። ምክንያቱም የክረምት ጿጋ በዓመት አንዴ ስለሆነ ነው። ቤታችንን በጋራ ሰርተን፣ ፍቅራችንን በጋራ አለምልመን ቀጣዩን የበጋ ወራት በደስታና በአንድነት እናልፍ ዘንድ ዛሬን መረዳዳት ግድ ይለናል።

መንግሥት ይሄን የክረምት ወቅት ለብዙ የልማት ስራዎች መጠቀም አለበት። እኛም ዜጎች በዚህ ክረምት ለራሳችንም ሆነ ለሌሎች በጎ ስራ በመስራት ሃላፊነታችንን መወጣት ይጠበቅብናል። ክረምትን በጦርነት ያሳለፈ ማሕበረሰብ ቀጣዩ ጊዜው የስቃይ ጊዜ ነው የሚሆነው። በክረምት ያላበቀለ፣ በክረምት ይቅር ያልተባባለ ጠበኛ መጪው ጊዜ ጥሩ አይሆንም። በክረምት ቂማችንን ካልተውን፣ በክረምት ትጥቅ ካልፈታን መጪው ጊዜ ይበረታብናል። እናም ክረምትን ለይቅርታና ለልማት፣ ለመረዳዳትና ለመተጋገዝ እንድናውለው አሳስባለሁ።

ሀገር መውደድ ሰውን መውደድ ነው። የሀገር ፍቅር ስሜት ከሚገለጽባቸው መንገዶች ውስጥ አንዱ አስቸጋሪ ጊዜዎችን በጋራ ማለፍ ነው። ከፊታችን ያሉ ጊዜዎች መልካም የሚሆኑት ዛሬ ላይ በምናደርገው ድርጊት ነውና ከነውር ወጥተን ሊጠቅመን በሚችል በጎ ስራ ላይ ማሳለፍ ይጠበቅብናል። ልባችንን ለበጎ ካስገዛን ክረምት የምንረዳዳበት ትክክለኛ ጊዜ ነው። ከፍ ብዬ እንዳልኳችሁ ከመቸውም ጊዜ በላይ ክረምት ስቃይ የሚሆንባቸው ብዙ የማሕበረሰብ ክፍሎች አሉ። ከመከራው አንጻር ጭራሽ ክረምት ባልመጣ ብለው የሚመኙ ጥቂቶች አይደሉም። ይሄ ደግሞ ክረምት ምን ያክል ችግረኛው ማሕበረሰብ ላይ እንደሚበረታ አንዱ ማሳያ ነው።

በዚህ ጊዜ ነው ለወገናችን ልንደርስለት የሚገባው። በእንዲህ ያለው ወቅት ነው አጋርነታችንን ልናሳይ የሚገባን። በክረምት የሚያለቅሱ አይኖች፣ የሚባቡ ልቦች ጥቂት አይደሉም።  ዙሪያችንን ቃኘት ማድረግ ብንችል ብዙ ችግረኛ ሰዎችን ማግኘት እንችላለን። በክረምት ቤታቸው ዝናብ እያስገባ የሚሰቃዩ እናቶች ጥቂት አይደሉም የነሱን እንባ ማበስ ደስታው ምን ያክል እንደሆነ መገመት አይከብድም። በክረምት መጠጊያ አጥተው ጎዳና ላይ እትት የሚሉ ችግረኛ ወገኖች አሉ እነሱን መታደግ በረከቱ ምን ያክል እንደሆነ አይጠፋንም። በክረምት መንገዶች በጎርፍ ይጥለቀለቃሉ፣ ይቦረቦራሉ፣ ጉምና ጭጋግ ስለሚበዛ በዚህም የትራፊክ አደጋ ከፍ ይላል። እኚህ ሁሉ ክረምት ወለድ ሀገራዊና ማሕበራዊ ችግሮቻችን እልባት የሚያገኙት በእኛ መልካም ተግባር ነውና ክረምትን ለበጎነት እንጠቀምበት እላለሁ።

በክረምት የመሬት መንሸራተት አደጋ ያይላል። በከተማም ሆነ በገጠር እንዲህ አይነቱ አደጋ የተለመደ ነው። ይሄን አይነቱን አደጋ ለመቅረፍ ከአሁኑ የእርከን ስራዎች ቢሰሩ መልካም ሆናል። አምና በዚህ ሰአት የክረምትን መግባት ተከትሎ የተከሰቱ በርካታ የተፈጥሮ አደጋዎች አሉ። እነዛን አደጋዎች ለመከላከል ሁላችንም ባለንበት መልፋት ይጠበቅብናል። ክረምትና የትራፊክ አደጋም እንደዚሁ የአንድ ሳንቲም ሁለት ገጽታዎች ሆነው ከትናንት ዛሬ የዘለቁ ናቸው። የመሬት መንሸራተት ስለሚኖር በዛው ልክ የትራፊክ አደጋው ይጨምራል። ጉሙና ጭጋጉ ሲጨመርበት ደግሞ ወትሮ ሃይ ባይ ያላገኘው የትራፊክ ችግራችን በእንቅርት ላይ ሆኖ ለአደጋ ተጋላጭ ነው የሚያደርገን። እግረኛም ሆነ አሽከርካሪ መጪውን ጊዜ ግምት ውስጥ በማስገባት ከወዲሁ ለራሱ ዋስትና ቢሰጥ መልካም ነው እላለሁ።

በሁሉም ነገር ለሀገራችን ዘብ የምንቆምበት ጊዜ ላይ ነን። በልማቱም በሰላሙም በእርቁም ለሀገራችን ውለታ የምንውልበት ጊዜ ላይ ነን። ብልህ ሰው ነገውን ዛሬ የሚሰራ ነው። ብልህ ሰው አስቸጋሪ ጊዜዎችን በመተባበር የሚያልፍ ነው። እኛም በቀና ልብ ነጋችንን ዛሬ መስራት ይኖርብናል። አስቸጋሪ ጊዜዎቻችንን በመነጋገርና በመመካከር ማለፍ ግድ ይለናል። መጪው ጊዜ ብሩህ እንዲሆን በመልካም ልብ የምናከናውናቸው ተግባራት ብዙ ናቸው። ከወዲሁ ተጋግዘን እልባት ካልሰጠናቸው በቀር ክረምትን ተከትለው የሚመጡ ማሕበራዊ ቀውሶች ቀላል የሚባሉ አይደሉም።

ከአንድ ብርቱ ሁለት መዳኒቱ እንደሚባለው ክረምት ወለድም ሆኑ በጋ ወለድ ችግሮቻችን በአንድነት የሚረቱ ናቸው። ሀገር በመረዳዳት ውስጥ ውብ ናት። ለብቻ ቆመን፣ ለብቻ አስበን የምናሳካው አንዳች ነገር የለም። የኔ ችግር የማሕበረሰቡ ችግር ነው። የአንተ ችግር የኔና የሌላው ችግር ነው። ይሄን እውነት ታሳቢ አድርገን ለጋራ ጥቅም በጋራ መንቀሳቀሳችን ትርፍ እንጂ ጉዳት የለውም። እስካሁን ድረስ ያልተሳካልን ለብቻ ስለቆምን ነው። ይሄ ክረምት አንዱ ለአንዱ አጋርነቱን የሚያሳይበት፣ ያለው ለሌለው አለሁልህ የሚልበት ጥሩ አጋጣሚ ነው። ችግሮቻችንን በህብረትና በአንድነት ካልሆነ በመለያየት የማንወጣበት ጊዜ ላይ ነን። መለያየት ጥቅም ቢኖረው ኖሮ ከማንም በፊት እኛ እንጠቀም ነበር። ግን ጥቅም የለውም..ተለያይተን ያተረፍነው ነገር የለም። ስለዚህም በዚህ የክረምት ወቅት በዙሪያችን ላሉ ሁሉ መልካም የምንሆንበት ጊዜ ነው። ለጎረቤቶቻችን፣ በአካባቢያችን ላሉ ችግረኞች የምንደርስበት ጊዜ ነው።

# ግብርና

# ግብርናን ለማዘመን የሚጥረው ምሁሩ አርሶ አደር

**ጽጌረዳ ጫንያለው**

ተወልዶ ያደገው በአማራ ክልል፣ ሰሜን ሸዋ ዞን፣ ሞረትና ጅሩ ወረዳ፣ እነዋሪ ከተማ ሲሆን፤ እስከ 12ኛ ክፍል ድረስ የተማረውም በዚያው ነው። በ1995 ዓ.ም ከጂማ ዩኒቨርሲቲ የግብርና ኮሌጅ በዲፕሎማ ትምህርቱን አጠናቋል።

የትምህርትን ዋጋ በደንብ ያውቃልና በተማረበት የግብርና ሙያ እየሰራ ትምህርቱን በመቀጠል እስከ ሁለተኛ ዲግሪ ድረስ ተምሯል። በፋይናንስና ኢኮኖሚክስ እንዲሁም በግብርና የትምህርት መስኮች ሁለት የመጀመሪያ ዲግሪዎች ባለቤት ነው። በገጠር ልማት አስተዳደር (Rural Development Management) የትምህርት መስክ ደግሞ ሁለተኛ ዲግሪውን ከባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ አግኝቷል። በዛሬው የግብርና አምዳችን ያቀረብነው የመማርን ትርጉም የተረዳው በጋሻው መብራቴ።

በአፋር፣ በቤኒሻንጉል፣ በአማራ ክልሎችና በአዲስ አበባ በተለያዩ መንግሥታዊ ተቋማት እንዲሁም ሀገር በቀልና ዓለም አቀፍ መንግሥታዊ ያልሆኑ ተቋማት ሰርቷል። በጋሻው ከሰራባቸው ተቋማት መካከል የአሜሪካ ዓለም አቀፍ ተራድኦ ድርጅት (USAID) እና ፋርም አፍሪካ (Farm Africa) ይገኙበታል።

በተለይም ግብርናውን ይፈትኑታል ተብለው የሚታሰቡትን በረሃና ሙቀት የሚፈራረቅባቸውን ቦታዎች በደንብ አይቷቸዋል፤ጥሩ ሥራም ከውኖባቸዋል። በተለያዩ የኃላፊነት ደረጃዎች ላይ ባገለገለባቸው ተቋማት ውስጥ ሲሰራ ስራዎቹ ሀገርን የሚጠቅሙና ግብርናውን የሚያሻሽሉ እንዲሆኑ ታትሯል። በእዚህም ብዙ ልምዶችን እንዲቀስም እድል አግኝቷል።

ፊት በግብርና ላይ ያለው እውቀትና ግንዛቤ ውስን ነበር። በስራና በትምህርት አጋጣሚዎቹ ግብርና ማለት አብዛኛው ሰው በተለምዶ ከሚያውቀው ተግባር የሰፋ እንደሆነ ተገነዘበ። ዘመናዊ የግብርና ቴክኖሎጂዎች፣ ምርታማነትን የሚጨምሩ የግብርና ዘዴዎች ፣ወዘተ. እንዳሉ አወቀ። ‹‹እኛ ኢትዮጵያውያን በግብርናው ዘርፍ ለምን ወደ ኋላ ቀረን›› እያለ በተደጋጋሚ ያስብና ይጠይቅ ነበር።

ተወልዶ ያደገበትን አካባቢ ያለውን የዘመናዊ የግብርና ግብአቶች እጥረት አስተዋለ። ‹‹እኔ ከአንድም ሁለት ዲግሪዎችን ተምሬያለሁ። ይህን ችግር ማቃለል ካልቻልኩ የእኔ መማር ትርጉሙ ምኑ ላይ ነው?›› ብሎ ራሱን ጠየቀ። የአርሶ አደሩን ችግር የሚያቃልልና የግብርናውን ዘርፍ ውጤታማነት ለማሳደግ አስተዋፅኦ የሚያደርግ ትልቅ የግብርና ኩባንያ ለማቋቋም ተመኘ።

ግብርናውን በቴክኖሎጂ በማገዝ የዘርፉን ውጤታማነት ለማሻሻል መስራት እንዳለበት አምኖ ስራውን ለመጀመር ተነሳ። መነሻ ካፒታል ለማግኘትም አማራጮችን ማማተር ጀመረ። በቶኒ ኤልመሉ ፋውንዴሽን የስራ ፈጠራ ውድድር ላይ ተሳትፎ በማሸነፍ መነሻ ካፒታል ማግኘት ቻለ። አካባቢውን፣ የአርሶ አደሩን ሕይወት እንዲሁም ግብርናው ያሉበትን ክፍተቶች ስለሚያውቅ ወደ ትውልድ ስፍራው ተመልሶ በ370ሺ ብር የእህል መውቂያ መሳሪያ ገዝቶ ስራ ጀመረ፤ በጋሻው የተማረ አርሶ አደር መሆን ጀመረ።

በድርጊቱ ብዙዎች ተገረሙ። ‹‹ጥሩ ክፍያ የምታገኝበትን ስራህን ትተህ እንዴት እንደዚህ ታደርጋለህ?›› ብለው የጠየቁት ነበሩ። ‹‹አብዷል›› ያሉትም ነበሩ። በትልልቅ መንግሥታዊ ያልሆኑ ተቋማት ውስጥ በከፍተኛ ደመወዝና በትልቅ የኃላፊነት ቦታ መስራትን በመተው ወደ ገጠር ተመልሶ አርሶ አደር መሆን ለአካባቢውም ሰው የሚዋጥ አይደለም። ለእርሱ ግን ወደ አካባቢው መመለሱም ሆነ ስራውን መጀመሩ የሚገጥሙትን መሰናክሎች ሁሉ ተቋቁሞ በማለፍ ያሰበውን ዓላማ ለማሳካት መሰረት የሚሆነው ተግባሩ ነውና በጥያቄውና በወቀሳው ሳይበገር በስራው በረታ።

ሙያው ሰርቶ ማሳየትን የሚፈልግ ነውና ወደ አርሶ አደሩ ዘንድ በመዝለቅ በስራና በትምህርት ልምድ ካገኘው ተሞክሮ ስለግብርና ቴክኖሎጂ ማስተማር ጀመረ። ጎን ለጎንም መሬት በኮንትራት ወስዶ በአትክልትና ፍራፍሬ ልማት እና በምርምር ስራ ላይ ተሰማራ። ለምርምሩ መነሻ የሆነውም በአካባቢው በስፋት ይስተዋል የነበረው የምስር በሽታ ነው። የዘር እጥረት ችግርን ለማቃለልም ምርምር ያደርጋል። አርሶ አደሩን የማስተማር፣ አትክልትና



ፍራፍሬ የማልማት እንዲሁም የምርምር ስራዎቹ መልካም ውጤቶችን አስገኝተውለታል።

በጋሻው በክረምት ወራት ቀደም ሲል በአካባቢው ያልተለመዱ እንደ ጥቁር አዝሙድ፣ ካሮትና ሱፍ የመሳሰሉትን በአንድ ላይና አሰባጥሮ በመዝራት ለአካባቢው ማህበረሰብና ለአርሶአደሩ ማስተማሩን ቀጠለ። ይህ ተግባሩም የአካባቢው ሕዝብ በክረምትም ሆነ በበጋ የአትክልትና ፍራፍሬ እጥረት እንዳይገጥመው ከማድረግ ባሻገር ያልተለመዱና በውድ ዋጋ የሚሸጡ እንደ ጥቁር አዝሙድ ያሉ ቅመማ ቅመሞችን በቀላሉና በተመጣጣኝ ዋጋ እንዲያገኙም አድርጓል።

ንብ በማነብ ሥራ ላይ የተሰማሩ አርሶ አደሮች ስራ ውጤታማ እንዲሆን በሚልም የሱፍ አበባን ከአትክልትና ፍራፍሬው ጎን ለጎን ያለማል፤ ምርቱንም አሸጎ ያከፋፍላል። ይህ ተግባር ለአካባቢው ውበት የሚሰጥ በመሆኑ ብዙዎች እንዲማረኩበትና በተለይም ወጣቶች ግብርናን እንዲወዱ አደረጋቸው። አርሶ አደሩም የበጋሻውን ፋና በመከተል የአትክልትና ፍራፍሬ ዘር ማሳው ላይ እንዲያመርትም አስችሎታል።

የተማረውን ሙያ በሚገባ በተግባር ላይ አለማየቱና ለአገሩ ያለው ልዩ ፍቅር አርሶአደሩ ዘንድ ወርዶ እንዲሰራ እንዳነሳሳው የሚናገረው በጋሻው፤ የግብርና ባለሙያ መሆን መሪም ሰሪም መሆን ነው ብሎ ያምናል። መሪነቱ ደግሞ በእውቀትና በተግባር መታየት እንዳለበትም ይገልጻል።

በጋሻው እስከ ሁለተኛ ዲግሪ ድረስ ሲማር ከግብርና ስላልተለየና ሥራውን በተማረው ልክ በማከናወኑ ውጤቱን ለመመልከት ብዙ ዓመታት አልፈጀበትም። የእርሱ የእርሻ ስራ ሰርቶ ማሳያ የሆነላቸው የአካባቢው አርሶ አደሮች ስራውን ተመልክተውና ልምዱን ወስደው የግብርናቸውን ጎደሎ ሞልተውበታል። የአካባቢው አርሶ አደሮች በበጋ ወራት በመስኖ ማምረትን ሰፋ አድርገው የያዙት ከበጋሻው ትምህርትና ተሞክሮ ወስደው ነው። በተለይ በክረምት ወቅት ለብዙ ወጣቶች የስራ እድል ፈጥሯል።

አርሶ አደሩን የቴክኖሎጂ ተጠቃሚ በማድረግ ምርቱን መጨመርና ሕይወቱን ማቅለል የበጋሻው ትኩረት ነው፤ ለእዚህም አርሶ አደሮች ዘመናዊ የግብርና ቴክኖሎጂዎችን እንዲጠቀሙ ቀንና ሌሊት ይተጋል። ‹‹ሁሉም ሰው ቴክኖሎጂን ተከትሎ መጓዝ አለበት፤ ከተቻለ ቀድሞ መጓዝም ያስፈልጋል። ቴክኖሎጂ ማለት አዳዲስ ነገሮችን መከተልና የሚጠቅመውን መርጦ መውሰድ ነው።›› የሚለው በጋሻው፣ አርሶ አደሩ ብዙ ሥራዎቹን ቀላል የሚያደርጉለት የቴክኖሎጂ ውጤቶች እንዳሉ መገንዘብና ማመን እንዳለበት ይናገራል። ‹‹ይህ ሲባል ግን ‹ተቀበል› የተባለውን ሁሉ መቀበል ይገባዋል ማለት አይደለም። ውጤታማነታቸው በሰርቶ ማሳያ የተረጋገጠና ለአካባቢውም ሆነ ለመሬቱ የሚስማሙ የግብርና ቴክኖሎጂዎችን መተግበር ይገባዋል›› ነው የሚለው። የሚያከናውናቸው ተግባራት ለአርሶ አደሩ የቴክኖሎጂ ሽግግርን እውን የሚያደርጉ እንዲሆኑ ይጥራል።

የእርሻ ባለሀብት የመሆን ራእይ ያለው በጋሻው፤ አሁን ብዙ ተግባራትን እየከወነ ይገኛል። በዚህ ፍጥነት ከተጓዘ በጥቂት ዓመታት ውስጥም ራእዩ እውን እንደሚሆንም ያምናል። በሀገሪቱ በግብርና ሥራ ፈጠራ ዙሪያ የሚፈለገውን ያህል ስላልተሰራ እርሱና ጓደኞቹ ይህን ሁኔታ ለመቀየር እንደ ባለሙያ ጥረቶችን እያደረጉ እንደሆነ ይናገራል።

‹‹በጋሻው ፋርም ቴክኖሎጂ (B Farm Tech)›› በተባለው በግሉ በከፈተው ድርጅት በኩል የመውቂያ ማሽን አቅርቦት አገልግሎት ከመስጠት በተጨማሪ ዘርፉን በዲጂታል ቴክኖሎጂ ለማገዝም እየሰራ ነው። በዚህ ተግባሩም መውቂያ እና ትራክተርን የሚያገናኝ መተግበሪያ (አፕሊኬሽን) በማሰራት ላይ ነው። ይህ ሥራ ልክ እንደራይድ አገልግሎት ፈላጊው ደውሎ አገልግሎቱን የሚያገኝበትን አሰራር የሚፈጥር ነው። በተጨማሪም የግብርና መሳሪያዎች ሁሉ ከውጭ እየመጡ አገልግሎት የሚሰጡ በመሆናቸው አገርንም አርሶአደሩንም መጥቀም ባለባቸው ልክ እየጠቀሙ ባለመሆኑ መሳሪያዎቹን በአገር ውስጥ ለማምረት ጥረት እያደረገ ነው።

‹‹የተለየ ጥረት የተለየ ስኬትን ይሰጣል›› ብሎ የሚያምነው በጋሻው፤ ከጓደኞቹ ጋር በመሆን ‹‹ንስር አግሪ ቴክ›› የሚባል ድርጅትም አቋቁሟል። በዚህ ድርጅት በኩል እስካሁን ካከናወናቸው ተግባራት የላቁ ተጨማሪ ስራዎችን ለመስራት አቅዷል። ድርጅቱን የመሰረቱት ባለሙያዎች የትምህርት ዝግጅትና የስራ ልምድ ደግሞ ይህን ዓላማ ከማሳካት የመነጨ እንደሆነ መገንዘብ ይቻላል። በግብርና ላይ የተሰማራው በጋሻው፣ በኤሮስፔስ (Aerospace) ዘርፍ የዶክትሬት ዲግሪ ካለው እና ከኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ባለሙያ ጓደኞቹ ጋር በጥምረት የተቋቋመው ይህ ድርጅት በግብርናው ዘርፍ ለአገር የበኩሉን አስተዋፅኦ እንደሚያበረክት ተስፋ አላቸው።

በአሁኑ ወቅት የበጋሻውና ጓደኞቹ ዋና ትኩረት የግብርናውን ምርታማነት የሚያሻሽል ድሮን (Drone) ጥቅም ላይ ማዋል ነው። በዚህ ተግባራቸውም በድሮን የሰብል፣ አትክልትና ፍራፍሬ በሽታዎችን የመለየት፤ የመድኃኒት ርጭት እና አንበጣ የማባረር ተግባራትን ለማከናወን እየጣሩ ነው። ሥራቸው እውቅና ተሰጥቶት ወደ ተግባር እንዲገቡ የተፈቀደ ቢሆንም፣ ድሮንን ለማብረር ሕግና ፖሊሲ አለመኖሩ ግን እንቅፋት ሆኖባቸዋል።

‹‹ግብርና ሥራ ሲያጡና ሥራ ሲፈቱ የሚገባበት ሙያ አይደለም፤ የራስ ገነትን መፍጠሪያ እንጂ። ምክንያቱም ተፈጥሮን እየተመገቡ ተፈጥሮን ለሌላ መመገብ የሚቻልበት መስክ ግብርና ነው።›› የሚለው በጋሻው፣ ይህ እውን የሚሆነው በእውቀትና በፍላጎት ሲሰራ ብቻ ነው ይላል።

‹‹እኔ አሁን ባለሁበት ደረጃ የመውቂያ ማሽን በማከራየትና በሌሎቹ የግብርና ስራዎቼ በወረዳ ደረጃ ማንም ሰው የማይከፈለውን ደመወዝ በወር አገኛለሁ። ከፋዩ ደግሞ ራሴ ነኝ። የምናተርፈው ብዙ ጊዜና ነጻነት እንዳለ ማወቅም ይገባናል። ሙያንና ልምድን ማካፈልም እጅግ አስፈላጊ ነው›› የሚለው የግብርና ባለሙያው፤ የምግብ ዋስትናን ማረጋገጥ እንደሚገባና በተለይም የግብርና ባለሙያዎች ይህን ቢጠቀሙ አትራፊ እንደሚሆኑ ይናገራል።

በጋሻው ግብናውን ለማዘመንና የአርሶ አደሩን ሕይወት ለማሻሻል ላከናወናቸው ተግባራት ሽልማቶችን አግኝቷል። ስራው ከአካባቢው አልፎ በክልል ደረጃ በመልካም ተሞክሮነት የሚጠቀስ ለመሆን በቅቷል።

በጋሻው ግብርና ከተለመደው አሰራር የተሻለና በሙያ የታገዘ አሰራር እንደሚያስፈልገው በፅኑ ያምናል። እንደ እርሱ ገለጻ፤ አመራሩ አርሶ አደሩን አሳምን ተብሎ ያልተገባ ነገር ማስተማር የለበትም። ኮርጆ ማስኮረጅም ይህ አይደለም። ምክንያቱም በዚህ ዓይነቱ አካሄድ አርሶ አደሩ በብዙ መንገድ ተጎድቷል። መሬቱ ሳይመረጥ ይህንን ዝራ ተብሎ ዋጋ እየከፈለ ነው። በተለይ ዛሬ ላይ የተፈጥሮ ማዳበሪያ እንኳን መጠቀም እንዳይችል ሆኗል። እናም መስጠት ያለብን የሚጠቅመውን እንጂ የማይስማማውን መሆን የለበትም። ባለሙያውን እንዲሰማና ቴክኖሎጂውን እንዲጠቀም ለእያንዳንዱ መልከአምድር የሚስማማውን ነገር ማጥናትና መስጠት ያስፈልጋል። ለዚህ ደግሞ የግብርና ባለሙያዎች ትልቅ ኃላፊነት አለባቸው። የሚጠቅመውን ለማሳየት መጣርና መመራመርም ይገባቸዋል።

የግብርና ባለሙያዎች የራሳቸው ሥራ ፈጣሪ እንዲሆኑ ማስቻል ላይም በሚገባ አልተሰራም ይላል፤ በጋሻው። ይህ ቢሆን ኖሮ ለአንድ ቦታ ብቻ የተሰጠውን ተክል ሌላ ቦታ ላይ በማላመድ የምግብ ችግራችንን መቅረፍ እንችል ነበር። ሆኖም ውጭውን እንጂ ራሳችንን እንድናይ ሆነን ስላላለፍንና አምነንበት ቁርጠኛ ሆነን ወደ ሥራው ስላልገባን ችግሩ እንዲቀጥል አድርጎታል። ስለሆነም በዚህ ጉዳይ ላይ መንግሥት ልዩ ትኩረት ሰጥቶ ጥናት ተደርጎ ሊሰራበት እንደሚገባም ያሳስባል።

‹‹ ... ሰው የሚሠራው አለቃው ያዘዘውን ነው። ሳይንስ ተኮርም አይደለም። ግብርና ደግሞ ፍላጎትንና እውቀትን ይሻል። እውቀቱና ሙያው የሌለው ሰው ቦታውን እየመራው፤ ባለሙያው ደግሞ በምንቸገረኝነት ሥራውን እየከወነው ውጤት መጠበቅ ሞኝነት ነው። እናም ከዚህ የአሰራር ችግር ካልወጣን ግብርናውን ማዘመን አንችልም። ሙያን በአግባቡ መጠቀም ከጥገኝነት መላቀቅ ብቻ ሳይሆን ለራስ ነጻነትን መስጠት ነው። አዳዲስ ፈጠራዎችን ለመስራት ራስን ነጻ ማድረግ ይገባል›› በማለት ያስረዳል።

የተማረ ሰው ብር ጠባቂ ሳይሆን ብር ፈጣሪ መሆን እንዳለበት የሚያምነው በጋሻው፤ በተለይም ቢሮ ላይ ያሉ ሰዎች ተጨማሪ የሙያቸው ሰራተኛ መሆን እንደሚገባቸው ይመክራል። በተለይም የግብርና ሰራተኞች የኃላፊያቸው ትዕዛዝ አስፈጻሚዎች መሆን ብቻ እንደሌለባቸውና እውቀት የሚጠይቁና በአርሶ አደሩ ሕይወት ላይ ተጨባጭ ለውጥ መፍጠር በሚችሉ የዘርፉ ተግባራት ላይ ማተኮር እንደሚገባቸው በአፅንዖት ይመክራል።

‹‹ ብዙ ችግሮች ካሉና ብዙ የሚማረር ሰው ካለ ያንን ችግር መፍታት የሚችል ኃይል ስለሚያስፈልግ ብዙ የሥራ እድል አለ ማለት ነው። ለዚህ ደግሞ ቅርብ የሚሆነው የተማረውና የተመራመረው ነው። እናም ራስን የዚያ አካል ማድረግ እጅግ አስፈላጊ ነው። በፈለጉት መልኩ ለመሥራት ያለንበትንና ወደ ፊት መሆን የምንፈልገውን ማወቅ አለብን። ከዚያም ሀሳባችንን ለመተግበር ቁርጠኛ እንሁን። ተስፋ ባለመቁረጥ ውስጥ አዳዲስ ፈጠራዎችን እንሞክር። ያን ጊዜ ለራሳችን ብቻ ሳይሆን ለሌሎችም የምንተርፍበትን መንገድ እናገኛለን›› ይላል።

ማህበራዊ

# አስኳላ

## እድልና ተስፋን ይዞ የመጣው የዲጂታል ትምህርት ማዕከል

**ጽጌረዳ ጫንያለው**




‹‹እኔ የዘጠነኛ ክፍል ተማሪ በመሆኔ እድለኝነቴን ዛሬ አይቻለሁ። ተስፋዬንም ከአሁን ጀምሮ ሰንቄያለሁ። ምክንያቱም ቀጣይ አራት ዓመታት በዲጅታል ቴክኖሎጂው እጠቀማለሁ። የተሻለች ተማሪ መሆንም እችላለሁ። በተለይም ምንም ኮምፒዩተር ነክቼ አለማወቄ ጉጉቴን አግዝፎታል። አዲስ ነገር ለማወቅም ሁልጊዜ እንደምሰራ ለራሴ ቃል እንድገባም አድርጎኛል። በተስፋና በተግባር የተደገፈ ትምህርት ደግሞ የታሰበበት ላይ እንደሚያደርስ አምናለሁ። ስለዚህም ኢትዮ ቴሌኮም ለሰጠኝ እድል አመሰግናለሁ›› ኢትዮ ቴሌኮም የዲጅታል ትምህርት ማዕከላትን በሁለተኛ ደረጃ ትምህርትቤት አቋቁሞ ባስመረቀበት ጊዜ በከፍተኛ 23 ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የምትማረዋ ልጅ ከመድረኩ ላይ ወጥታ የተናገረችው ነው።

ይህ እድል እርሷንና መሰሎቿን ለማንቃት፣ ለማሻሻልና የአገር ጠበቃ ለማድረግ የመጣ በመሆኑ በደስታ ነው ሃሳቧን የገለጸችው። በተመሳሳይ ይህንኑ ሃሳብ የሚጋሩት የቀድሞ የከፍተኛ 23 ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪና የአሁኑ የኢትዮ- ቴሌኮም ተፊክስድ ኔትዎርክ ቺፍ ኦፊሰር አቶ ቴዎድሮስ ኃይለመስቀል፤ ይህ ጊዜ ብዙ እድል የሰጠበት ነው። በተለይ ተማሪዎች ከተጠቀሙበት እድለኛ የሆኑበት ወቅት ነው። ቴክኖሎጂውን በኮምፒዩተር ብቻ ሳይሆን በእጅ ሞባይላቸው ጭምር ይዘው የሚዞሩትና ለመረጃ ቅርብ የሚሆኑበትም ነው። እናም እድለኝነታቸው በቃላት የሚገለጽ ካለመሆኑም በላይ የመማር ማስተማር ስራውን በብዙ መንገድ ያሳልጣል ይላሉ።

አቶ ቴዎድሮስ እንደሚሉት እርሳቸው ተማሪ በነበሩበት ወቅት ቤተመጻሐፍት አግኝቶ ለማጥናት እንኳን ከሰዓት በላይ በእግራቸው ይጓዙ ነበር። ኮምፒዩተርማ የማይታሰብ ነበር። እናም ትምህርት ከመጻሐፍት ውጪ የለም። እርሱም ቢሆን እንደልብ ከተገኘ ነው። ስለሆነም ከኮምፒዩተር ጋር የተዋወቅነው ሥራ ላይ ሳለን ነው በማለት ተማሪዎች ይህንን አጋጣሚ በአግባቡ ሊጠቀሙበት እንደሚገባ መክረዋል። ነገር ግን ይህንን ቀላል መንገድ መጠቀሙ ደግሞ እንዳያዘናጋቸውም ጥንቃቄ ማድረግም ይገባል ባይ ናቸው።

የኢትዮ ቴሌኮም ዋና ሥራ አስፈጻሚ ወይዘሪት ፍሬህይወት ታምሩም በበኩላቸው በእርሳቸው ጊዜ ተማሪዎች የሚገጥማቸው ችግር በቀላሉ የሚገለጽ እንዳልነበረ ያስታውሳሉ። ኮምፒዩተር ሳይንስ ጭምር በዲግሪ የተመረቁ ተማሪዎች ዳግመኛ ካልተማሩ ለመሥራት የሚቸገሩበት ሁኔታ እንደነበርም ያስታውሳሉ። ይህ ደግሞ ጊዜንና ገንዘባቸውን እንደሚወስደውም ያወሳሉ። ምክንያቱ ደግሞ ከታች ጀምሮ አለመማራቸውና ከቴክኖሎጂው ጋር አለመተዋወቃቸው ነው። ዩኒቨርሲቲ እስኪገቡ ድረስ ብዙዎች ኮምፒዩተርን አይጠቀሙም። ዩኒቨርሲቲም ከገቡ በኋላ ገና ዳዴ ስለሚሉ ቶሎ እውቀቱን ለመጨበጥ ይቸገራሉ። ከወጡ በኋላም ለመቀጠር ወኔ የማይኖራቸው ለዚህ እንደሆነ ያስረዳሉ።

የሚቀጥር ሰው ለማግኘት አቅምና ችሎታ ግድ እንደሆነ የሚያነሱት ዋና ስራ አስፈጻሚዋ፤ ጊዜ ፈጅተው ዳግም ኮምፒዩተር ሴንተር ገብተው ለመለማመድ የሚያስገድዳቸውም ይህ ጉዳይ ነው። ግን ዛሬ ነገሮች አልፈዋል። የአሁን ተማሪዎች በተለይም የሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች ብዙ ነገርን የሚያቀሉበትን እድል አግኝተዋል። ትምህርታቸውን ጭምር በቀላሉ ለማጥናትና የፈለጋቸውን መረጃ ለማግኘት ምንም አይቸገሩም። ይህ ደግሞ ተማሪ ሆነውም ቢሆን የመሥራት እድላቸው እንዲሰፋላቸው ያደርጋል። በአግባቡ ከተማሩና ከተመረቁ በኋላም ስለ ቅጥር የሚያስቡት ነገር እንዳይኖር የሚያግዛቸው ነው። ሆኖም ለተጠቀመበት እንጂ ላየው አይደለም ይላሉ።

እንደ ወይዘሪት ፍሬህይወት ገለጻ፤ የቴሌኮም አገልግሎቶችን መጀመር ብዙ ነገሮችን ለተማሪዎች መስጠት ነው። ያልተማረውን ማሕበረሰብ ጭምር ማገዝ ነው። ምክንያቱም አገልግሎቱ በአንድ ቦታ የተወሰነ አይደለም። እንደ አገር የሰፋ ፤ ብዙውን የማሕበረሰብ ክፍል የሚያዳርስ ከዚያም ባሻገር መሰረተ ልማቶችን ለማስፋፋት፣ ዘመኑ የደረሰበትን አዳዲስ ቴክኖሎጂዎች ተግባራዊ ለማድረግ የሚያግዝ ነው። እናም ጅማሮውን በትምህርት ቤት ማድረጉ መሰረቱ የጸና እንዲሆንም ያስችለዋል።

የዲጂታል መማሪያ ማዕከላት (digital learning centers) መስፋት የማሕበረሰብ ተጠቃሚነትን ከማረጋገጥ ባሻገር አገር ተረካቢ ትውልድን ለማፍራት አስፈላጊ ነው። ለዚህ ደግሞ ከምንም በላይ በትምህርት ዘርፉ ላይ ትርጉም ያለው ለውጥ ማምጣት ያስፈልጋልና ዘመኑን የሚመጥን ትምህርት ለመስጠት ኢትዮ ቴሌኮም ስትራቴጂያዊ እቅዶችን ነድፎ ተግባራዊ እያደረገ ይገኛል ብለዋል።

ያለንበት ዘመን የዲጂታል ዘመን እንደመሆኑ የመማሪያ ማዕከላትን መገንባት ፤ የቴክኖሎጂና አዳዲስ የመማሪያ አካባቢን መፍጠር ያስፈልጋል። ተማሪዎች ከዲጂታል ቴክኖሎጂው ጋር አብረው እንዲጓዙ መደገፍም የግድ ነው። በተጨማሪም የመረጃ ተደራሽነትን ማሳደግ፣ የበጎ ፈቃደኛ ሠራተኞችን ተሳትፎ በትምህርትና በሥልጠና ማጎልበት፤ እውቀታቸውንና ክህሎታቸውን ለሚኖሩበት ማሕበረሰብ እንዲያካፍሉ ማስቻል እንዲሁም ሙያዊ ትንታኔ እና ችግር ፈቺ ክህሎቶችን ማዳበርም ይገባል። ለዚህ ደግሞ ሁሉም ተቋም ኃላፊነቱን ወስደው ባሉበት ደረጃ ልክ መወጣት ይኖርባቸዋል። በመሆኑም ኢትዮ ቴሌኮም ጀማሪ የመሆን ተግባሩን እንደፈጸመ በምረቃው ወቅት ተናግረዋል።

ሌላው የዲጂታል መማሪያ ማዕከላትን በማቋቋም ተግባራዊ የተደረገው ይህ እድል በአገር አቀፍ ደረጃ በ66 የመንግሥት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ሲሆን ኢትዮ ቴሌኮም ዲጂታል ኢትዮጵያን ዕውን ለማድረግ ብሎም የነገ ሀገር ተረካቢ ዜጎችን በዕውቀት ለማነጽ በሚል ሥራውን እያከናወነ እንደሚገኝም አብራርተዋል። በተለይም ሁለገብ ሀገራዊ ጥረትን ለማገዝና ሀገራዊ እና ተቋማዊ ማሕበራዊ ኃላፊነትን ለመወጣት ተማሪዎችን በቴክኖሎጂው ማገዝ ከምንም በላይ አስፈላጊ እንደሆነም አስረድተዋል።

ፕሮጀክቱ ኢትዮ ቴሌኮም ከሚሰራቸው በርካታ ስራዎች ውስጥ አንዱ እንደሆነ የሚያነሱት ኃላፊዋ፤ በተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች ይተገበራል። ከእነዚህ መካከልም 66 የመንግሥት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በዋናነት የሚጠቀሱ ናቸው። ለዚህም አስፈላጊ የሆኑ ኮምፒዩተሮች፣ ልዩ ልዩ የትምህርት ቤት መገልገያ መሳሪያዎችን እና ከፍተኛ ፍጥነት ያለው መደበኛ የብሮድባንድ ኢንተርኔት አገልግሎት እንደተሟላላቸው ተናግረዋል።

በተጨማሪም ተማሪዎች ከሌላ ትምህርት ቤቶች ጋር መረጃ በቀላሉ መለዋወጥ እንዲችሉ፣ ማሕበረሰባዊ ለውጥ ማምጣት የሚችሉ የምርምር ሥራዎችን ለማከናወን፣ የመማር ማስተማሩን ሂደት ውጤታማ እና የተሻለ ለማድረግ፣ ተመርቀው ሲወጡ ለዲጂታል አለሙ ራሳቸውን ዝግጁ እንዲያደርጉ እና የዲጂታል ቴክኖሎጂውን በሚጠቀሙ እና በማይጠቀሙት መካከል ያለውን ክፍተት ለማጥበብ ከፍተኛ አስተዋጽኦ እንደሚኖረውም አስረድተዋል።

በመላ አገሪቱ ለሚገኙ 66 ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ከ 45 ነጥብ 48 ሚሊዮን ብር በላይ ወጪ በማድረግ 1 ሺህ 386 ዴስክቶፕ ኮምፒዩተሮች፣ 1 ሺ 386 ጠረጴዛዎችና ወንበሮችን፣ የትምህርት ቤት መገልገያ መሳሪያዎችን በማሟላት የዲጂታል የመማሪያ ማዕከሎቹን አቋቁሟል። በዚህም ከ140 ሺ 596 በላይ ተማሪዎች ተጠቃሚ ናቸው። ከእነዚህ 66 ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች መካከል 18 ትምህርት ቤቶች በአዲስ አበባ፣ የሚገኙ ሲሆን፤ ቀሪዎቹ 48 ትምህርት ቤቶች ደግሞ በክልሎች ያሉ እንደሆኑ አንስተዋል።

በአዲስ አበባ እና በክልሎች ያሉ ትምህርት ቤቶች በትምህርት ቢሮዎቻቸው አማካይነት መመረጣቸውን ገልጸው በኢትዮ ቴሌኮም የሪጅንና የዞን ጽህፈት ቤቶች አማካኝነት ስራዎች እየተከናወኑ መሆናቸውንም ወይዘሪት ፍሬህይወት ጠቅሰዋል። የትምህርቱ ዘርፍ ለሀገራችን ሁለገብ የልማት እንቅስቃሴ ያለውን ፈርጀ-ብዙ ሚና የሚወጣም መሆኑን አክለዋል።

እንደ ወይዘሪት ፍሬህይወት ማብራሪያ፤ የትምህርት ተቋማትን በቴክኖሎጂ የተደገፈና ጥራት ያለው ትምህርት በቀጥታ ስርጭት እንዲያገኙ ማድረግ፣ ከፍተኛ አቅም ባላቸው የገመድ እና የሳተላይት መገናኛ አማራጮች ማገናኘት (ስኩል ኔት)፣ የኢንተርኔት አገልግሎቶችን በነጻ እንዲሁም እስከ 86 በመቶ በሚደርስ ቅናሽ መስጠት በገንዘብ ሲተመን ከ 4 ነጥብ 8 ቢሊዮን ብር በላይ መሆኑንም አመልክተዋል። በተጨማሪም በ2014 ዓ.ም የትምህርት ዘመን በሀገር አቀፍ ደረጃ በ665 የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ለሚገኙ ተማሪዎች 16 ነጥብ 5 ሚሊዮን ብር የሚገመት 50 ሺ ደርዘን የመማሪያ ደብተሮችን በዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ውስጥ ለሚገኙ ተማሪዎች ልገሳ መካሄዱንም ገልጸዋል።

በ24 ትምህርት ቤቶች ለሚማሩ 9 ሺ ተማሪዎች ለትምህርት ቤት ምገባ መርሐ ግብር የሚውል 23 ነጥብ 4 ሚሊዮን ብር፣ በ 45 ዩኒቨርሲቲዎች ለተመረጡ 5ሺ 500 ተማሪዎች ለአንድ ዓመት የኪስ ገንዘብ የሚሆን 22 ሚሊዮን ብር መድቦ ለእያንዳንዱ ተማሪ በወር 400 ብር ድጋፍ እያደረገ እንደሚገኝ ያነሱት ኃላፊዋ፤ ከዚህ ባሻገር ሴቶች የመረጃ እና የዲጂታል ኢኮኖሚ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ለማስቻል 54 ነጥብ 4 ሚሊዮን ብር በሚገመት ወጪ 70 ሺ የሞባይል ቀፎዎችን ከሲም ካርድ ጋር በአገራችን 846 ወረዳዎች ለሚገኙ ሴቶች በስጦታ ማበርከቱን ተናግረዋል።

ሴት መምህራን በዲጂታል ቴክኖሎጂ ተደግፈው በተሰማሩበት የሙያ መስክ ውጤታማ እንዲሆኑ ለመደገፍ 50 ላፕቶፕና 200 ዘመናዊ የስልክ ቀፎዎችን በመላ ሀገሪቱ ለሚገኙ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ከፍተኛ አፈጻጸም ላስመዘገቡት መምህራን ሽልማት መስጠቱን ገልጸዋል።

ለትምህርቱ ዘርፍ ልህቀት አሁንም ቢሆን ተቋሙ ቁርጠኛ አቋም አለው የሚሉት ወይዘሪት ፍሬህይወት፤ በቅርቡ በአገሪቱ የተለያዩ አካባቢዎች ተከስቶ በነበረው ጦርነት ከፍተኛ የመሰረተ ልማት ውድመት የደረሰባቸውን የትምህርት ተቋማት መልሶ ለማቋቋምና ተማሪዎችን ወደ ትምህርት ገበታቸው ለመመለስ በአጭር የጽሁፍ መልእክት (9222) እና በቴሌብር መተግበሪያ አማካኝነት ድጋፍ ሰጪዎች አቅማቸው የፈቀደውን የገንዘብ መጠን ድጋፍ ማድረግ የሚችሉበትን ማመቻቸቱን አስታውሰዋል። እንደ አንድ ሀገራዊ ተቋም የትምህርት ዘርፉን በመደገፍ እና የተሻለ ትውልድ ለመገንባት የሚደረገውን ጥረት ለማገዝ እንዲሁም በማሕበረሰቡ ሁለንተናዊ የእድገት እንቅስቃሴ ላይ በቀጥታ በመሳተፍ ሀገራዊ አለኝታነቱንና ማሕበራዊ ኃላፊነቱን እንደሚወጣም በንግግራቸው አረጋግጠዋል።

ዲጅታል ማዕከሉን በተመለከተም የተቋሙ ሰራተኞች በሚያጋጥሙ ችግሮች ብቻ ሳይሆን በመማር ማስተማሩ ሥራ ጭምር በመግባት እንዲያግዙ ይደረጋልም ብለዋል።

ከዚህ ቀደም በትምህርት ቤቱ ቢበዛ አራት ኮምፒዩተር እንደነበር ያንን ለመጠቀም ከባድና ብዙ ሰው በአንዴ መግባት ስለማይችል ተከፋፍሎ መግባት የሚያስገድድ ከዛ በኋላም ያለው አጠቃቀም ውጤታማ እንዳልነበር የምትናገረው ደግሞ የከፍተኛ 23 ሁለተኛ ደረጃ የ 10ኛ ክፍል ተማሪዋ ሰሚራ መሀመድ ናት ፤ አሁን ግን የዚህ እድል ተጠቃሚ በመሆናቸው እጅግ ደስተኛ መሆኗንና አሁን ያለው ብዛቱ ብቻ ሳይሆን ፍጥነቱ የተሻለ ተደርጎ ዲጅታል ማዕከሉ በኢትዮ ቴሌኮም አማካኝነት መከፈቱ ችግራቸው እንደሚፈታ እምነት አላት።

የተከለያዩ ወርክ ሽቶችን አትሞ (ፕሪንት) እያደረጉ ለማጥናት መልካም እድሎችን እንደሚፈጥርላቸውም ተስፋ አድርጋለች። እናም ይህንን እድል ለሰጣቸው ኢትዮ ቴሌኮም ትልቅ አክብሮት እንዳላት ትገልጻለች።

‹‹የኮምፒዩተር ሳይንስና መሰል ቴክኖሎጂውን የሚነካኩ መስኮችን መርጦ ለመማርም ከወዲሁ ያዘጋጀናል›› የምትለው ደግሞ የዚሁ ትምህርትቤት የ12ኛ ክፍል ተማሪዋ ኢየሩሳሌም መኮንን ነች። እርሷ እንዳለችን፤ እስከ አሁን በነበረው የትምህርት ቆይታ ብዙ ከኮምፒዩተር ጋር የሚያገናኙን ነገሮች ቢኖሩን እድሉ ግን ጠባብ ነው። መረጃዎችን እንኳን ለማግኘት ሌሎች ማዕከላት ጋር መሄድ ግዴታችን ነበር ። በዚህም ወጪያችን ቀላል አይደለም። ከዚያም አልፎ ቤታችን ሆነን በሞባይል ዳታ ለመጠቀም ያልተጠበቀ ወጪ እናወጣለን። እናም ጥቂት ጊዜም ቢሆን እፎይታን ስለሚሰጠን በእድሉ ደስተኛ ነኝ ትላለች።

ለቀሪዎቹ በተለይም ለዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች እጅግ የሚያስደስት እድል ነው። እናም ጊዜው ሳያመልጣቸው እንዲጠቀሙበት ትመክራለች። እኛም እድሉ የተሰጣችሁ የመንግሥት ትምህርት ቤቶች ተጠቀሙበት አገራችሁን አስጠሩበት።

# የግማሽ ክፍለ ዘመን ሀገራዊ ሁነቶች በፎቶ ግራፍ ሲነገሩ

ኢያሱ መሠለ

የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ከተቋቋመ ከ1933 ዓ.ም ጀምሮ ላለፉት ሰማንያ አንድ ዓመታት ታላላቅ ሀገራዊ ሁነቶችን የሚገልጹ ፎቶግራፎችን ሰንዷል። ድርጅቱ ከሰሞኑ ከ1960ዎቹ ጀምሮ እስከ አሁን ድረስ የተከናወኑ ታላላቅ ሀገራዊ ሁነቶችን የሚያስቃኝ የፎቶግራፍ አውደ ርዕይ በማቅረብ ላይ ይገኛል።

‹‹ስለ ኢትዮጵያ›› የተሰኘውን የፎቶግራፍ አውደ ርዕይና የፓናል ውይይት በአስራ አንድ የኢትዮጵያ ከተሞች ለማቅረብ አቅዶ ወደተግባር የገባ ሲሆን ፤ በዚሁ መሰረት ዝግጅቱን በምስራቅ ኢትዮጵያ የተመረጡ ከተሞች አቅርቧል። በሶማሌ ክልል ጅግጅጋ ከተማ አንድ ብሎ የጀመረውን የፎቶግራፍ አውደ ርዕይና የፓናል ውይይት በድሬዳዋና ሐረር ከተሞችም ደግሞታል።

በድርጊትና በጊዜ ቅደም ተከተል ተደራጅተው ለእይታ የቀረቡት እነዚህ ፎቶ ግራፎች የሀገሪቱን የግማሽ ክፍለ ዘመን ፖለቲካዊ ውጣውረዶች፣ ማህበራዊ ክንዋኔዎች፣ ሃይማኖታዊና ባህላዊ እሴቶች ወዘተ የሚያስቃኙ ናቸው።

ጠቅለል አድርገን ስንመለከታቸው በንጉሱ ዘመን፣ በደርግ ዘመን፣ በኢህአዴግ ዘመን እና በአሁኑ ወቅትም ያሉትን ነባራዊ ሁኔታዎች የዳሰሰ ሲሆን በተለይም አሁን የመጣውን ሀገራዊ ለውጥ ተከትሎ ያለውን ፈተና ድልና ተስፋም የሚያሳዩ ናቸው።

የዘውድ አገዛዙን ዙፋን ከነቀነቁ የሕዝብ ጥያቄዎች መካከል መሬት ላራሹ ፤ የጎጃም አርሶአደሮች የግብር ይቀነስልን አመጽ እና የወሎ ረሃብ ተጠቃሽ ናቸው። የተማሪዎችን ተቋውሞ ተከትሎ ወታደራዊው መንግሥት ንጉሡን ከሥልጣን አውርዶ ወንበር የያዘበትን ሁኔታ ፤ የነጭና የቀይሽብር ግፎች ፣ የእድገት በሕብረት ዘመቻ ፣ የሲያድባሬን ወረራ ለመቀልበስ የተደረገውን ጥሪ እና የተሰጠውን ምላሽ የሚያሳዩ ፎቶግራፎች በአወደ ርዕዩ ላይ ተካተዋል።

ከደርግ ወድቀት በኋላ ሥልጣን የተቆጣጠረው ሕወሓት መራሹ የኢህአዴግ መንግሥት በ27 ዓመት የሥልጣን ቆይታው ሕገመንግሥት አርቅቆ ከማስጸደቅ ጀምሮ ለይስሙላህ ያከናወናቸው ምርጫዎችና የምርጫው ውጤት መጭበርበሩን ተከትሎ በተለይም ለተቃውሞ የወጡ የአዲስ አበባ ከተማ ወጣቶች ላይ የተፈጸመው ግድያ፤ በ‹‹ ኢሬቻ ሆራ ቢሾፍቱ›› መርሃ ግብር ላይ የሞቱና የተጎዱ ሰዎችን እንዲሁም በኦሮሚያና በአማራ ክልል ኢህአዴግን በመቃወም የተቀጣጠሉት ተቃውሞዎች፤ በፎቶግራፍ አውደ ርዕዩ ከተካተቱ ታሪካዊ ክስተቶች የሚጠቀሱ ናቸው።

ጠቅላይ ሚኒስትር ሃይለማርም ደሳለኝ ሰላማዊ በሆነ መንገድ ሥልጣናቸውን ሲያስረክቡ፤ ሕወሓት መራሹ ሥርዓት በሕዝቦች ተቃውሞና ትግል ተገርስሶ አዲሱ የለውጥ አመራር ሥራ ሲጀምር፤ በፖለቲካ ምክንያት ከሀገር የኮበለሉ ግለሰቦችና ድርጅቶች ወደሀገራቸው ሲመለሱ እና የትጥቅ ትግል ሲያደርጉ የነበሩትም ሰላማዊ ትግል እንዲያደርጉ ጥሪ ቀርቦላቸው ሲገቡ ፤ በፖለቲካ አመለካከታቸው ምክንያት የታሰሩ ሲፈቱ የነበረውን ሁኔታ ፎቶግራፎቹ ያስታውሳሉ።

ከሀገር ቤት እስከ ውጭ ሀገር ድረስ በተለያዩ ጉዳዮች የተደረጉ የድጋፍና የተቋውሞ ሰልፎች ፤ የብልጽግና ፓርቲ ምስረታና የሕወሓት ማፈንገጥንም እንዲሁ ፎቶ ግራፎቹ ይናገራሉ።

በተለይም አሸባሪው የሕወሓት ቡድን በሰሜን እዝ መከላከያ ሠራዊት ላይ የፈጸመውን ክህደትና ያደረሳቸውን ግፎች ፤ በአማራና አፋር ንጹሃን ዜጎች ላይ የፈጸማቸውን ሰቆቃዎች ፤ ያወደማቸውን ንብረቶች፤ ፎቶግራፎቹ ቁልጭ አድርገው ያሳያሉ።

መንግሥት በወሰደው ሕግ የማስከበር ርምጃ በሶስት ሳምንት ውስጥ የተገኘውን ድል፤ የመልሶ ግንባታና ርዳታ ፤ ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አህመድ በግንባር ተገኝተው ወታደራዊ አመራር ሲሰጡ የነበረው ሁኔታ በፎቶግራፎቹ ይገለጻል።

ኢትዮጵያ የውስጥና የውጭ ጫናዎችን ተቋቁማ ለመጀመሪያ ጊዜ ነጻ ፍትሃዊ፣ ተአማኒና ዴሞክራሲያዊ



ምርጫ አካሂዳ የብልጽግና መንግሥትን መመስረቷን፤ በፈተና ውስጥ ሆኗም ታላላቅ ሀገራዊ የልማት ሥራዎች መሠራታቸውን ከፎቶ ግራፎቹ መረዳት ይቻላል።

በጅግጅጋ፣ ድሬዳዋና ሐረር ከተሞች የተከናወኑትን የፎቶግራፍ አውደ ርዕዮች ተከትሎ የፓናል ውይይቶች ተካሂደዋል። በውይይቱ ላይ የፌዴራልና የክልል ከፍተኛ የመንግሥት ባለሥልጣናት፣ የሀገር ሽማግሌዎች፣ የጦር መኮንኖች ፣ ባለሀብቶች፣ አርቲስቶች ፣ ደራሲዎች ፣ ወጣቶች፣ ተማሪዎች እና እንደውይይቱ ርእሰ ጉዳዩ ጥሪ የተደረገላቸው ሌሎች አካላትም ተሳትፈዋል።

## በክልል ደረጃ የተካሄደ የመጀመርያ መድረክ

የፎቶግራፍ አውደ ርዕዩ ለመጀመሪያ ጊዜ በሶማሌ ክልል ጅግጅጋ ከተማ በተከፈተበት ወቅት የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ሥራ አስፈጻሚ አቶ ጌትነት ታደሰ አላማውን ሲናገሩ ‹‹ጊዜው ምክክርን፣ ሰላምንና አንድነትን የሚፈልግ ስለሆነ የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት የበኩሉን ለመወጣት ይህንን የውይይትና የሰላም መድረክ ጀምሮታል›› ብለዋል።

በአውደ ርዕዩ የተካተቱት ፎቶ ግራፎች በየዘመናቱ የተነሱ ጥያቄዎች ምን እንደነበሩ፤ በዘመኑ የነበሩ መሪዎች ጥያቄውን የመለሱበት መንገድ ምን እንደሚመስል የሚያስታውሱ ናቸው። የሚያስታውሱ ብቻ ሳይሆኑ ከዚያ እስከዚህ ድረስ የመጣንበት መንገድ ምን እንደሚመስልና በየሥርዓተ መንግሥቱ ያለውን ሁኔታ እንድናነጻጽር የሚያደርጉ ናቸው።

እንደ አቶ ጌትነት ገለጻ፤ የፎቶ ግራፉ አውደ ርዕዩ በዋናነት ያካተተው በንጉሱ ዘመን፣ በደርግ ዘመንና በአህአዴግ ዘመን የነበረውን የህዝብ ጥያቄና የሥርዓት ለውጥ ሲሆን፣ አሁን ያለውን ሀገራዊ ለውጥ ተከትሎ ያጋጠመውን ፈተና ፣ ድልና ተስፋ የውይይቱ ትኩረት አድርጎ ስለ ኢትዮጵያ ቀጣይነት ሁሉም የድርሻውን እንዲወጣ ማስቻል ነው።

የእለቱ የክብር እንግዳ የሕዝብ ተወካዮች አፈ ጉባኤ አቶ ታገሰ ጫፎ የፓናል ውይይቱን ሲያስጀምሩ እንደተናገሩት ፤ ‹‹ስለ ኢትዮጵያ›› የተሰኘው የፎቶግራፍ አውደ ርዕይና የፓናል ውይይት ስለኢትዮጵያ ሰላምና ብልጽግና ያገባኛል የሚለውን ጽንሰ ሐሳብ የያዘ ነው ብለዋል። በያገባኛል መንፈስ በመነጋገርና በመወያየት መሄድ ከተቻለ አገርን ማስቀጠል ይቻላል ብለዋል።

ያለንን በቅጡ መጠቀም ያልቻልነው መስማማት ስላልቻልን ነው ያሉት አቶ ታገሰ ጫፎ ተቀራርበን በመነጋገርና የችግራችንን ሰንኮፍ ነቅለን በመጣል ለብልጽግና ጉዟችን ራሳችንን ከወዲሁ ማዘጋጀት እንደሚጠበቅብን ተናግረዋል፤ ለዚህ ደግሞ ምክክርና ውይይት የግድ እንደሚል ገልጸዋል። የተዘጋጀው መድረክም ቀጣይ ለሚኖረው ሀገራዊ የምክክር መድረክ በር ከፋች ሊሆን ይችላል ብለዋል።

ኢትዮጵያን ለማሻገር በሰላምና በደህንነት ጉዳዮች መረባበረብ ማስፈለጉን ተናግረው እንዲህ አይነቱ መድረክም ችግሮችን ለመቅረፍ ጉልህ አስተዋጽኦ እንደሚኖረው ጠቅሰዋል። የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ይህን የመሰለ የፎቶግራፍ አውደ ርዕይና የፓናል ውይይት ማዘጋጀቱ የሚያስመሰግነው እንደሆነ ገልጸዋል።

የሱማሌ ክልል ርዕሰ መስተዳድር እና የመድረኩ አወያይ አቶ ሙስጠፌ መሃመድ በበኩላቸው እንደተናገሩት፤ ማንነትና ብዝሃነት ተፈጥሯዊ ስለሆኑ መካድ አይቻልም፤ ስለዚህ የባህልንና የሃይማኖት ልዩነትን ማክበር አስፈላጊ ነው፤ ኢትዮጵያ አንዱ የሌላውን ጉዳይ በማክበር ረገድ ችግር የሌላባት አገር እንደመሆኗ ይህንኑ ማስቀጠል የግድ ይላል ብለዋል። መቻቻልን በማስቀጠል አንዱ ክልል ከሌላው ክልል ጋር በመቀራረብ መልካም የሆነውን መማማር አስፈላጊ እንደሆነ ተናግረዋል።

ለአንድ ክልል አንድ ቋንቋ መናገርና አንድ ብሔር ብቻ መሆን በራሱ ለሰላም ዋስትና አይሰጥም ያሉት አቶ ሙስጠፌ፤ አንድ ቋንቋ ተናጋሪ እንዲሁም አንድ አይነት ሃይማኖት ተከታይ የሆኑ ሲገዳደሉ እንደሚስተዋሉ ገልጸው ሰላም የሚሰፍነው ሁሉም የየራሱን ኃላፊነት ሲወጣና በትዕግስት የተሻለውን አቅጣጫ ይዞ መጓዝ ሲችል ነው ብለዋል።

በፎቶግራፍ አውደ ርዕዩና በፓናል ውይይቱ ላይ የብልጽግና ፓርቲ የሕዝብና ዓለም አቀፍ ግንኙነት ዘርፍ ኃላፊ ዶክተር ቢቂላ ሁሪሳ እና የአማራ ክልል ብልጽግና ፓርቲ ጽህፈት ቤት ኃላፊ አቶ አብረሃም አለኸኝ የመነሻ ጽሑፍ አቅርበው ውይይት ተካሂዶበታል። የውይይት መነሻውን መሰረት በማድረግ ከተሳታፊዎች ጠቃሚ

ወቅታዊና ልዩ ልዩ

# ወቅታዊ






ሃሳቦች ተንሸራሽረዋል።

## ሁለተኛው የፎቶግራፍ አውደ ርዕይና የፓናል ውይይት

ሁለተኛው የፎቶግራፍ አውደ ርዕይና የፓናል ውይይት በድሬዳዋ ከተማ ሲካሄድ ትኩረቱን ያደረገው በኢኮኖሚው ዘርፍ በተለይም በኢንዱስትሪው ልማት ላይ ነበር። በመድረኩ ላይ የፌዴራልና የክልል መንግሥታት ከፍተኛ ባለሥልጣናት፣ ባለሀብቶችና ጥሪ የተደረገላቸው እንግዶች ታድመዋል።

የመድረኩ አወያይ የገንዘብ ሚኒስትሩ አቶ አህመድ ሽዴ እንደተናገሩት፤ የኢትዮጵያ መንግሥት ከሌሎች አገራት ኢንቨስትሮች በተሻለ የሀገር ውስጥ ባለሀብቶችን የመደገፍ ጽኑ ፍላጎት እንዳለው ተናግረዋል።

የሀገር ውስጥ እና የውጭ ባለሀብቶች ለኢኮኖሚው ያስፈልጋሉ ያሉት ሚኒስትሩ፤ ሁለቱንም በቅንጅት እንዲሠሩ በማድረግ በተለያዩ የኢንዱስትሪ ፓርኮችም ውጤት ማምጣት ተችሏል። ይሁንና የመንግሥት ዋና ዓላማ የሀገር ውስጥ ባለሀብቱን በመደገፍና በማብቃት አቅሙ እንዲጠናከር ማድረግ ነው ብለዋል።

የሀገር ውስጥ ባለሀብቱ ይበልጥ እንዲጠናከር ድጋፍ ይደረግለታል ሲባል ግን ኢንዱስትሪው በሀገር ውስጥ አቅም ብቻ ይሳካል ማለት አለመሆኑንም ገልጸዋል። የፋይናንስ፤ የቴክኖሎጂና መሰል አቅማችን ገና ውስን በመሆኑ ከውጭ ባለሀብቶች ጋር ተቀናጅቶ መሥራት ያስፈልገናል ብለዋል።

የአምራች ኢንዱስትሪውም ሆነ የአገልግሎት ዘርፉ የሚያድገው በዋናነት በግል ባለሀብቱ ተሳትፎ መሆኑን የተናገሩት ሚኒስትሩ፤ በመንግሥት በኩልም መሠረተ ልማትን ማስፋት፣ የሕግ የበላይነትን ማረጋገጥ፣ የውጭ ምንዛሬ አቅርቦትን በማሳደግ ረገድ አቅም በፈቀደው ልክ እንቅስቃሴ እየተደረገ መሆኑን ጠቁመዋል። በመንግሥት አገልግሎት አሰጣጥ ላይ ያለውን ቢሮክራሲ ለማቅለልም የተሻለ እየተሠራ ነው ብለዋል።

የሀገር ውስጥ ባለሀብቱ አቅም ሲጠናከር መዋዕለ ንዋያቸውንም መልሰው ለሀገር ለማዋል ያስችላቸዋል ያሉት ሚኒስትሩ የሥራ ዕድሎችን በስፋት የመፍጠር አቅም ይኖራቸዋል ብለዋል።

በዚህ አግባብ ሲታይ ከኢንተርፕራይዝ አንስቶ እስከ ከፍተኛ ኢንቨስትመንቶች ድረስ መንግሥት የመስሪያ ቦታ በማመቻቸት፣ የውጭ ምንዛሬ አቅርቦትን በማሳደግ፣ በልዩነት የተመረጡ የንግድ ስራዎች ላይ ኢትዮጵያውያን ብቻ እንዲሠሩ የተለያዩ ድጋፎችን ያደርጋል ሲሉ ሚኒስትሩ አስረድተዋል።

እንደ አቶ አህመድ ሽዴ ገለጻ፤ ኢትዮጵያ ውስጥ ባለሀብቱን ከመደገፍና ምርታማነትን ከማሳደግ አኳያ ያለው ችግር የፖሊሲ ሳይሆን ያሉትን ፖሊሲዎች በጥራት ማውረድና መፈጸም ላይ ነው።

የኢንዱስትሪ ሚኒስትሩ አቶ መላኩ አለበል የዘርፉን እንቅስቃሴ የሚገልጽ ጽሁፍ ሲያቀርቡ እንደገለጹት፤ የውጭ ምንዛሪ እጥረት ችግርን ለመፍታት የመጀመሪያውና መሠረታዊው መፍትሄ የአገር ውስጥ ምርትን ማሳደግ ነው።

አሁን የኢንዱስትሪዎች የምርታማነት አቅም 50 በመቶ እንደሆነና በተለያዩ ምክንያቶች የተፈጠረው የማምረት አቅም ማነስ በሚፈለገው ደረጃ ምርት እንዳይቀርብ ማድረጉን ገልጸዋል። በቀጣይ የአምራቹን አቅም ወደ 85 በመቶ ለማድረስ ውጥን መያዙን ጠቁመዋል።

አምራች ዘርፉ ከአጠቃላይ የአገሪቱ ጂዲፒ የስድስት ነጥብ ስምንት በመቶ ድርሻ እንዳለው የጠቆሙት አቶ መላኩ፤ ድርሻውን ወደ 17 ነጥብ ሁለት በመቶ ለማሳደግ እየተሠራ እንደሚገኝና ይህም ምርታማነትን ከማሳደግ ባለፈ የውጭ ምንዛሪ እጥረትንም ለማቃለል አይነተኛ መፍትሄ ይሆናል ብለዋል።

መንግሥት ዘርፉን ለማጠናከር በ‹‹ኢትዮጵያ ታምርት›› ንቅናቄ የአቅም ማጠናከር ሥራ እያከናወነ መሆኑን አስታውቀዋል።

የሚድሮክ ኢንቨስትመንት ግሩፕ ኃላፊ አቶ ጀማል አህመድ በግሉ ዘርፍ ባለው የአምራች ኢንዱስትሪ ተግዳሮትና ተያያዥ ጉዳዮች ዙሪያ ባቀረቡት ጽሁፍ እንደገለጹት፤ መንግሥት ለሀገር ውስጥ ባለሀብቶች የሚያደርገውን ድጋፍ ማሳደግ እንዳለበት ጠቅሰዋል። በተለይም የውጭ ምንዛሪ አቅርቦትን በፍትሐዊነት ለአምራች ኢንዱስትሪዎች በማቅረብ ዘርፉን ማሳደግ ይገባል ብለዋል።

በአምራች ኢንዱስትሪዎች ላይ የሚያጋጥሙ ዘርፈ ብዙ ችግሮች መኖራቸውን የጠቆሙት አቶ ጀማል መንግሥት ከግሉ ዘርፍ ጋር ያለውን ትብብር እያጠናከረ ከሄደ በአምራቾች ላይ የሚያጋጥሙ ችግሮችን በመቅረፍ ምርታማነትን ማሳደግ እንደሚቻል አመልክተዋል።

በፓናል ውይይቱ የድሬዳዋ አስተዳደር ከንቲባ አቶ ከድር ጁሀር የከተማዋን ኢንቨስትመንት አማራጮች እንቅስቃሴ የሚያሳይ ጽሁፍ አቅርበዋል።

## ሦስተኛው የፎቶግራፍ አውደ ርዕይና የፓናል ውይይት

ሦስተኛው መድረክ በዩኔስኮ የሰላም፣ የፍቅርና የአብሮነት ከተማ ተብላ በተመዘገበችው ሐረር ከተማ ተካሂዷል። የሐረሪ ክልል ርዕሰ መስተዳድር አቶ ኦርዲን በድሪ አውደ ርዕዩን በከፈቱበት ወቅት እንደተናገሩት፤ ከፎቶ ግራፍ አውደ ርዕይ በርካታ ቁም ነገሮችን መማር እንደሚቻል ጠቅሰው ፎቶግራፎቹ በሀገራችን የተከሰቱ ዋና ዋና ሁነቶችን፣ ከዘውዳዊው አገዛዝ ጀምሮ የነበሩ መንግሥታት ምን አይነት ባህሪያት እንደነበራቸውና በተለያዩ ጊዜያት የነበሩ የሕዝብ ጥያቄዎችና ትግሎችን በአጭር ሰዓት ውስጥ ማስረዳት የሚችሉ መሆናቸውን ተናግረዋል። በመክፈቻ መርሃ ግብሩ የተገኙት የኢትዮጵያ ብዙኃን መገናኛ ባለሥልጣን ዋና ዳይሬክተር አቶ መሐመድ እድሪስ በበኩላቸው፥ አውደ ርዕዩ ትናንትን ከዛሬ፣ ዛሬን ከነገ ያዋሃደ ትልቅ ሀገራዊ ፕሮጀክት መሆኑን ጠቅሰው፤ በአውደ ርዕዩ ኢትዮጵያ ባለፉት ዓመታት ያሳለፈቻቸውን ማሕበራዊ፣ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ውጣ ውረዶችን መመልከታቸው ተናግረዋል።

የሰላም ሚኒስትሩ አቶ ብናልፍ አንዷለም የውይይት መድረኩን መርተዋል። የባሕልና ስፖርት ሚኒስትሩ አቶ ቀጄላ መርዳሳ፣ የፌዴራልና የክልል የመንግሥት የሥራ ኃላፊዎች፣ ምሁራን፣ የሃይማኖት አባቶች፣ የሀገር ሽማግሌዎች፣ ወጣቶች፣ ተማሪዎች የተለያዩ የኅብረተሰብ ክፍል ተወካዮች፣ ታዋቂ ግለሰቦችና ተጋባዥ እንግዶች በውይይቱ ላይ ተገኝተዋል።

የሐረሪ ክልል ባህል፣ ቱሪዝምና ቅርስ ቢሮ ኃላፊ አቶ ተወለዳ አብዶሽ፣ የሕግ ባለሙያና ጠበቃ አቶ ቀለመወርቅ ሚደቅሳ እንዲሁም ዶክተር ወዳጄነህ መሃረነ የውይይት መነሻ ሃሳቦችን አቅርበዋል።

ጽሁፎቹ በኢትዮጵያውያን የሥነ-ልቦና ውቅርና የጋራ እሴቶች ላይ ትኩረታቸውን ያደረጉ ነበሩ። በውይይቱም ከትውልድ ወደ ትውልድ የተላለፉና ሀገርን በአንድነት ያስቀጠሉ የጋራ እሴቶችን አሟጦ መጠቀም እንደሚገባ ከተሳታፊዎች ተገልጿል። የጋሞ አባቶች የግጭት አፈታት ተሞክሮ ማሳደግ እንደሚስፈልግ፤ በየማሕበረሰቡ ጥቅም ላይ የሚውሉ መልካም እሴቶችን ማሳደግ እንደሚገባ ከተሳታፊዎች ተገልጿል።

በትውልዶች መካከል ያለውን ክፍተት እንዴት መሙላት እንደሚገባ ፤ በእድሜ ደረጃቸው ተለይተው በአዳራሹ ውስጥ የተቀመጡ ተሳታፊዎች የሚወክሉትን ትውልድ ተንተርሰው ሃሳብ ሰጥተዋል።

የሰላም ሚኒስትሩ አቶ ብናልፍ አንዱዓለም በማጠቃለያ ንግግራቸው ብዝኃነትን ያላከበረና ለብዝኃነት እውቅና ያልሰጠ ትውልድ አንድ እርምጃ ወደፊት መጓዝ እንደማይችል ተናግረዋል።

"እኔ አውቅልሃለሁ" ማለትና መገፋፋት ለሀገሪቷ እንደማይበጅ የገለጹት አቶ ብናልፍ ትውልዱን በሥነ-ምግባርና በእውቀት መቅረጽ ፤ የሰለጠነች፣ ዴሞክራሲ የሰፈነባት፣ ሰላሟ የተረጋገጠና የበለጸገች ኢትዮጵያ እውን ለማድረግ ይረዳል ብለዋል።

ወጣቱ ታሪኩን በሚገባ ለማወቅ መትጋት፣ ማንበብና እናትና አባቶቹ እንዲሁም ታላላቆቹን መጠየት እንዳለበትም አሳስበዋል። ኢትዮጵያውያን ዘመናትን የተሻገሩ በርካታ የጋራ እሴቶች ባለቤቶች መሆናቸውን የገለጹት የሰላም ሚኒስትሩ፤ ለዘመናት ያካበትናቸው የጋራ እሴቶች ተጠብቀው እንዲቆዩ የሽማግሌዎች ሚና ከፍተኛ መሆኑን ጠቁመዋል። በንግግራቸው የጋሞ አባቶችን ለአብነት ጠቅሰዋል።

አቶ ብናልፍ እንደገለጹት፤ አብዛኞቹ የሀገሪቱ ችግሮች ከልሂቃን የሚመነጩ መሆኑን ጠቅሰው ልሂቃን የመፍትሄው አካል ለመሆን መሥራት እንደሚጠበቅባቸውም አሳስበዋል።

በአጠቃላይ ስለኢትዮጵያ በሚል በተዘጋጀው በዚህ የፎቶግራፍ አውደ ርዕይ መነሻነት በሶስት ከተሞች የተካሄደው የውይይት መድረክ የግማሽ ክፍለ ዘመንን ፖለቲካዊ፣ ማሕበራዊና ኢኮኖሚያዊ ውጣ ውረድ ያሳየና ትውልዱ የመፍትሄ ሃሳቦችን በማመንጨት ኢትዮጵያን ወደፊት ለማሻገር በመግባባት ችግሮችን መፍታት እንዳለበት ያመላከተ ነው። መርሃ ግብሩ በቀጣይ ሊደረግ ለታሰበው ሀገራዊ ምክክርና መግባባት መንደርደሪያ መሆን ያስቻለ ነው።

# ዓለም አቀፍ

## ሩሲያ ለዓለም ሁለንተናዊ ደኅንነት ስትል ጦርነቷን ታቁም ስትል ዩክሬን ጠየቀች

አዲስ አበባ፡- ለዓለም ሁለንተናዊ ደኅንነት ሲባል ሩሲያ የምታካሂደውን ጦርነት ታቁም ስትል በእስያን ሀገራት የመከላከያ ጉባዔ ላይ ዩክሬን ጠየቀች።


በሲንጋፖር በተካሄደው የእስያ ሀገራት ቀጣናዊ የደኅንነት እና የመከላከያ ጉባዔ የዩክሬኑ ፕሬዚዳንት ቮሎድሚር ዘለንስኪ ከምስጢራዊ ቦታ ሆነው በበይነ መረብ ባስተላለፉት መልዕክት፣ የጦርነቱ ጦስ ሀገራቸውን ብቻ ሳይሆን የዓለምን ሥርዓት እንደሚያናጋው ማስጠንቀቃቸውን ዘ ስትሬይትስ ታይምስ ዘግቧል፡፡

ዘለንስኪ ኃያላን ሀገራት ታዳጊዎቹን እንደፈለጉ ቢያጠቁ እና ዓለም አቀፍ ሕግ ባይኖር ዓለም ትጠፋለች” በማለት በበይነ መረብ ባደረጉት የ10 ደቂቃ ንግግራቸው ፣ “ዓለምአቀፍ ሕግ ባይኖር ኖሮ እና ትልቁ ዓሳ ትንሹን ቢበላ ፣ ትንሹም ዓሳ ከእሱ ያነሱ ትንንሾቹን ቢበላ ማናችንም አንተርፍም ነበር” ብለዋል፡፡

ዘለንስኪ አክለውም ፣ የእስያ ሀገራት ድጋፋቸውን ለዩክሬን መስጠት እንዲቀጥሉና ለዓለም አቀፉ ማኅበረሰብ ከምግብ አቅርቦት ወጭ ንግድ ለማሳለጥ ሩሲያ የዘጋችውን የባህር ወደብ እንድትከፍት ግፊት እንዲያደርጉ ጠይቀዋል፡፡

ይህ ካልሆነ ግን ዓለም አቀፉ ማኅበረሰብ በተለይም እስያ እና አፍሪካ ለከፋ የምግብ ዕጥረት እና ለረሃብ እንደሚጋለጡ አስጠንቅቀዋል ፕሬዚዳንት ዘለንስኪ፡፡

በዚህ ዓመት የእስያ ሀገራት ቀጣናዊ የደኅንነት እና የመከላከያ ጉባዔ ላይ ከ 40 እስያ ሀገራት የተውጣጡ 575 ተወካዮች ተካፍለዋል፡፡






## አሜሪካ ከውጭ ለሚገቡ መንገደኞች ያስቀመጠችውን የኮቪድ ምርመራ መስፈርት አነሳች

አዲስ አበባ፡- አሜሪካ የአየር መንገደኞች ወደ ሀገሪቱ ከመግባታቸው በፊት የኮቪድ-19 ምርመራ ማረጋገጫ እንዲኖራቸው ያስቀመጠችውን ህግ አነሳች።

ህጉ የተነሳው ሀገሪቱ ኮቪድ-19ኝን ለመከላከል ባደረገችው ጥረት የቫይረሱ ታማሚዎች ቁጥር ከፍተኛ መሻሻል ማሳየቱን ተከትሎ መሆኑን የሀገሪቱ ባለስልጣናት ገልፀዋል፡፡

የሀገሪቱ የውጭ ጉዞ ኢንዱስትሪ የኮቪድ-19 ህጉ እንዲነሳ ግፊት ሲያደርግ እንደነበር የተገለፀ ሲሆን፣ በተለይም ወደ አሜሪካ የሚሄዱ ሰዎች ቀድመው ቦታ ለመያዝ በመስፈርቱ ምክንያት ሲቸገሩ እንደነበር ተመላክቷል፡፡

የሀገሪቱ የበሽታዎች መከላከያ እና መቆጣጠሪያ ማዕከል የኮቪድ ፖሊሲ ውሳኔውን በ90 ቀናት ውስጥ እንደገና ይገመግማል የተባለ ሲሆን፣ አዲስ የኮቪድ ስርጭት የሚስተዋል ከሆኑ እና ባለስልጣናቱ አስፈላጊ ነው ብለው ካመኑበት ህጉ ወደ ነበረበት ሊመለስ ይችላልም ነው የተባለው፡፡

አንድ የአሜሪካ ባለስልጣን ለጋዜጠኞች በሰጡት መግለጫ “ይህንን እርምጃ መውሰድ የቻልነው ቫይረሱን ለመከላከል ባደረግነው ከፍተኛ ጥረት ነው” ብለዋል፡፡

ሕይወት አድን የሆኑ ክትባቶችን እና ህክምናዎችን በስፋት ተደራሽ አድርገናል ያሉት ባለስልጣኑ፣ እነዚህ ክትባቶች እና ህክምናዎች የቫይረሱን ህመም እና ሞቶች እያስቀሩ ነው ማለታቸውን ቢቢሲ ዘግቧል፡፡

## ከኢፌዴሪ ትምህርት ሚኒስቴር ጋር በመተባበር በየሳምንቱ ሰኞና ዓርብ የሚታተም

# የጋራ ጥረትን የሚጠይቀው የሐሰተኛ የትምህርት ማስረጃ አሰጣጥ የማስቆም ስራ

**እዮሩስ ተስፋዬ**

በርካታ ውጣውረዶች ከሚገጥማቸው ዘርፎች መካከል የትምህርቱ ዘርፍ ከቀዳሚዎቹ ተርታ ይቀመጣል። ለበርካታ ዓመታት የተደራረቡ ችግሮች የትምህርት ጥራት ላይ ተጽዕኖ ከመፍጠር ባሻገር በነገው ሀገር ተረካቢ ትውልድ ላይ የሚያሳርፈው ጠባሳ ቀላል የሚባል አይደለም። ለችግሩም የመንግሥትም ይሁኑ የግል የትምህርት ተቋማት ድርሻቸው ከፍተኛ እንደሆነም ይገለጻል።

በተለይም በግል ትምህርት ተቋማት ከሚስተዋሉት ችግሮች አንዱ ሐሰተኛ የትምህርት ማስረጃ ሲሆን፤ የችግሩን አሳሳቢነት በመረዳት ግለሰቦችና አስመራቂ የትምህርት ተቋማት ላይ ሕጋዊ እርምጃ ለመውሰድ እየተሠራ መሆኑን የትምህርትና ሥልጠና ባለሥልጣን መግለጹ ይታወሳል። ባለሥልጣኑ የትምህርት ጥራትን ከመቆጣጠር ባሻገር የትምህርት ማስረጃ ትክክለኛነትን የማረጋገጥ ሥራን ያከናውናል። በዚህም ከፍተኛ የትምህርት ተቋማቱ የተማሪዎቻቸውን ዝርዝር መረጃና የትምህርት ማስረጃ ከምዝገባ እስከ ምረቃ ድረስ ለባለሥልጣኑ የመላክ ግዴታ አለባቸው።

በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የሰው ሀብት ልማት፣ ሥራ ሥምሪት እና ቴክኖሎጂ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴም በትምህርትና ሥልጠና ባለሥልጣን በመገኘት የመስክ ምልከታ ማድረጉ ይታወቃል። በዚህም መሠረት በርካታ የግል የትምህርት ተቋማት የሐሰተኛ የትምህርት ማስረጃ የሚታደልባቸው እየሆኑ በመምጣታቸው ጥብቅ ቁጥጥር እንዲደረግ የምክር ቤቱ ቋሚ ኮሚቴ አሳስቧል።

የትምህርትና ሥልጠና ባለሥልጣን ዋና ዳይሬክተር ዶክተር አንዱዓለም አድማሴ፤ ተቋሙ በተለያዩ አስቸጋሪ ሁኔታዎችም ውስጥ ሆኖ ኃላፊነቱን ለመወጣት ከፍተኛ ጥረት በማድረግ ላይ መሆኑን ለቋሚ ኮሚቴው ያስረዱ ሲሆን፤ ለሠራተኞች ቢሮ ምቹ ካለመሆኑ በተጨማሪ የቢሮ እጥረት በመኖሩ በአንድ ክፍል ውስጥ ከ30 በላይ ሠራተኞች በተጨናነቀ ሁኔታ ለመሥራት ተገደዋል።

ባለሥልጣኑ ከፍተኛ ሀገራዊ ኃላፊነት ተጥሎበት የሚሠራ ተቋም ቢሆንም ሰፊውን ሴክተር በበቂ ሁኔታ መፈጸም የሚችል የሰው ኃይል አደረጃጀት አለመኖሩንም ዋና ዳይሬክተሩ ጠቅሰው፤ ሕገ ወጥ የትምህርት ማስረጃ እና ሕገ ወጥ ተቋማት በየቦታው እየተበራከተ በመሆኑ ችግሩን ለማስተካከል ቀደም ሲል ከቋሚ ኮሚቴው ጋር መምከራቸውን አስታውሰዋል።

በምክር ቤቱ የሰው ሀብት ልማት፣ሥራ ሥምሪት እና ቴክኖሎጂ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ ዶክተር ነገሪ ሌንጮ፤ በርካታ የግል የትምህርት ተቋማት የሐሰተኛ የትምህርት ማስረጃ የሚታደልባቸው እየሆኑ መጥተዋል ያሉ ሲሆን፤ የትምህርት ዘርፍ ለሀገር ግንባታ ዋነኛ መሰረት በመሆኑ ችግሩን በዘላቂነት ለመፍታት ቀልጣፋና ዘመናዊ የአሠራር ሥርዓት በመዘርጋት ጥብቅ ቁጥጥር ማድረግ እንደሚገባ እና ከሚመለከተው አካል ተገቢ ፈቃድ ሳይሰጣቸው የሚሠሩ ተቋማት ላይ እርምጃ ሊወሰድባቸውና በሕግም ሊጠየቁ እንደሚገባ ይናገራሉ።

ዶክተር ነገሪ፤ ለዚህ ተግባር በተለይም የትምህርትና ሥልጠና ባለሥልጣን ከፍተኛ ኃላፊነት ያለበት መሆኑን ገልጸው፤ የቁጥጥርና ክትትል ተግባሩን አጠናክሮ እንዲቀጥል እንዲሁም በተቋሙ ለሥራ አስቸጋሪ የሆኑ ሁኔታዎች በተቻለ መጠን መስተካከል እንዲችሉ ቋሚ ኮሚቴው አስፈላጊውን ድጋፍ የሚያደርግ መሆኑንም ይገልፃሉ።

የቋሚ ኮሚቴው ምክትል ሰብሳቢ ዶክተር ኸይረዲን ተዘራ በበኩላቸው፤ የትምህርት ጥራትን ከማረጋገጥ አንጻር እንደ ሀገር ተቋሙ ትልቅ ተልዕኮ የተሰጠው በመሆኑ የሁሉንም ድጋፍና እገዛ እንደሚጠይቅ እንዲሁም በውስን የሰው ኃይል እና ምቹ ባልሆነ የሥራ ቦታ ተቋሙ ኃላፊነቱን እየተወጣ መሆኑን አድንቀው፤ ችግሮች እንዲፈቱ ቋሚ ኮሚቴው ድጋፍ እንደሚያደርግ ያስረዳሉ።


በተጨማሪም በባለሥልጣኑ ቅጥር ጊቢ ውስጥ የሚገኘው የሂሳብና ሳይንስ ትምህርቶች ማሻሻያ ማዕከል በርካታ ቢሮዎች ከአስር ዓመታት በላይ ተዘግተው



ዶክተር አንዱዓለም አድማሴ

መቆየታቸው ተገቢ አለመሆኑን ቋሚ ኮሚቴው ማስመዝገቡን ከኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት ያገኘነው መረጃ ያመለክታል። በተያያዘም የትምህርትና ሥልጠና ባለሥልጣን ከዓለም ባንክ ባገኘው የገንዘብ ድጋፍ ባለ ሰባት ወለል ህንጻ ለማስገንባት በሂደት ላይ መሆኑም ለማወቅ ተችሏል።

# ስፖርት



## አዲስ አበባ ቀጣዩን የኢትዮጵያ የወጣቶች ኦሊምፒክ ታዘጋጃለች

**ቦጋለ አበበ**

ባለፉት ሁለት ሳምንታት በሐዋሳ ከተማ ለመጀመሪያ ጊዜ ሲካሄድ በቆየው የኢትዮጵያ ወጣቶች ኦሊምፒክ አዲስ አበባ ከተማ የሜዳሊያ ሰንጠረዡን ቀዳሚ ሆና አጠናቃለች። የበርካታ ስፖርተኞች መቀመጫ የሆነችው አዲስ አበባ ከዚህ ቀደም በሚካሄዱ አገር አቀፍ ውድድሮች ከሌሎች ክልሎች አኳያ ውጤቷ የሚመጥናት እንዳልሆነ በተለያዩ አጋጣሚዎች ሲነገር ነበር። ይሁን እንጂ በዚህ የመጀመሪያ የወጣቶች ኦሊምፒክ ከተማዋ ከሌሎች ተሳታፊዎች የላቀ ውጤት በማስመዝገብ በሰፊ ልዩነት ልታጠናቅቅ ችላለች።

አዲስ አበባ በአጠቃላይ 44 የወርቅ፣28 የብርና 32 የነሐስ ሜዳሊያ በድምሩ 104 ሜዳሊያ በመሰብሰብ ነው ቀዳሚ ሆና ያጠናቀቀችው። የመጨረሻውን የወርቅ ሜዳሊያ ያስመዘገበችውም የኦሊምፒኩ የመዝጊያ መርሐግብር ላይ በተካሄደው የሴቶች እግር ኳስ ፍጻሜ አስተናጋጇ ሲዳማ ክልልን በመለያ ምት በመርታት ነው። አዲስ አበባን ተከትሎ ኦሮሚያ ክልል በ27 ወርቅ፣23 ብርና 25 ነሐስ በአጠቃላይ በስልሳ አምስት ሜዳሊያ ሁለተኛ ሆኖ ማጠናቀቁን አረጋግጧል። ደቡብ ክልል በ9 ወርቅ፣13 ብርና 21 ነሐስ በድምሩ በ43 ሜዳሊያ ሶስተኛ ደረጃን ይዞ የሚያጠናቅቅ ሆኗል። ጋምቤላ፣አፋር፣ሶማሌና ደቡብ ምእራብ ክልሎች በዚህ የመጀመሪያ የኢትዮጵያ ወጣቶች ኦሊምፒክ አንድም የወርቅ ሜዳሊያ ሳያስመዘግቡ ያጠናቀቁ ናቸው። ከፍተኛ ውጤት ያስመዘገበው የአዲስ አበባ ልኡካን ቡድን ትናንት ወደ አዲስ አበባ ተመልሶም በከንቲባ ጽህፈት ቤት ደማቅ




**በውጤት አሸብርቃ ያጠናቀቀችው አዲስ አበባ ቀጣዩን የኢትዮጵያ ወጣቶች ኦሊምፒክ እንድታዘጋጅ ተመርጣለች፣**

አቀባበል እንደተደረገለት ታውቋል።

“እውነተኛ ዕድሜ ለኢትዮጵያ ስፖርት ዕድገት “ በሚል መሪ ቃል የተካሄደው ይህ አንደኛው የኢትዮጵያ ወጣቶች የኦሊምፒክ ከሁለት የከተማ አስተዳደሮችና ዘጠኝ ክልሎች የተውጣጡ ከስድስት ሺ በላይ ስፖርተኞችን አሳትፏል። ውድድሮቹም ከኦሊምፒክ ስፖርቶች አትሌቲክስ፣ እግር ኳስ፣መረብ ኳስ፣ ቅርጫት ኳስ፣ እጅ ኳስ፣ ብስክሌት፣ ቦክስ፣ጅምናስቲክና ወርልድ ቴኳንዶ ፉክክር የተደረገባቸው ሲሆን ከኦሊምፒክ ስፖርቶች ውጪ ቼዝ፣ ኢንተርናሽናል ቴኳንዶና ውሹ መካተታቸው ታውቋል።

አዲስ አበባ የቀጣዩና ሁለተኛውን የኢትዮጵያ ወጣቶች ኦሊምፒክ አዘጋጅ በመሆንም ከሲዳማ ክልል አርማና የኦሊምፒክ ችቦውንም በሐዋሳ ዩኒቨርሲቲ የመዝጊያ መርሐግብር ላይ ተረክባለች። ቀጣዩ የወጣቶች ኦሊምፒክ ከሁለት ዓመት በኋላ ይካሄዳል።

በመዝጊያው መርሐግብሩ ላይ ንግግር ያደረጉት የኢትዮጵያ ኦሊምፒክ ኮሚቴ ፕሬዚዳንት ዶክተር አሸብር ወልደጊዮርጊስ የመጀመሪያው የኢትዮጵያ ወጣቶች ኦሊምፒክ ባለፉት ሁለት ሳምንታት ባካሄዳቸው በርካታ ውድድሮች ከመቼውም ጊዜ በበለጠ መቀራረብንና መተሳሰብን ፣ ብርቱ ፉክክርንና ውጤትን በከተማ አስተዳደሮችና በክልሎች መካከል በማሳየት በድምቀትና በታላቅ ስኬት መጠናቀቁን ገልጸዋል። እስካሁንም መሰል ውድድሮች በአገር አቀፍ ደረጃ አለመካሄዳቸው የሚያስቆጭ መሆኑን የተናገሩት ፕሬዚዳንቱ የኢትዮጵያን ስፖርት ማሳደግ ከተፈለገ ወጣቶች ላይ ትኩረት ያደረጉ መሰል ውድድሮች በየጊዜው መካሄድ እንዳለባቸው አብራርተዋል።

በመዝጊያ ሥነ ሥርዓቱም የኢትዮጵያ ፕሪሚየር ሊግ አክሲዮን ማህበር ፕሬዚዳንት መቶ አለቃ ፈቃደ ማሞ እንዲሁም የሲዳማ ክልል ከፍተኛ አመራሮችና የየክልሉ ስፖርት አመራሮች ተገኝተዋል:: የአፍሪካ ብሔራዊ ኦሊምፒክ ኮሚቴዎች ማህበር(አኖካ) ዋና ጸሐፊ አህመድ ሃሺም በልዩ እንግድነት የመዝጊያ ሥነሥርዓቱ ላይ የተገኙ ሲሆን ኢትዮጵያ በቀጣይ ዓመት የአፍሪካ ወጣቶች ኦሊምፒክን እንድታዘጋጅ ለኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ የማመልከቻ ደብዳቤ እንደሚያስገቡ ተጠቁሟል። አራተኛውን የአፍሪካ ወጣቶች ኦሊምፒክ ኢትዮጵያ እንደምታዘጋጅ ቀደም ሲል ተገልጾ እንደነበር የሚታወስ ሲሆን ግልጽ ባልሆነ ምክንያት ውድድሩ በግብጽ አዘጋጅነት ሊካሄድ እንደሚችል ሲነገር ቆይቷል። ይሁን እንጂ ግብጽም ይህን ታላቅ ውድድር እንደማታዘጋጅ የተገለጸ ሲሆን ኢትዮጵያ ዳግም አዘጋጅ እንድትሆን ዋና ጸሐፊው ጥያቄ እንደሚያቀርቡ ታውቋል።

ቢ.ጂ.አይ. ኢትዮጵያ BGI Ethiopia

# የጨረታ ማስታወቂያ

CASTEL

ቢ.ጂ.አይ– ነቀምት እና ሻምቡ መስመር፣ አሶሳ መስመር ፣ጋምቤላ መስመር፣ ነጆ እና መንዲ መስመር፤ ጊምቢ መስመር፣ ደምቢዶሎ መስመር የቢ.ጂ አይ ቢራ ምርቶችን ለማከፋፈል ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን መስፈርቶች የሚያሟሉ ተጫራቾችን አወዳድሮ ማሰራት ይፈልጋል፡

**ስለሆነም:-**

1. የንግድ ምዝገባ በተያዘው የኢትዮጵያ በጀት ዓመት የታደሰ
2. የንግድ ፈቃድ : በወቅቱ የኢትዮጵያ በጀት ዓመት የታደሰ
3. የተጨማሪ እሴት ታክስ ምዝገባ ምስክር ወረቀት
4. የግብር መለያ ቁጥር ምስክር ወረቀት
5. የስራ ማስኬጃ በቂ ካፒታል ያለው መሆኑን የሚያሳይ ማስረጃ ማቅረብ የሚችሉ
6. አከፋፋዩ የኃ.የተ/ የግ/ማ ወይንም የአክስዮን ማህበር ከሆነ ስራ አስኪያጁ ድርጅቱን መወከል የሚያስችል የውክልና ወረቀት ማቅረብ ይኖርበታል
7. የድርጅቱ የምስረታ ሰነዶች (ለ የኃ/የተ/የግ/ማ እና አ/ማ /
8. አዲስ ያልሆነና በስራ ላይ ያለ ድርጅት ከሆነ ያለፈው የበጀት ዓመት የሚያሳይ የሂሳብ መዝገብ ዝርዝር
9. አከፋፋይ የሆነው ግለሰብ/ ድርጅት የባንክ መግለጫ
10. በአካባቢው ለረጅም ጊዜ ነዋሪ የሆነና በአካባቢው ማህበረሰብ መልካም ስም ያለው፤
11. ማህበራዊ እና ህጋዊ ግዴታዎችን በአግባቡ እየተወጣ ያለና ማስረጃ ማቅረብ የሚችል፤
12. የስራ አስኪያጁ የታደሰ የቀበሌ መታወቂያ /መንጃ ፍቃድ/
13. የመጠጥ ወይንም ለስላሳ መጠጦች/ምርቶችን የማከፋፈል ልምድ ያለው ይበረታታል።

ከላይ በተጠቀሰው መሰረት መስፈርቶቹን የሚያሟሉ ማንኛውም ተወዳዳሪዎች ይህ ማስታወቂያ ከተነገረበት ቀን አንስቶ ባሉት 10 ተከታታይ የስራ ቀናት አስፈላጊውን ሠነድ አሟልተው አዲስ አበባ፣ ቢ.ጂ.አይ ፋብሪካ ዋና መስሪያ ቤት ሜክሲኮ አንደኛ ፎቅ በመምጣት መወዳደር ይችላሉ።

**ማሳሰቢያ:-**

ይህ ማስታወቂያና ይዘቱ በማናቸውም ሁኔታ በ ቢ.ጂ.አይ ላይ የውልም ሆነ የህግ ሀላፊነት የላቸውም።

ቢ.ጂ.አይ በከፊልም ሆነ በሙሉ የጨረታ ማስታወቂያውን የማሻሻል፣ የመቀየር ወይንም የመሰረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው።

ለስራው የተመረጡ አመልካቾች በስልክ የሚገለፅላቸው ይሆናል።

# ቢ.ጂ.አይ ኢትዮጵያ